አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ፎክሎራዊ እይታ በፍኖተሠላም አካባቢ

በ

የኔአሳብ የሠራህ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነ ሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

መስከረም 2004ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ፎክሎራዊ እይታ በፍኖተሠላም አካባቢ

በ

የኔአሳብ የሠራህ

አማካሪ

ጌታቸው ሳህለማርያም (ዶ/ር)

ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነ ሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የቆሎ ተማሪዎች ሕይወት ፎክሎራዊ እይታ በፍኖተሰላም አካባቢ

በ

የኔአሳብ የሰራህ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነ ሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

[illegible]

አማካሪ

ፊርማ

ዘሪሁን አስፋው

ፈታኝ

ፊርማ

ILS LIBRARY ADDIS

# አበርክቶ

ይቺ ስራ ከሩቅ በሚያዩት የእውቀት ብርሃን ልባቸው ሸፍቶ ከሞቀ ቤታቸውና ከሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸው ተለይተው ከቦታ ቦታ እየተንከራተቱ ለሚኖሩ የቆሎ ተማሪዎች ትሁንልኝ፡፡

ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምስጋና

ምኞቴ ሁሉ ተሳክቶ አይ ዘንድ  ከእራሴ በላይ የሚያስብልኝ ወንድም አለኝ።የአንተን መሰረታዊ ፍላጎት እንኳን ሳታሟላ የትምህርት ክፍያዬን በመሸፈንና በምንም ሊመነዘር የማይችል ወንድማዊ ምክርህን በመለገስ እዚህ ላደርስከኝ ወንድሜ ወርቂ ሞሴ ሁሉን አድራጊ አምላክ ውለታህን ይክፈልህ፡፡

ባለህ የተጣበበ ጊዜ (ተማሪ ነህና) ጠቃሚ ምክሮችን በመለገስና መጽሐፍትን በመጠቆም ለአገዘከኝ መምህሬ ለማ ንጋቱ (ጋሼ) ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡

የትየባ ስራውን በትዕግስት ለተወጣሽልኝ ማህሌት ታደሰ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

ማውጫ

ርዕስ ገፅ

አበርክቶ ..... I
ምስጋና ..... II
አጠቃሎ ..... III
ምዕራፍ አንድ ..... 1
1. መግቢያ ..... 1
1.1. የጥናቱ አነሳሻ ምክንያት ..... 2
1.2. የጥናቱ ዓላማ ..... 3
1.3. የጥናቱ ጥያቄዎች ..... 3
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 3
1.5. የጥናቱ ወሰን ..... 4
1.6. የጥናቱ ዘዴ ..... 4
ምልከታ ..... 5
ቃለ መጠይቅ ..... 5
1.6.1. የመረጃ ምንጮች ..... 5
1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ..... 6
ምዕራፍ ሁለት ..... 8
2. የፍኖተሰላም አካባቢ ዳራዊ መግለጫ ..... 8
2.1. መልካዓ ምድራዊ አቀማመጥና የህዝብ ብዛት ..... 8
2.2. መሰረተ ልማትና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ..... 8
2.3. ሐይማኖት ..... 9
2.4. መተዳደሪያ ..... 9
2.5. ታሪካዊ ቦታዎች ..... 10
2.6. መረዳዳትና መደጋገፍ ..... 10
ምዕራፍ ሶስት ..... 11
3. ክለሳ ድርሳን ..... 11
3.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 11

3.2. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት .................... 16

3.2.1 የቆሎ ተማሪዎች ስያሜ .................... 16

3.2.2 የቆሎ ተማሪዎች አኗኗር .................... 18

3.2.3. የፎክሎር ምንነትና ተዛማጅ ጽንሰ ሀሳቦች .................... 20

ምዕራፍ አራት .................... 27

4. የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ፎክሎራዊ እይታ .................... 27

4.1. ጉዞ .................... 27

4.2. ስም ቅየራ .................... 30

4.2.1. ከቤተሰብ ለመደበቅ .................... 30

4.2.2. እራስን ከመተት ለመከላከል .................... 31

4.2.3. ከመጽሐፍ ቅዱስ በመነሳት .................... 32

4.3. ልመና .................... 33

4.3.1. የመለመኛ ሰዓት .................... 33

4.3.2. የመንደር ድልድል .................... 34

4.3.3. የመለመኛ ቁሳቁሶች .................... 35

4.3.4. ማህበረሰቡ ለልመና ያለው አመለካከት .................... 38

4.3.4.1. አዎንታዊ አመለካከት .................... 38

4.3.4.2. አሉታዊ አመለካከት .................... 39

4.4. መረዳዳት .................... 41

4.4.1. አዲስ ተማሪ አቀባበል .................... 41

4.4.2. ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚደረግ እንክብካቤ .................... 44

4.5. ትምህርትና ወቅት .................... 45

4.5.1. ክረምት .................... 45

4.5.2. አብይ ፆም .................... 47

4.6. አዲስ ነገር ፈጠራ .................... 48

4.7. እውቀትና ማህበራዊ ደረጃ ........................................ 49

4.8. የእርስ በእርስ መማማር ........................................ 52

ምዕራፍ አምስት ........................................ 55
5. የቆሎ ተማሪ ተረቶች ........................................ 55
5.1. ትዝብትና ተቃውሞ ገላጭ ተረቶች ........................................ 55

5.2. ማንነትን ገላጭ ተረቶች ........................................ 59

5.3. ያጡትን ማግኛ ተረቶች ........................................ 62

ምዕራፍ ስድስት ........................................ 65
6. ማጠቃለያ ........................................ 65
ዋቢ ጽሑፎች ........................................ 68
አባሪ አንድ ........................................ 71
አባሪ ሁለት ........................................ 78
አባሪ ሶስት ........................................ 80
አባሪ አራት ........................................ 81

RSITY

# አጠቃሎ

"የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ፎክሎሯዊ እይታ በፍኖተሰላም አካባቢ" በሚል ርዕስ የተካሄደው ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው የቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ህይወት ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ ይህ ዓላማ ግቡን ይመታ ዘንድም ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎች ከቀዳማይና ካልአይ ምንጮች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበዋል፡፡

በዚህ ጥናት በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ ጊዜ ተደጋግመው የሚከሰቱና የተማሪዎች መገለጫ የሆኑ እንደ ጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ ልመና፣ መረዳዳት፣ ትምህርትና ወቅት፣ እውቀትና ማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም እርስ በእርስ መማማር የመሳሰሉ ጉዳዮች ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡ በተጨማሪም በቆሎ ተማሪዎች ዋና ገፀባህርይነት የሚተረኩ ተረቶች ይዘታቸውን መሰረት በማድረግ ከተማሪዎች ህይወት ጋር እየተቆራኙ ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡ ከጥናቱ መረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች የሚፈፅሟቸው እንደ ጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ ልመና ያሉ ጉዳዮች በተማሪዎች ዘንድ ሀይማኖታዊ፣ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ምክንያቶችን የያዙ ናቸው፡፡ እንዲሁም ማህበረሰቡ ለተማሪዎችና ለልመና ያለው አመለካከት ሁለት አይነት እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድ ተማሪዎች በአዎንታዊም ከአሉታዊም መንገድ እንደሚታዩ ማወቅ ተችሏል፡፡ ከጥናቱ መረዳት እንደተቻለው በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ክረምትና አብይ ጾም ሀሳባቸውን ሰብስበው ለመማርና አዲስ ነገር ለመፍጠር ስለሚያግዟቸው በጉጉት የሚጠበቁ የትምህርት ወቅቶች ናቸው፡፡ እንዲሁም በተማሪዎች ዘንድ በእውቀት በልጦ መገኘት በሚማሩበት ትምህርት ቤትም ሆነ በቀሪው ማህበረሰብ ዘንድ ያላቸውን ደረጃና ቦታ ከፍ እንዲሚያደርግ ጥናቱ ያሳያል፡፡

በመጨረሻም የቆሎ ተማሪዎች በዋና ገፀባህርይነት የተሳሉባቸው ተረቶች ይዘታቸው ከተማሪዎች ህይወት ጋር በቀጥታ እንደሚቆራኝ ማወቅ ተችሏል፡፡ ተረቶችም ተማሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ የታዘቡትን ነገር የሚቃወሙባቸው፣ የእራሳቸውን ማንነት የሚገለፁባቸውና የሚያጠናክሩባቸው እንዲሁም ያጡትንና የተከለከሉትን ነገር የሚያገኙባቸው እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንንም ሆነ አዲስ ኪዳንን ቀድማ በመቀበል የታወቀች ሀገር ናት፡፡ ኢትዮጵያ በ4ኛው ክፍለ ዘመን ክርስትናን ከተቀበለች በኋላ ሀይማኖታዊ ትምህርት በተለያየ መንገድ ስትሰጥ ቆይታለች፡፡ ክርስትናን ከመቀበሏ ጋር ተያይዞ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ሊቃውንትን ለማፍራት ሀይማኖታዊ ትምህርት በሰፊው ይሰጥ ነበር (Pankhurst; 1966,27)፡፡ ብዙውን ጊዜ ሀይማኖታዊ ትምህርት ይሰጥ የነበረው በቤተክርስቲያን የበላይ ጠባቂነት ነው፡፡ ከክርስትና ሀይማኖት መስፋፋት ጋር በተያያዘም በተለያየ መልኩ በተለይም ለወጣቶች በይዘቱ ሰፋ ያለ እና በአቀራረቡ የጠነከረ ትምህርት ይሰጥ ነበር (ሀይለማርያም፣ 1963፡42)። ይህንን ሀይማኖታዊ ትምህርት ከሚከታተሉት ወጣቶች መካከል በተለምዶ የቆሎ ተማሪዎች ተብለው የሚታወቁት ተቀዳሚ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

የቆሎ ተማሪዎች ለቤተክርስቲያን አገልጋይ ለመሆን በቤተክርስቲያን ሀላፊነት መምህር ተዘጋጅቶላቸው የሚማሩ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት መቼ እና የት ጉባኤ ዘርግተው ማስተማር እንደጀመሩ በውል ባይታወቅም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን በተደራጀ መልኩ በየቤተክርስቲያኑ የተጠናከረ ትምህርት ይሰጥ እንደነበር የሚያስረዱ መረጃዎች ይገኛሉ (Pankhurst; 1966,28)፡፡ የቆሎ ተማሪዎች ይህንን ሀይማኖታዊ ትምህርት በቤተክርስቲያን ዙሪያ ተሰባስበው ሲከታተሉ የእራሳቸው የሆነ የትምህርት ስርዓት፣ የአኗኗር ብልሃትና የህይወት መገለጫዎች አሏቸው፡፡ የትምህርት ስርዓታቸውም በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ የንባብ ቤት፣ የዜማ ቤት፣ የቅኔ ቤትና የመጽሐፍ ቤት በመባል ይታወቃሉ፡፡ በሌላ በኩል በትምህርት ቤት ህይወታቸው የእኛ የሚሏቸውና ከቀሪው ማህበረሰብ ጋር የሚጋሯቸው የሕይወት መገለጫዎች አሏቸው፡፡ ይህ ጥናትም የቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ህይወት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው፡፡

ጥናቱ በስድስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ መግቢያ ሲሆን በውስጡም የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱን ጥያቄ፣ የጥናቱን አስፈላጊነት፣ የጥናቱን ዘዴ፣ የመረጃ ምንጮች፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎችን አካቷል፡፡ ምዕራፍ ሁለት ጥናቱ ስለተካሔደበት አካባቢ አጭር መግለጫ ይዟል፡፡ በውስጡም የአካባቢውን ስያሜ አመጣጥ፣

መልካዓምድራዊ አቀማመጥ፣ የህዝብ ብዛት፣ የገቢ ምንጭ፣ ቋንቋ፣ ሀይማኖትና የመሳሰሉትን መረጃዎች ይዟል፡፡ ምዕራፍ ሶስት ላይ ክለሳ ድርሳናት በሚል አቢይ ርዕስ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና የንድፍ ሀሳብ ቅኝቶች ቀርበዋል፡፡ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በሚለው ንዑስ ርዕስ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የቆሎ ተማሪዎችን የጥናታቸው ትኩረት ያደረጉ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችና የጥናት ወረቀቶች ቀርበዋል፡፡ እንዲሁም የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ስር ስለቆሎ ተማሪዎች ስያሜና አኗኗር የተለያዩ ጸሐፊዎች ያቀረቡት ሃሳብ እንዲሁም ስለፎክሎር ምንነትና ተዛማጅ ጽንስ ሀሳቦች ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡

ምዕራፍ አራት የጥናቱ ዋና ርዕስ ሲሆን የቆሎ ተማሪዎችን ህይወት ፎክሎራዊ ጉዳዮች የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ተደጋግመው የሚከሰቱ እንደ ጉዞ፣ ስም ቅየራ፣ ልመና፣ መረዳዳት፣ ትምህርት እና ወቅት፣ እውቀትና ማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም እርስ በእርስ መማማር የሚሉት ጉዳዮች ከነ ንዑስ ርዕሳቸው ተካተው ቀርበዋል፡፡ በምዕራፍ አምስት ደግሞ በቆሎ ተማሪዎች ገጸባህሪነት የሚተረኩ ተረቶች ከተማሪዎች ህይወት ጋር ያላቸው ቁርኝትና ተደጋግመው የሚነሱ ይዘቶች ምን እንደሆኑ ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡ የመጨረሻውና ስድስተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ የቀረበበት ምዕራፍ ነው፡፡ ጥናቱ በመጨረሻም ዋቢ መጽሐፍትንና የተለያዩ አባሪዎችን አካቷል፡፡

### 1.1. የጥናቱ አነሳሻ ምክንያት

ይህንን ጥናት ለማጥናት ካነሳሱኝ ምክንያቶች መካከል በቅድሚያ የሚጠቀሰው የቆሎ ተማሪዎችን ህይወት በሰፊው የዳሰሰ ጥናት አለማግኘቴ ነው። በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ለተለያዩ ኮርሶች ማሟያ የተለያዩ ጥናታዊ ወረቀቶችን የማንበብ ዕድሉ ገጥሞኝ ስለነበረ የቆሎ ተማሪዎችን ህይወት በሰፊው የዳሰሰ ጥናት ባለማግኘቴ ይህን ጥናት ለማድረግ ተነሳስቻለሁ፡፡ በተጨማሪም፡-

1. በአደግሁበት ፍኖተሰላም አካባቢ ለቆሎ ተማሪዎች ቅርበት ስለነበረኝ በትምህርት ቤት ህይወታቸው ተደጋግመው ከሚከሰቱ ሁኔታዎች በመነሳት ህይወታቸው ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ካለኝ ጉጉት የተነሳ
2. እንዲሁም በተለምዶ 'ተሜ' እየተባሉ የቆሎ ተማሪዎች በገጸባህሪነት የሚሳሉባቸው ተረቶች ይዘታቸው ምን ይሆን? ከህይወታቸው ጋር ያላቸው ግንኙነትስ እንዴት

ተገልጸ ይሆን ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ካለኝ ፍላጎት የተነሳ ይህ ጥናት ሊካሄድ ችሏል፡፡

### 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በፍኖተሰላም አካባቢ የሚገኙ የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ በውስጡም የሚከተሉትን ንዑሳን ዓላማዎች አካቷል፡፡

1. በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ተደጋግመው የሚከሰቱ የህይወት መገለጫዎች ምን ምን እንደሆኑ መጠቆም፣
2. የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው የሚያልፉባቸውን ደረጃዎች ማሳየት፣
3. የቆሎ ተማሪዎች ስለ ማህበረሰቡ፣ ቀሪው ማህበረሰብ ስለ እነሱ ያለውን አመላካከት መግለጽ
4. የቆሎ ተማሪዎች በገጸ ባህሪይነት የሚሳሉባቸው ተረቶች ይዘታቸው ምን ምን እንደሆነና ከህይወታችው ጋር ያላቸውን ቁርኝት ማመልከት

### 1.3. የጥናቱ ጥያቄዎች

ከላይ የተነሱትን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በዚህ ጥናት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ተደርጓል፡፡

1. የቆሎ ተማሪዎች ተለይተው የሚታወቁባቸው የህይወት መገለጫዎች ምን ምን ናቸው?
2. የቆሎ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ሲያልፉ የሚያገኙት ነገር ምንድን ነው?
3. ማህበረሰቡ ስለተማሪዎች ተማሪዎችስ ስለማህበረሰቡ ያላቸው አመላካከት ምን ይመስላል?
4. በቆሎ ተማሪዎች ገጸባህሪይነት የሚተረኩ ተረቶች ይዘታቸው ምንድን ነው? ከተማሪዎች ህይወት ጋርስ በምን ይገናኛሉ?

### 1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ የቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ህይወት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ይህ ጥናት የቆሎ ተማሪዎችን የተለያዩ ጉዳዮች (ለምሳሌ ስነቃሎቻቸውን፣ የትምህርት አሰጣጡን፣ እያንዳንዱን የክፍል ደረጃ ወዘተ) ከፋፍሎ

ማጥናት ለሚፈልግ ተመራማሪ ጥቅል የሆነ የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም የእነዚህን ተማሪዎች ህልውና ለማስቀጠል ለሚንቀሳቀሱ (ለምሳሌ እንደ ማህበረ ቅዱሳን ላሉ ድርጅቶች) ተማሪዎች በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ መረጃ ይሰጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

### 1.5. የጥናቱ ወሰን

ማንኛውም ጥናት ይዞት የተነሳው ዓላማ ይሳካ ዘንድ የእራሱ የሆነ የጥናት ወሰን ይኖረዋል፡፡ ይህ ጥናትም ከቦታ አንጻር በጎጃም፣ ፍኖተሰላም አካባቢ ላይ ብቻ በሚገኙ የቆሎ ትምህርት ቤቶች ላይ ተወስኗል፡፡በጥናቱም ሁለት የቅኔ ቤት ጉባኤዎች፣ አንድ የዜማ ቤት ጉባኤና አንድ የንባብ ቤት ጉባኤ በ ናሙናነት ተወስደዋል።ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ መጠን የቆሎ ተማሪዎችን የትምህርት አሰጣጥ ከስነ ትምህርት ንድፍ ሃሳብ አንጻር አልተመለከተም፡፡ ህይወታቸውን ለማሳየት ግን የትምህርት አሰጣጥ እንደ አስፈላጊነቱ ተነስቷል፡፡ በቆሎ ተማሪዎች ከሚነገሩና ስለቆሎ ተማሪዎች ከሚነገሩ ስነቃሎች መካከል በተረቶች ላይ ብቻ እንዲገደብ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ከቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ደረጃዎች መካከል በንባብ ቤት፣ በዜማ ቤትና በቅኔ ቤት ላይ ብቻ በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ የመጽሐፍት ቤት ተማሪዎችን ጥናቱ አይመለከትም (ምክንያቱን በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ከሚለው ክፍል ላይ ይመልከቱ)፡፡

### 1.6. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው የቆሎ ተማሪዎችን ህይወት ማሳየት ነው፡፡ ስለሆነም ገላጭ የምርምር ስልትን ተጠቅሟል፡፡ በመስክ ጊዜ የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግም የይዘት ትንተና እና ትርጎማ እንደአስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ በፎክሎር ጥናት መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና፣ መጠይቅ ዋና ዋናዎቹ ዘዴዎች ናቸው (ፈቃደ፣ 1991ዓ.ም) በዚህ ጥናትም ምልከታና ቃለ መጠይቅ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ናቸው፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችም በፎቶና በድምጽ ማስረጃዎች ተደግፈው ቀርበዋል፡፡

ምልከታ

በዚህ ጥናት ምልከታ የተመረጠበት ምክንያት የተማሪዎችን የእለት ከእለት ክንውን በቀጥታ በማየትና በመስማት በመርጃ መሳሪያዎች ለመሰብሰብ ታስቦ ነው፡፡ ምክንያቱም ምልከታ የሚጠቅመው ለጥናት በተመረጠው ቦታ በቀጥታ በመገኘት መረጃዎችን በተለያየ መልኩ ለመሰብሰብ ነው፡፡ (Goldstin; 1964,77) በዚህ ጥናትም ተማሪዎች በሚኖሩባቸው ጎጆዎች፣ የመማሪያ ጉባኤዎች፣ የቆጠራ ስፍራዎች ወዘተ ላይ በመገኘት መረጃዎችን ከምንጫቸው ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡

በምልከታ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሶስት አይነት መንገዶችን መጠቀም ይቻላል፡፡ ተፈጥሮአዊ መቼት ፣ አርተፊሻል ፣ እና ቅንብር ተፈጥሮአዊ መጠቀም ይቻላል፡፡ (ፈቃደ 1991፡122-123) በዚህ ጥናትም በተፈጥሮአዊ መቼት መረጃ በሰፊው ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎችንም ሆነ ቁልፍ የመረጃ ምንጮችን ስለቆሎ ተማሪዎች የሚነገሩ ተረቶችን እንዲነገሩ በመጠየቅ አርተፊሻል በሆነ መልኩ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ሰዎች ስለሚያውቋቸው የተለያዩ ጉዳዮች ጥቂዎችን በአካል ቀርቦ በመጠየቅ መረጃ ከምንጩ የሚገኝበት መንገድ ነው፡፡ ስለሆነም (ፈቃደ 1991) እንደሚመክረው ዝግ እና ክፍት ጥያቄዎችን በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ለቃለ መጠይቁ የተዘጋጁ ጥቂዎችም በግማሽ የተዋቀሩ እና እንደሁኔታው የመጠየቁ ናቸው፡፡

### 1.6.1. የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች ተሰብስበዋል፡፡ ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉትም በሁለት የተከፈሉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ከመስክ ስራ በፊት የተለያዩ መዛግብትን በማገላበጥ የተገኘ መረጃ ነው፡፡

በዚህ መሰረት ስለ ፎክሎርና ስለቆሎ ተማሪዎች የተጻፉ መጽሐፍት፣ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች፣ የጉባኤ ህትመቶችና ጥናታዊ ጽሑፎች ወዘተ በመረጃ ምንጭነት አገልግለዋል፡፡ መረጃዎችንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በሚገኙ የኬኔዲ፣ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ቤተመጽሐፎችና እንዲሁም በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤትና በማህበረ ቅዱሳን ቤተ መጽሐፎች ተሰብስበዋል፡፡ ሁለተኛው የመረጃ ምንጭ በመስክ ስራ ሂደት የተገኘ መረጃ ነው በመስክ ስራውም በዋናነት መረጌታዎች፣ የቆሎ

ተማሪዎች፣ የእቤት እመቤቶችና የእድሜ ባለጸጋ አዛውንቶች ቁልፍ መረጃ አቀባዮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ እንዲሁም የቤተክህነት ሀላፊዎች እና የወረዳ ጽሕፈት ቤት ሀላፊዎች ተጨማሪ መረጃዎች በመስጠት አገልግለዋል። እነዚህ መረጃ አቀባዮችም የተመረጡት ለጉዳዩ ባላቸው ቅርበትና በአካባቢው ማህበረሰብ ካላቸው ተቀባይነት በመነሳት ነው። በአጠቃላይ ሀያ አንድ ሰዎች በመረጃ አቀባይነት አገልግለዋል ፡፡ ከእነዚህም መካከል ሶስትመሪጌታዎች (መምህሮች)፣ አምስት ተማሪዎች፣ አንድ የእቤት እመቤት፣ አንድ የእድሜ ባለጸጋ አዛውንት በአጠቃላይ አስር ሰዎች ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ነበሩ፡፡

## 1.7. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይህ ጥናት ሲካሄድ ብዙ ያጋጠሙ ችግሮች ነበሩ፡፡ ከአጋጠሙ ችግሮች መካከል ትልቁን ድርሻ የሚወስደው ከወቅት ጋር የተያያዘው ችግር ነው፡፡ የመጀመሪያው የመስክ ጉዞ የነበረው ከሚያዚያ 26 እስከ ግንቦት 15፣ 2003ዓ.ም ባለው ጊዜ ነበር፡፡ ወደፊት በምዕራፍ ሶስት በሰፊው እንደሚገለጸው ተማሪዎች በየጉባኤው ተሟልተው የሚገኙት በአቢይ ጾምና በክረምት ወቅት ነው፡፡ ነገር ግን የመጀመሪያ የመስክ ጉዞዬ የአብይ ጾም ካለፈ በኋላ እና ክረምቱም ከመግባቱ በፊት ስለነበረ ብዙዎች ተማሪዎች ለፋሲካ በዓል ወደየቤተሰቦቻቸው ከሄዱበት አልተመለሱም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያትም በተዟዟርኩባቸው ጉባኤዎች ብዙ ተማሪዎችን አግኝቼ መረጃ ለመሰብሰብ ተቸግሬ ነበር፡፡ ነገር ግን በሁለተኛ ዙር የመስክ ጉዞዬ ማለትም ከሰኔ 13 እስከ ሰኔ 24 2003ዓ.ም ባለው ጊዜ ተማሪዎች በየጉባኤው ከመጀመሪያው ዙር ጉዞ በአንድና በሁለት እጥፍ ጨምረው ማግኘት ስለቻልኩ መረጃውን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ሌላውና ሁለተኛው ችግር አብዛኛው የዜማም ሆነ የቅኔ ትምህርት የሚሰጠው ማታ በተለይም ከለሊቱ አስር ሰዓት ጀምሮ በመሆኑ መረጃዎችን ከአውዳቸው ለመሰብሰብ ችግር ገጥሞኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ቀስ በቀስ ከተማሪዎች ጋር በመግባባት እና ከመርጌታዎች ቤት በማደር ሌሊት ሲነሱ አብሬ በመነሳት መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ሶስተኛው ችግር አጥኚው በእቅዱ አራቱን የቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ደረጃዎች ማለትም የንባብ ቤት፣ የዜማ ቤት፣ የቅኔ ቤትና የመጽሐፍት ቤትን ለመመልከት አስቤ የነበረ ቢሆንም ተማሪ በመጥፋቱ ምክንያት የመጽሐፍት ቤት ጉባኤ ታጥፏል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት በሶስቱ የትምህርት ደረጃዎች ብቻ እንዲካሄድ ሆኗል። በመጨረሻ ላይ

የገጠመው ችግር ከህይማኖት ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ይህ ጥናት ከመካሄዱ በፊት የተለያዩ ግለሰቦች ጥናት እናደርጋለን፣ እርዳታ እናመጣላችኋለን፣ መጽሐፍት እንሰጣችኋለን በማለት በየትምህርት ቤቶቹ እየገቡ የሌላ ህይማኖት ሲሰብኩ ተገኝተዋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ምንም እንኳን ከወረዳው ሰበካ ጉባኤና ከወረዳው አስተዳደር ጽህፈት ቤት የተጻፈ ደብዳቤ የያዝሁ ቢሆንም አንዳንድ ጉባኤዎች ተቀብለው ሊያስተናግዱኝ ፈቃደኛ አልነበሩም ነገር ግን የወረዳው ሰበካ ጉባኤ ጸሐፊ መሪጌታ ዳዊት ነብዩ አብረውኝ ቦታው ድረስ በመሄድና መሪጌታዎች ለገበያ በመጡበት በማስተዋወቅ ችግሩ ተቀርፎ መረጃ ልሰበስብ ችያለሁ፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተከፍተው ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ መካከል በፍኖተሰላም ከተማ ብቻ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ አንድ የከፍተኛ ትምህርትመሰናዶ ትምህርት ቤት እንዲሁም አንድ የመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅና አንድ የቴክንክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም እንደሚገኙ ከወረዳው ትምህርት ፅህፈት ቤት በተገኘ መረጃ ማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በወረዳው አንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ አንድ ሆስፒታልና ሶስት የጤና አጠባበቅ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ በአሁኑ ወቅት የወረዳው ዋና ከተማ የሆነችው ፍኖተሰላምን ጨምሮ ሶስት ከተማዎች የ24 ሰዓት የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ ሲሆኑ የንፁህ የመጠጥ ውሃና የስልክም ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡

## 2.3. ሐይማኖት

በወረዳው ከሚኖረው ህዝብ መካከል 99% የሚሆነው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ተከታይ ነው፡፡ ቀሪው 1% ደግሞ የእስልምና፣ የፕሮቴስታንት እና የካቶሊክ እምነት ተከታይ ነው። የወረዳው ቤተክህነት ሀላፊ ከሆኑት መላዕከ ሰላም ኤፍሬም ሙሉአለም ሰኔ 16-10-2003ዓ.ም በተደረገ ቃለ መጠይቅ መረዳት እንደተቻለው በወረዳው ከሚገኙ ከ67 በላይ ጎጦች (ንዑስ የገጠር ቀበሌዎች) መካከል አንድ ጎጥ ብቻ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ ነው፡፡ የተለያዩ ሀይማኖቶች ተከታይ የሆኑትም አብዛኞቹ በከተማ እንደሚገኙ ለመረዳት ተችሏል፡፡ እያንዳንዱ የገጠር ጎጥ (ንዑስ ቀበሌ) የሚጠራውና ተለይቶ የሚታወቀው በአካባቢው ባለው ቤተክርስቲያን ስም ነው፡፡ ከ67 በላይ የሚሆኑት ንዑስ ቀበሌዎች የሚጠሩት በቤተክርስቲያን ስያሜ ነው፡፡ ግንቦት 7፣ 2003ዓ.ም ከወረዳው ቤተክህነት በተገኘ መረጃ መሰረት ወደ አስራ ስምንት የሚደርሱ ቤተክርስቲያኖች መምህር ተመድቦላቸው በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ አዘመር ጊዮርጊስ፣ ቦንጊት ማሪያም፣ የልማዳር አቦ ወ.ዘ.ተ በመባል ተለይተው ይታወቃሉ፡፡

## 2.4. መተዳደሪያ

በወረዳው ከሚኖረው ህዝብ መካከል 94% የሚሆነው መተዳደሪያው ግብርና ሲሆን አስተራረሱም ባህላዊ አስተራረስ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ቀሪው 6% ደግሞ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመንግስት ተቀጣሪ በመሆንና በንግድ ስራ የሚተዳደር ነው፡፡ በወረዳው ባህላዊ የአስተራረስ ዘዴን በመጠቀም እንደ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ አተርና ባቄላ የመሳሰሉት በብዛት ይመረታሉ፡፡ ነገር ግን በምዕራብ ጎጃም ዞን ከሚገኙት ዘጠኝ

ወረዳዎች መካከል ወረዳው በሎሚ፣ በሸንኮራ አገዳና በጤፍ ምርቱ ተለይቶ ይታወቃል፡፡ ዋና ዋና ምግቦቻቸውም ከበቆሎና ከጤፍ የሚዘጋጅ እንጀራ እንዲሁም ከአተርና ከባቄላ የሚዘጋጅ ሽሮ ወጥ ናቸው፡፡

## 2.5. ታሪካዊ ቦታዎች

የወረዳው ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት ታሪካዊ ቦታዎች ብሎ ከሰየማቸው መካከል በጣልያን ወረራ ጊዜ እንደተሰራ የሚነገርለት የጆርጌ ድልድይና በጣልያን ጦርነት ጊዜ ኢትዮጵያዊያን አርበኞች መሽገውበት እንደነበር የሚነገርለት የዘውዴ ዋሻ ይጠቀሳሉ፡፡ እንዲሁም ከ300 ዓመት በላይ እንዳስቆጠረ የሚነገርለት ቀጥ ብሎ ከወጣ ተራራ አናት ላይ ያረፈው የድንግል ማሪያም ቤተክርስቲያን ይገኝበታል፡፡ በተጨማሪም የመኮድ ወታደራዊ ማሰልጠኛ (ብርሸለቆ ታችበር) እና የፍቅር አስከመቃብር ልብወለድ ታሪክ መጠንሰሻ የሆነችው የማንኩሳ ከተማ በወረዳው ስር ይገኛሉ፡፡

## 2.6. መረዳዳትና መደጋገፍ

የወረዳው ህዝብ በደስታም ሆነ በሀዘን ጊዜ ተደጋግፎና ተረዳድቶ የመኖር ባህል ያለው ህዝብ ነው፡፡ የተለያዩ የመሰባሰቢያ መንገዶችን በመፍጠርም በጋራና በመደጋገፍ ይኖራል፡፡ ማህበር፣ ዕጌ፣ ሰንበቴ የመሳሰሉት ማህበረሰቡ የጋራ ኑሮውን ለማጎልበት የሚፈጥራቸው የጋራ ኑሮ መገለጫዎች ናቸው፡፡ እንዲሁም በሀዘን ጊዜ ‹‹እዝን›› በሚባል የመረዳዳት ስርዓት ሀዘንተኛን ያስተዛዝናሉ፡፡ የሟች ቁርባንንም በመደጋገፍ ያወጣሉ፡፡ በሰርግ ጊዜም አቆልቋይ (ሽመት) በመያዝ አስራጊውን ቤተሰብ በወጭ ያግዛሉ በተጨማሪም በስራ ወቅቶች ማለትም በዘር፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ ጊዜ ወንፈል (ወበራ) በሚባል የመረዳዳት ዘዴ በጋራ በመስራት ያመርታሉ፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## 3. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው ተዛማጅ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎችና የንድፈ ሀሳብ መጽሐፎች ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡

### 3.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ በተለያዩ ተመራማሪዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የቆሎ ተማሪዎችን ህይወት የዳሰሱ የዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች (ዲማጾች) እና ጥናታዊ ጽሑፎች ምልከታ ተካሂዶባቸዋል፡፡

ከቆሎ ተማሪዎች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ጥናቶች ካደረጉት ተመራማሪዎች መካከል አለማየሁ ሞገስ በ1971 እ.ኤ.አ "Traditional church Education" በሚል ርዕስ በአደረገው ጥናት ይጠቀሳል፡፡ ጥናቱም በ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ ለB.th ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ስራ ነው፡፡ አጥኚው ለጥናቱ የሚበጁ መረጃዎችን እንዴት እና ከማን እንደሰበሰበ ባይገልጽም ጥናቱን በframework በማስቀመጥ አካሂዷል፡፡ በጥናቱ እንደተገለፀው ማንኛውም ህብተረሰብ የኑሮ ዘይቤውን የሚያስተላልፍበት የእራሱ የሆነ መንገድ አለው፡፡ ከእነዚህ መንገዶች መካከል እውቀት አንዱ መገለጫ ነው በማለት እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደሚተላለፍ ገልጿል፡፡ የእውቀት መተላለፊያ መንገድ ደግሞ ባህል ይባላል በማለት የኑሮ ዘይቤ፣ እውቀትና ባህል ያላቸውን ቁርኝነት ለማሳየት ችሏል፡፡ በጥናቱ በቀጥታ ባያገለፅም ባህል እውቀትን በውስጡ እንደሚያካትት፣ እውቀት ደግሞ አንዱ የአኗኗር ዘይቤ መገለጫ መሆኑ ተገልጿል፡፡ አለማየሁ በዚህ ጥናቱ ሶስቱን ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የኢትዮጵያ ባህል የሚጠበቀውና እውቀትም ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፈው ቤተክርስቲያን በምትሰጠው ትምህርት አማካይነት መሆኑ በጥናቱ አጽንኦት ተሰጥቶት ቀርቧል፡፡

በዚህ ጥናት የታየው ሌላው ጉልህ ጉዳይ በዘመኑ ብዙም ያልተለመደ ጉዳይን ማንሳቱ ነው፡፡ አጥኚው ጥናቱን ሲያካሂድ ከእሱ በፊት የተካሄዱ ጥናቶችን በመቃወም ነው፡፡ ጥናትን ተቃውሞ ጥናት ማካሄድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተለመደ የመጣ ቢሆንም አለማየሁ ሞገስ ግን ከእሱ በፊት ይህንን ርዕስ ጉዳይ ያነሱ የህብተማሪያም ወርቅነህንና የእምባቆም

ቃለወልድን ስራ በመተቸት ጥናቱን አካሂዷል፡፡ አጥኚው እንደገለፀው ከእሱ በፊት ባህላዊ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናት ያደረጉ ሰዎች ወገንተኝነት ታይቶባቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ባህላዊ ትምህርት ቤቶችን ገለልተኛ በሆነ ስሜት በመመልከት ባህልን ለመጠበቅና ታሪክን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲሁም ያላቸውን ጥቅም ለማሳየት ጥናቱን ማካሄዱን ገልጿል፡፡ በዚህ ረገድ አጥኚው አዲስ ነገር በማምጣት አዲስ የአጠናን ዘዴ ተከትሏል፡፡ ይህ ጥናት በተለይም እውቀት፣ ባህልና የኑሮ ዘይቤ የመሳሰሉ የፎክሎራዊ ገጽታዎችን ከባህላዊ ትምህርት ቤቶች ጋር አዛምዶ በማቅረቡ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ፈጥሯል፡፡

ሌላው ሂሳዊ ምልከታ የተካሄደበት ጥናታዊ ጽሑፍ በላይነህ ደሴ በ1999 ዓ.ም "የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች" በሚል ርዕስ ያደረገው ጥናት ነው፡፡ ይህ ስራ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው፡፡

አጥኚው ለጥናቱ ማስኬጃ ከተጠቀመባቸው ንድፈ ሀሳቦችና ጥቅም ላይ ካዋላቸው መንገዶች አንፃር ከዚህ በፊት ምልከታ ከተካሄደበት ስራ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አጥኚው የሪቻርድ ዶርሰንን ሀሳብ በመያዝ ሀይማኖታዊ ክንውኖች ከፎክሎር ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንደሚኖራቸው ገልጿል፡፡ እነዚህ ባህላዊ ትምህርት ቤቶችም ሪቻርድ ዶርሶን folk religious በሚለው የፎክሎር ዘርፍ ይጠቃለላሉ በማለት ባህላዊ የቅኔ ትምህርት አሰጣጥ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር እንደሚጠቃለል ገልጿል፡፡

አጥኚው የተከተለው የአጠናን ዘዴ ገላጭ (descriptive) ነው፡፡ ምክንያቱም አጥኚው ዋና ዓላማ አድርጎ የተነሳው የቅኔ ትምህርት አሰጣጥን ማሳየትና መግለፅ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የመረጠው የአጠናን ዘዴ ይዞት ከተነሳ ዓላማ አንፃር ትክክለኛና ተገቢ ነው፡፡ ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይትን ተጠቅሟል፡፡ የአንዱን ክፍተት በሌላው በመሙላትና ሶስቱን ዘዴዎች በማማከል መረጃዎችን መሰብሰቡ የጥናቱን ሳይንሳዊነት ያጠናክራል፡፡ ይህ ጥናት ከቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ደረጃዎች መካከል የቅኔ ቤትን ብቻ በመውሰድ በዚህ ትምህርት ቤት የሚሰጠውን የትምህርት አይነትና አሰጣጥ አብራርቶ አቅርቧል፡፡ ‹‹የቅኔ ትምህርት ቤት ህይወት በጎጃም የቅኔ ጉባኤዎች›› የሚለው ንዑስ ርዕስ ከዚህ ስራ ጋር ይበልጥ እንዲመሳሰል አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም የቅኔ ቤት ከቆሎ ተማሪዎች የክፍል ደረጃዎች

መካከል አንዱ በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ጥናት አድራጊ ምልከታ መሰረት በላይነህ መነሻውን በፎክሎር ጽንሰ ሀሳብ እንደመጀመሩ መጠን ወደ ሥርዓተ ትምህርቱ ከማተኮር ይልቅ የቅኔ ትምህርት ቤትን ህይወት በሰፊው ቢመለከት የተሻለ ሥራ ይሆን ነበር፡፡ ይህ ጥናትም ይህንን ክፍተት ይሞላል ተብሎ ይታመናል፡፡

‹‹የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ›› በሚል ርዕስ ሚስጢረ ሰዋሰው በ1974ዓ.ም ያደረገው ጥናት ሌላው ተዛማጅ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ቢሆንም በጥናቱ ከተነሱ ጉዳዮች አንፃር ግን ጥልቅ ምርምር የተካሄደበት ስራ ነው፡፡ ጥናቱ ስለ ግዕዝ ቋንቋ አመጣጥ ታሪካዊ ዳሰሳ ካደረገ በኋላ አባቶች በግዕዝ ቋንቋ ብዙ ፅፈዋል፣ እጅግ ብዙ ተመራምረዋል በማለት ይህንን እውቀት ከየት አመጡት? እንዴትስ ተማሩ? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ ጥናቱን ማካሄዱን ገልጿል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ከመነሻው የምርምር ጥያቄዎቹን በማስቀመጥ የተካሄደ ጥናት ነው ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ እና ዓላማውን ለማሳካት ደግሞ የሊቃውንት አባቶች መፍለቂያ ወደ ሆነው የቆሎ ትምህርት ቤት እንደሄደ በጥናቱ አሳይቷል፡፡ እነዚህን ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች ማጥናት የቀደሙትን ሊቃውንት ህይወት ሊያሳይ እንደሚችል በማመን ባህላዊ ትምህርት ቤቶችን የጥናቱ ትኩረት ማድረጉ ከምርምር ጥያቄዎች አንፃር ትክክለኛና ተገቢ አካሄድ ይመስላል፡፡ በዚህ ጥናት አቅራቢ እይታ መሰረት ምስጢረ ሰዋሰው ያነሳቸው የምርምር ጥያቄዎች ከተመለከታቸው ሁኔታዎች መነሳታቸውና ጥያቄዎችን ለመመለስ ደግሞ የቆሎ ትምህርት ቤቶችን ተተኳሪ ማድረጉ ጥናቱን የተሻለና ውጤታማ አድርጎታል፡፡

አጥኚው የቆሎ ተማሪዎችን የትምህርት አሰጣጥ በዳሰሰበት ምዕራፍ የእነዚህ ትምህርት ቤቶች የትምህርት አሰጣጥ በሽምደዳ ላይ ብቻ የተመሰረተ አይደለም ይልቁንስ ትምህርቱ የተማሪዎችን ነፃ የፈጠራ ችሎታ የሚያጎለብት ስርዓት ነው በማለት ይከራከራል፡፡ በሽምደዳ ላይ የተመሰረተ ነው የሚሉ አጥኚዎችንም ሞግቷል፡፡ ይህ ጥናት እስካሁን የቆሎ ትምህርት ቤቶችን በተለይም የቅኔ ቤትን ከአጠኑ ተመራማሪዎች የሚለየው ሁለት የታወቁ የቅኔ ጉባኤዎችን በመውሰድ በመካከላቸው ያለውን የቋንቋ ትምህርት ፍልስፍና ልዩነት ማሳየቱ ነው፡፡ የጎጃም የቅኔ መምህራን እንደሚሉት የቅኔ ተማሪዎች ቅኔ ሲማሩ የቋንቋውን ሰዋሰው (ህግ) መማር የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ተማሪው በቋንቋ አገባብ ህግ ከታሰረ ህጉን ላለመጣስ ሲል የመፍጠር ችሎታውን ይገድባል፤ ሀሳቡም የተወሰነ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የቅኔ ፈጠራ ችሎታውን ለማጎልበት ስለቅኔው አገባብና ሰዋሰው መጨነቅ የለበትም

የሚል ሲሆን የዋድላ ቅኔ መምህራን ደግሞ የቅኔ ተማሪ ቅኔን ለመማር ሲነሳ የቋንቋውን ህግም አጣምሮ ማወቅ ይጠበቅበታል ይላሉ፡፡ ምክንያቱም ቋንቋ የሀሳብ ማስተላለፊያ ነው፡፡ ስለዚህ ቋንቋው ህግ ከሌላው ሀሳብ አያስተላልፍም፣ ሀሳብ የማያስተላልፍ ቅኔ ደግሞ ሞኑ ቅኔ ሆነ? በማለት እንደሚከራከሩ ሁለቱን የቋንቋ ትምህርት ፍልስፍናዎች በሰፊው መመርመሩ አጥኚው ጥናቱን በጥልቀት እንዳካሄደ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በመነሳትም የቅኔ ትምህርት አሰጣጥ ተመሳሳይ እና የማይለወጥ ነው የሚለውን ሀሳብ ውድቅ ማድረግ ችሏል፡፡ ይህንን ሀሳብ ቀድሞ በማንሳቱም ጥናቱ የተሻለ ስራ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምስጢረ በማጠቃለያው ባህላዊ ትምህርት ቤቶች ኋላ ቀርና የማይለወጡ ሳይሆኑ ብዙ የህይወት ልምዶች የሚገኙባቸው የእውቀት ማዕከላት መሆናቸውን በአፅንኦት ገልጿል፡፡፡ በአጠቃላይ ይህ ስራ የተማሪዎችን ህይወትም በጥልቀት ለመመርመር ባደረገው ጥረት ከዚህ ስራ ጋር ሲመሳሰል ማህበረሰቡ ለተማሪዎች ያለውን አመለካከት ባለመግለፁ እና በስነቃሎቻቸው ህይወታቸው እንዴት እንደሚገለፅ ባለማየቱ ከዚህ ጥናት ጋር እንዲለያይ አድርጎታል፡፡

አምሀ እየሱስ አሰፋ በ1994ዓ.ም ‹‹መንፈሳዊ ትምህርት ቤት (ቄስ ትምህርት ቤት) በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ ያደረገው ጥናት ምልከታ ተካሂዶበታል፡፡ ጥናቱ በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ስራ ነው፡፡ አጥኚው ገና ከመነሻው በቄስ ትምህርት ቤቶች ላይ እና በሚያነሷቸው ጉዳዮች ላይ የቀረበ ጥናት ባለማግኘቱ ይህንን ጥናት ለማካሄድ መነሳቱን ገልጿል፡፡ አጥኚው የሙዚቃ ትምህርት ቤት ተማሪ እንደመሆኑ መጠን ትኩረት ያደረገው ከቄስ ትምህርት ቤት ደረጃዎች መካከል በ "ዜማ ቤት" ላይ ነው፡፡ ጥናቱ በዜማ ቤት ላይ ቢያተኩርም በመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ጉድለት ምክንያት ስራውን በትክክል መግለፅ አልቻለም፡፡ ገና ከርዕሱ ‹‹ቄስ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ›› ብሎ ርዕሱን ሰፊ ቢያደርገውም የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ግን ከስራው ጋር አብረው የማይሄዱ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ የተካሄደው በእድሜ ገፋ ያሉ ቄሶችን ብቻ ቃለ መጠይቅ በማድረግ መሆኑ በጥናቱ ተገልጿልና ነው፡፡

አጥኚው የዜማ ትምህርት አሰጣጥን ለማንሳት በኢትዮጵያ የቄስ ትምህርት ቤት እንዴት እና መቼ እንደተጀመረ ታሪካዊ ዳሰሳ አድርጓል፡፡ በጥናቱ እንደተገለፀው እነዚህ ትምህርት ቤቶች መቼ እንደተጀመሩ በውል ማወቅ ባይቻልም ለዘመናዊ ትምህርት መነሻ መሆናቸው

ግን አያጠያይቅም በማለት የቄስ ትምህርት ቤቶች ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት ጥረት አድርጓል፡፡ ትምህርት ቤቶች በቤተክርስቲያን ስር መታቀፋቸውና መምህራኑ በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸው ከፍተኛ ተቀባይነት ብቸኛ የትምህርት ማዕከል ሆነው ለብዙ አመታት እንዲኖሩ አስችሏቸዋል በማለት በጥናቱ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ በመረጃ ከማስደገፍ ይልቅ የግል አስተያየት በሚመስል ሁኔታ አቅርቦታል፡፡ በጥናቱ እንደተገለፀው ዜማ ቤት መሰረቱ ያሬዳዊ ዜማ መሆኑን ከመግለፅ አልፎ ቁርኝታቸውን በመረጃ አስደግፎ ለማሳየት ምንም የተደረገ ጥረት በጥናቱ አልታየም፡፡ ጥናቱ በመረጃ አሰባሰብ በኩል ትልቅ ክፍተት ታይቶበታል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋርም ከርዕሱ በዘለለ ብዙም ተመሳሳይነት የላቸውም፡፡

በመጨረሻ ቅኝት የተደረገበት ስራ ገዛኸኝ ጌታቸው «የአብነት ትምህርት ቤቶች ለዘመናዊ ትምህርት እድገትና ለሀገሪቱ አስተዳደር ያደረጉት አስተዋፅኦ» (አመተ ምህረት ያልተጠቀሰ) በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡ ጥናቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማህበረ ቅዱሳን ባዘጋጀው ሀገር አቀፍ አውደ ጥናት ላይ የቀረበ ስራ ነው፡፡ ይህ ጥናት የምርምር ጥያቄዎችን በማንሳት በጥናቱ መልስ ለማግኘት ሞክሯል፡፡ በጥናቱ እንደተገለፀው በቤተክርስቲያን ትምህርት የሚሰጥባቸው ማዕከላት በተለምዶ የቆሎ ትምህርት ቤቶች ይባላሉ፡፡ የእነዚህ ትምህርት ቤቶች ዓላማ የቤተክርስቲያን ሊቃውንትን ማፍራት ቢሆንም አያሌ ሀገራዊ ተግባራትን ለኢትዮጵያ ሲያበረክቱ መቆየታቸውን መረጃ እያጣቀሰ ማሳየት ችሏል፡፡ ሀገራችን ታሪኳ ተመዝግቦና ተጠብቆ የኖረው ከቆሎ ትምህርት ቤቶች ተምረው ችሏል፡፡ ሀገራችን ህግ አውጭም ሆኑ ህግ በሚወጡ ተማሪዎች እንደነበር ማሳየት ችሏል፡፡ በሀገራችን ህግ አውጭም ሆኑ ህግ አስከባሪ አካላት የሚወጡት ከእነዚህ የትምህርት ማዕከላት እንደነበር በአፅንኦት ገልጿል፡፡

አጥኚው ከዚህ በፊት በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናት ያካሄዱ ተመራማሪዎች የትምህርት ቤቶቹን ጠንካራ ጎን ከመመልከት ይልቅ ለሀገራችን ድህነትና ኋላቀርነት ተጠያቂ ሲያደርጓቸው መቆየታቸውን አንስቷል፡፡ ይህም ሳይንሳዊ ምርምር ሳያደርጉ ከግል ስሜት የመነጨ ሃሳብ ነው በማለት አጥኚዎችን ይነቅፋል፡፡ ይልቁንስ እነዚህን ትምህርት ቤቶች የታሪክ፣ የባህልና የፖለቲካ ተመራማሪዎች በጥልቀትና በገለልተኝነት ስሜት ሊመረምሯቸው ይገባል በማለት የግል አስተያየቱን አስቀምጧል፡፡ አጥኚው በማጠቃለያው እንደገለፀው ሀገር በቀል እውቀት ለአንድ ሀገር እድገት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ የቆሎ ትምህርት ቤቶችም ሲያደርጉ የኖሩት ይህንን ነው በማለት

የነበራቸውን ሀገራዊ ፋይዳ አንፀባርቋል፡፡ አያይዞም የሙዚቃ፣ የስነ-ፅሁፍ፣ የስነ ልቦናና የፍልስፍና ትምህርት ክፍሎች ከነዚህ ትምህርት ቤቶች ጋር የሚገናኙበት ሁኔታ ስላለ ትኩረት ሰጥተው ቢመረምሯቸው ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ገልጿል፡፡ የቆሎ ትምህርት ቤቶች የብዙ ነገር መገኛ መሆናቸውንም ለማንፀባረቅ ሞክሯል፡፡ ከዚህ አኳያ ጥናቱ ይዞት ከተነሳ ርዕስና የምርምር ጥያቄ አንፃር ግቡን መቷል ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት አድራጊ ቅኝት የተደረገባቸው ስራዎች ለተለያየ ዓላማ የተደረጉ ጥናቶች ቢሆኑም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ከቆሎ ተማሪዎች ጋር የሚገናኙ ጉዳዮችን ስለሚያነሱ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ ጥናቶቹ ከስነ ትምህርት፣ ከታሪክና ከሙዚቃ ጋር በተያያዘ የተጠኑ ቢሆኑም ሁሉም የቆሎ ትምህርት ቤቶች የብዙ ነገር መገኛ መሆናቸውን መመስከር ችለዋል፡፡ እያንዳንዱ ስራ የራሱ ደካማና ጠንካራ ጎን እንዳለ ሆኖ የተማሪዎችን ህይወት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በማንሳታቸው ከዚህ ጥናት ጋር የቀረበ ተመሳሳይነት ፈጥረዋል፡፡ በአንፃሩ ሁሉም የተማሪዎችን ህይወት ሲያነሱ ስነቃሎቻቸውን ሳይመለከቱት በመቅረታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያሉ፡፡

### 3.2. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስለ ቆሎ ተማሪዎች ስያሜና ህይወት እንዲሁም ስለፎክሎር እና ተዛማጅ ፅንሰ ሀሳቦች ከተለያዩ ምንጮች የተገኙ የንድፍ ሀሳብ ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡

#### 3.2.1 የቆሎ ተማሪዎች ስያሜ

በቤተክርስቲያን ስር ተጠቃለው የሚማሩ ተማሪዎች በተለያዩ ስያሜዎች ይጠራሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ‹‹የአብነት ተማሪዎች››፣ ‹‹የቂስ ተማሪዎች›› እና ‹‹የቆሎ ተማሪዎች›› የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ ነገር ግን ለዚህ ጥናት ‹‹የቆሎ ተማሪዎች›› የሚለው ስያሜ ተመራጭ ሆኗል፡፡ ሁለቱ ስያሜዎች ያልተመረጡበትን ምክንያት ስንመለከት "የአብነት ተማሪዎች" የሚለው መጠሪያ በዚህ ጥናት ያልተመረጠበት ምክንያት የዚህ ጥናት ተተኳሪ ተማሪዎች በሚገኙበት አካባቢ ያልተለመደ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ መጠሪያ ከቅርብ ጊዜ በተለይም ‹‹ማህበረ ቅዱሳን›› የሚባለው ሀይማኖታዊ ድርጅት የሚጠቀምበት መጠሪያ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው መዝገበ ቃላት ‹‹አብነት›› የሚለውን ቃል (1) ምሳሌ፣ አርአያ ብሎ ሲተረጉመው (2) የጠለቀ ትምህርት ያለው እና እውቅ መምህር" በማለት ይተረጉመዋል፡፡ ይህ ስያሜ አንድም የትምህርት መጀመሪያ

መሆናቸውን ለመጠቆምና በሌላ በኩል በእውቀት የበለፀጉ መሆናቸውን ለመጠቆም የተሰጠ ስያሜ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን ይህ ስያሜ የቅርብ ጊዜ በመሆኑ እና በተለይም ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ የተለመደ ስላልሆነ ለተማሪዎች መጠሪያነት አልዋለም። በሌላ በኩል «የቄስ ተማሪዎች» የሚለውን ስያሜ ስንመለከት ስያሜውን ያገኙት ከትምህርት በኋላ ከሚሰማሩበት ሙያ በአንዱ ላይ ብቻ በመመስረት ነው። ይህ ስያሜ የተማሪዎችን ማንነት ሙሉ በሙሉ አይገልፅም ምክንያቱም «ቄስ» የሚለው ቃል «ቀሰ» አገለገለ ከሚለው የግዕዝ ቋንቋ የመጣ መሆኑን ኪዳነማርያም ይገልፃል (1980፡81) ስለዚህ ይህ ስያሜ ተማሪዎች ከትምህርት በኋላ በሚሰጡት አገልግሎት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ የተማሪዎች ጥቅል መጠሪያ ሊሆን አልቻለም።

«የቆሎ ተማሪዎች» የሚለው መጠሪያ በሁለት ምክንያቶች በዚህ ጥናት ለተማሪዎች መጠሪያ ሆኖ ተመርጧል። በመጀመሪያ ይህ ጥናት የፎክሎር ጥናት እንደመሆኑ መጠን አካባቢያዊ ስያሜ ትልቅ ድርሻ ይሰጠዋል። ለጥናት በተመረጠው አካባቢ ከሁለቱ ስያሜዎች ይልቅ "የቆሎ ተማሪዎች" የሚለው መጠሪያ በሰፊው ጥቅም ላይ ይውላል። እንዲሁም ተማሪዎች እራሳቸውን የሚጠሩበት መጠሪያ ስለሆነ ሊመረጥ ችሏል። በሌላ በኩል ስያሜው የተማሪዎችን ትክክለኛ ህይወት የሚያሳይ በመሆኑ ነው። በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት መሰረት «የቆሎ ተማሪ ማለት ከየመንደሩ የሚያገኘውን ቁራሽ እንጀራ እንዲሁም ጥራጥሬውን በቆሎ መልክ እያዘጋጀ በመመገብ እንደ ንባብ፣ ዜማ፣ ቅኔ...ወዘተ ያሉትን የትምህርት አይነቶች የሚቀጽል የቤተክህነት ተማሪ ነው»። (1993፡203) በዚህ ስያሜ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎች ጥቅል መጠሪያ መሆኑ እና ስያሜውም የትምህርት ቤት ህይወታቸውን የሚገልፅ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ኪዳነማሪያም ጌታሁን «ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ» በሚለው መጽሐፉ የቆሎ ተማሪ ማለት ጥሬ ቆርጥሞ፣ ውሃ ጠጥቶ በችግርና በረሃብ የሚማር መሆኑን ገልጿል። (1980፡6) ከላይ የተነሱት ሁለቱም ስያሜዎች እንደገለፁት የቆሎ ተማሪ የሚለው መጠሪያ ህይወታቸውን መሰረት አድርጎ የተሰጠ መጠሪያ ነው። በነዚህ ምክንያቶችም ስያሜው ለዚህ ጥናት የተማሪዎች ጥቅል መጠሪያ ስያሜ በመሆን አገልግሏል።

### 3.2.2 የቆሎ ተማሪዎች አኗኗር

የቆሎ ተማሪዎች የእራሳቸው የሆነ የአኗኗር ስርአት አላቸው፡፡ ሀብተማርያም ወርቅነህ ‹‹ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት›› በሚለው መጽሐፉ በሀገራችን የሚገኙ የቆሎ ተማሪዎች ህይወት የእራሱ የሆነ ወግና ስርዓት እንዳለው ገልጿል (1963፡288)። ኑሯቸውንም የሚመሩት በቤተክርስቲያን አቅራቢያና በመምህራቸው ቤት ዙሪያ በህብረት በሚቀልሷቸው ጎጆዎች ውስጥ ነው፡፡ የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው የሚያልፉባቸው አራት ዋና ዋና የትምህርት ደረጃዎች አሉ፡፡ እነሱም ንባብ ቤት፣ ዜማ ቤት፣ ቅኔ ቤትና መጻሕፍት ቤት ናቸው፡፡ (እምባቆም፣ 1970፡3፣ ሀብተማሪያም 1963፡39፣ Pankhurst; 1966, 32-33) እያንዳንዳቸው ደረጃዎች በውስጣቸው ብዙ ንዑሳን ክፍሎች ቢኖሯቸውም አራቱ ደረጃዎች ግን ጎልተው የሚታወቁት ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ትምህርት የተለያየ መልክ ስላለው በተለይም የትምህርት አሰጣጡ እራሱን ችሎ ሊጠና እንደሚችል ሀብተማሪያም ይገልጻል(1963፡15)።

በገጠሯ ኢትዮጵያ በእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ የእራሱ ቤተክርስቲያንና ትምህርት ቤት አለው፡፡ ትምህርት ቤቶቹም ብዙውን ጊዜ በቤተክርስቲያን አቅራቢ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር የሪቻርድ ፓንክረስትን ሀሳብ ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል፡፡

> *In the Christian part of abysiniya there is a church in almost every village, every church has its school which is an honored institution. Church schools nearly always in the precincts the church generally with in the outer wall of the church green. (1966, 30)*

በየቤተክርስቲያኑ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የቆሎ ተማሪዎች እንደየደረጃቸው ገብተው ይማራሉ፡፡ የተማሪዎች መማሪያ ቦታ ከቤተክርስቲያን አለመራቁ ትምህርት ቤቶቹ በቤተክርስቲያን ሀላፊነት እንደሚመሩ ይጠቁማል፡፡ ለትምህርት የሚነሱ የቆሎ ተማሪዎችም ከቤተሰቦቻቸው ርቀው በመሄድ እና የእራሳቸውን ጎጆ በመቀለስ ለምነው በሚያገኙት ቁራሽ እንጀራ የእራሳቸውን ህይወት መኖር ይጀምራሉ፡፡

ተማሪዎች ሀይማኖታዊ ትምህርትን ዋና ዓላማ አድርገው ቢነሱም በትምህርት ቤት ቆይታቸው እንደ ታሪክ፣ ግጥም፣ ሙዚቃ ፍልስፍናና መድሃኒት ቅመማ ወዘተ የመሳሰሉትን የትምህርት አይነቶች ሁሉ እንደሚማሩ ሪቻርድ ፓንክረስት ያስረዳል

(Pankhurst; 1966,28) ከሪቻርድ ፓንክረስት መረዳት እንደሚቻለው ዛሬ ላይ የዘመናዊ ትምህርት ትኩረት የሆኑት የትምህርት ዘርፎች ቀደም ብሎም በኢትዮጵያ የቆሎ ትምህርት ቤቶች ይሰጡ ነበር፡፡ በተጨማሪም እነዚህ ትምህርት ቤቶች በሀገራችን ለሚሰጠው ዘመናዊ ትምህርት መሰረት መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እነዚህን ተማሪዎች የሚያስተምሯቸው መምህራን በእውቀት የበለፀጉ እና በአውሮፓ "ፕሮፌሰር" ከሚባሉት ሙህራን ጋር እንደሚስተካከሉ ሪቻርድ ፓንክረስት Lady Harbert'ን በመጥቀስ የመምህራኖቹን አዋቂነት ይገልጻል (1966,29)። የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ህወታቸው በብዙ የእውቀት መስኮች የበለጸጉ ቢሆኑም የትምህርት ቤት ህይወታቸው ግን በችግርና በስቃይ የተሞላ ነው፡፡ ችግራቸው የሚጀመረውም ገና ከመነሻው ቤተሰቦቻቸውን ጥለው በመሰደድ በሚያደርጉት መስዋእትነት ነው፡፡ ይህንን የተማሪዎችን ችግር ሀብተማሪያም እንደገለፀው በኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ ትምህርት ይወደድ ነበር፡፡ ህዝቡም በህብረት ትምህርት ቤት ይሰራና መምህራን ይቀጥር ነበር፡፡ ነገር ግን በተማሪዎች ላይ ብዙ ችግር ይደርስባቸው ነበር (1963፡29)።

የቆሎ ተማሪዎች ለትምህርት ከቤተሰቦቻቸው ርቀው ሲሰደዱ ምንም ተስፋ የሚያደርጉት ነገር የለም፡፡ ከቤተሰቦቻቸው ፈቃድ ስለማያገኙ ቤተሰቦቻቸውን አማክረው ስንቅ ከማዘጋጀት ይልቅ በድብቅ አስቸጋሪውን ህይወት ይጀምራሉ፡፡ ሪቻርድ ፓንክረስት እንደሚለው እውቀትን ተጠምቶ የሚሰደድ ተማሪ ብቸኛ ሀብቱ የቁራሽ እንጀራ መለመኛ የምትሆነው "አከፋዳው" ብቻ ናት፡፡ ህይወቱንም በልመና በሚያገኘው እንጀራ እንደሚመራ ተስፋ በማድረግ ብቻ ነው ቤተሰቦቹን ጥሎ የሚሰደደው (Pankhurst; 1966፡29)። የቆሎ ተማሪዎች እውቀትን ፍለጋ ከቤተሰቦቻቸው ርቀው ከተሰደዱ በኋላ በየትምህርት ቤቱ ሲገናኙ ኑሮአቸው በመተሳሰብ ላይ የተመረተ የጋርዮሽ ኑሮ ነው፡፡ እምበቆም ቃለወልድ "Traditional Ethiopian Church School" በሚለው መጽሐፉ ተማሪዎች በጋራ ጎጆ ይቀልሳሉ፣ በጋራ ይሰራሉ፣ በጋራ ይማራሉ እንዲሁም በጋራ ይመገባሉ በማለት ማህበራዊ ህይወታቸው የጠነከረ መሆኑን ያስረዳል (እምባቆም፣ 1970፡16-19) ህይወታቸው በጋርዮሽ ላይ የተመሰረተ መሆኑ እነዚህ ተማሪዎች እንደ አንድ ቡድን ተቆጥረው ጥቅል ህይወታቸው ይጠናል፡፡

### 3.2.3. የፎክሎር ምንነትና ተዛማጅ ጽንሰ ሀሳቦች

ፎክሎር የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ Willam John Thoms በ1846 እ.ኤ.አ ከተጠቀመበት በኋላ የተለያዩ ምሁራን እንደየዘመኑ የእውቀት ደረጃ የተለያየ ብያኔ ሲሰጡት ቆይተዋል፡፡ ሁሉም ስለፎክሎር ብያኔ የሰጡ ሙሁራን ፎክሎር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ለብያኔ አስቸጋሪ መሆኑን ሳይጠቁሙ አላለፉም፡፡ ጽንስ ሀሳቡን በቃል መሰየም ብቻም ሳይሆን በውስጡ የሚያጠቃልላቸው ነገሮች ብዛት ጉዳዩን የበለጠ አወሳስቦታል፡፡ በተለይም ፎክሎር አንድ የጥናት ዘርፍ መሆኑ እና በተጨማሪም ዘርፉ የሚያጠናቸው ጉዳዮች ጥቅል መጠሪያ መሆኑ ቁርጥ ያለ ብያኔ እንዳይሰጠው አድርጓል (Martha and Martine; 2005,1)፡፡በሌላ በኩል Ben-Amos እንደሚለው ፎክሎር አንድ የእውቀት ዘርፍ መሆኑ፣የእውቀት ማስተላለፊያ መንገድ መሆኑ እና ፎክሎር በራሱ እንደአንድ የጥበብ ዘርፍ መቆጠሩ ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት እንዳስቸገረ ገልጿል። አያይዞም እነዚህ ጉዳዮች በቀጥታ ከ ባህል ጋር ስለሚያያዙ ፎክሎርና ባህልቁርኝት እንዳላቸው ገልጿል (Ben-Amos; 1971,4)። ነገር ግን በየጊዜው የተነሱ ተመራማሪዎች የእየራሳቸውን ስያሜ አስቀምጠው ቢያልፉም አንድና ወጥ የሆነ ስያሜ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በሌላ በኩል ፎክሎር ምንም ይበል ምንም የሰው ልጆችን የእለት ከእለት ህይወት ስለሚመለከት ከሰው ልጆች እድገትና ስልጣኔ ጋር አብሮ እየተለወጠ እንደመጣ መረዳት ይቻላል፡፡ Martha and Martine ፎክሎር ሁልጊዜም በለውጥ ሂደት ያለ መሆኑንና ብያኔውም በየጊዜው እንደሚለዋወጥ ይገልጻሉ፡፡ "Folklorists is continue to define and redefine the term frequently. Because folklore itself is changes and so does our understanding at it" (2005,11)

ከላይ እንደተጠቀሰው አንድም ዘርፉ በራሱ በለውጥ ሂደት ውስጥ መሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ተማራማሪዎች ስለ ዘርፉ ያላቸው አተያይ እየሰፋ እና እየተለወጠ መሄዱ ተደማምረው ቁርጥ ያለ ብያኔ ለመስጠት አስቸጋሪ እንዳደረገት መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ዛሬ ላይ የምንጠቀምበት የፎክሎር ብያኔም ነገ ሊቀየር እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ ለብያኔ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ይመስላል ስለፎክሎር የተሰጡት አብዛኞቹ ብያኔዎች ፎክሎር ማለት ይህ ነው ብሎ ከመግለፅ ይልቅ በውስጡ የሚይዛቸውን ነገሮች ብቻ በመዘርዘር ሲያልፉ ይታያል (ፈቃደ፣ 1991፣2) ነገር ግን አላንዳንደስ (Alan Dundus) ፎክሎር በውስጡ ያጠቃልላቸዋል ብሎ ከዘረዘራቸው መረዳት እንደሚቻለው ፎክሎር አብዛኛውን የሰውን ልጅ የእለት ከእለት ህይወት ገጠመኝ እንደሚያካትት መረዳት ይቻላል፡፡

በቅርብ ጊዜ የተሰጡትን የፎክሎር ብያኔዎች ብንመለከት ፎክሎር ትምህርት ቤት ገብተን የማንማረው ነገር ግን መደበኛ ባልሆነ መልኩ ስለ እራሳችን፣ ከሰዎች ጋር ስላለን ግንኙነት፣ ስለ እምነታችን፣ ስለ ባህላችን በአጠቃላይ ስለ አለም ያለንን ግንዛቤ የምንገልጽበት የህይወታችን ክፍል ነው(Martha and Martine; 2005,12)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Robert A.Georges እና Micheal own Jhonas ፎክሎር ይህ ነው ብለን ቁርጥ ያለ ብያኔ ከመስጠት ይልቅ በማህበራዊና ባህላዊ አውድ እያስገባን ከሚሰጠው አገልግሎት (function) በመነሳት ምንነቱን ማወቅ ይቻላል የሚል ሀሳብ ያነሳሉ (1995,189)። በሌላ በኩል ፈቃደ አዘዘ ዶርሰንን በመጥቀስ ፎክሎርን በአራት ዋና ዋና ዘርፎች ከፍሎ እያንዳንዳቸው በውስጣቸው የሚይዟቸውን ጉዳዮች በመዘርዘር አቅርቧል፡፡ ቃላዊ ፎክሎር (oral folklore)፣ ሀገረሰባዊ ልማድ (Social folk custom) ቁሳዊ ባህል (material culture) እና ሀገረሰባዊ ጥበብ (folk art) በማለት የዶርሰንን አከፋፈል ፈቃደ ሀገራዊ ስያሜ ሰጥቷቸዋል(1991፣10) በሌላ በኩል Martha እና Martine ፎክሎርን በዘርፍ (gener) መከፋፈል ለአጠናን እንደሚያመች ገልጸው ዶርሰን በአራት ዘርፍ መድቧቸው የነበሩትን ወደ ሶስት አጠቃልለዋቸዋል፡፡ ልማድ፣ ስነቃልና ቁሳዊ ባህል በማለት አቅርበዋቸዋል (2005,12) Marthaእና Martine ፎክሎርን በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች ይመድቡት እንጂ ፎክሎርን በ gener መከፋፈል በፎክሎር ጥናት ጊዜ ተቀዳሚ ተግባር እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ስለፎክሎር ሀሳብ ለመያዝና በተለይም አንድን የፎክሎር ዘርፍ ነጥሎ ለሚያጠና ተመራማሪ መነሻ ሊሆን ይችላል እንጂ ፎክሎርን በዘርፍ መመደብ ብቸኛው የፎክሎር ማጥኛ መንገድ እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ እነዚህን የሚጋሩ፣ የሚመስሉ ሀሳቦች የሚያብራራውን ሀሳብ እንመልከት፡፡

> *While the use of gener lable is still a very handy way for us to talk about folklore, we want to introduce here a concept that goes beyond gener classification, and instead look at folklore as acomplex, interconnected act of communication. (Martha and Martine; 2005,19)*

ከላይ በተነሳው ሀሳብ መሰረት ፎክሎርን በ gener መከፋፈል የፎክሎር ጥናት ተቀዳሚ ተግባር አይደለም ሲባል በ gener ከፋፍሎ ማጥናት ያለውን ጥቅም ወደ ጎን በማለት እንዳልሆነ ተገልጿል፡፡

ፎክሎር ውስብስብ የሰው ልጆች ህይወት መገለጫና መግባቢያ መንገድ በመሆኑ ድንበር እያበጁ መከፋፈሉ በፎክሎር ጥናት አይመረጥም፡፡ ከዚህ ይልቅ በሰዎች ለሰዎች ግንኙነት

ውስጥ እያስገቡ መተርጎሙና መረዳቱ የተሻለ ይሆናል፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው ፎክሎር የሰዎች መግባቢያ መንገድ ከሆነ የግድ እርስ በእርሳቸው ግንኙነት የሚፈጥሩ የህብተተሰብ ፍክሎች ያስፈልጋሉ ወደ ሚል ድምዳሜ ይወስደናል፡፡ ፎክሎር የሰው ልጆችን የእለት ከእለት ህይወት ስለሚመለከት የሚጋሩት የጋራ መገለጫ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ይፈጥራሉ፡፡ Martha እና Martine alan Dndesን በመጥቀስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የጋራችን የሚሉት ነገር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችም እራሳቸውን ችለው ሊጠኑ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ (2005፣35) በሌላ በኩል Georges እና Jones እንደሚሉት ፎክሎር በሶስት አይነት መንገድ ሊጠና እንደሚችልና ከነዚህ መንገዶች መካከል ፎክሎርን የአንድ ቡድን (folk group) መገለጫ አድርጎ ማጥናት እንደሚቻል ይገልጻሉ፡፡ (1995,22) ስለዚህ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆኑት የቆሎ ተማሪዎች እንደ አንድ የህብረተሰብ ክፍል (group) ተቆጥረው የእራሳችን የሚሉትን ፎክሎር ማጥናት ይቻላል፡፡

በፎክሎር ጥናት ቡድን ( group) የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ለአንድ የፎክሎር ተመራማሪ ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ከላይ ከተሰጠው ብያኔ በመነሳት ፎክሎር ትርጉም ሊኖረው የሚችለው የግድ ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች ህይወት ውስጥ ያለው ሚና ሲመረመር በመሆኑ ነው፡፡ “folklore is not thought as existing without or a part from a structured group (Ben-Amos; 1971, 14)፡፡Ben- Amos እንደገለጸው ፎክሎርን ከቡድን ነጥሎ ማየት አይቻልም ምክንያትም አንድ የህብረተሰብ ክፍል የእራሱን ህይወት የሚገልጽበትና የሚታወቅበት የጋራ ጉዳይ ይኖረዋል፡፡ ይህ የጋራ ጉዳይ፣ የእርስ በእርስ ግንኙነት፣ ስለራሳቸው ብሎም ስለ ሌላው ማህበረሰብ ያላቸው አመለካከት የሚገልጽበት ደግሞ ፎክሎር ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ የበለጠ ለማብራራት የ Georges እና Jones ን ሀሳብ እንመልከት፡፡

> *"Folklore as an aspect and manifestation of the culture to single social group. Implicit in the studies surveyed are the assumptions (1) that the group under consideration has a culture; (2) that folklore is an integral and essential part of the culture of that group; and (3) that the culture (include the folklore) of any given group can be discerned, described and analyzed independently of the culture of other groups (1995, 193 አጽንኦት የኔ)*

ከላይ የተነሳው ሀሳብ አንድ የህብረተሰብ ክፍል የእራሱ ፎክሎር ይጠናል ሲባል ታሳቢ የሚደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮችን አንስቷል፡፡ ፎክሎር የአንድን ነጠላ ቡድን ህይወት ያሳያል

ብለን ስንነሳ የጋራ መገለጫ የሆነ ባህል አላቸው ከሚል ሀሳብ ነው፡፡ የጋራ የሆነ የሚታወቁበት ባህል ከሌላቸው እንደ አንድ ነጠላ ቡድን ሊቆጠሩ አይችሉም ማለት ነው፡፡ ሌላውና ትልቁ ጉዳይ አንድ ነጠላ ቡድን የባህሉ መገለጫ የሆነው ፎክሎር ይጠናል ሲባል የቡድኑ ባህል ከሌሎች የተለየ ነገር ሲኖረው (ተለይቶ የሚታወቅበት ሲሆን) እና ያ ባህል እንዲህ ነው ተብሎ የሚገለጽና የሚተረጉም ሲሆን ነው፡፡ በአጠቃላይ አንድን ቡድን እራሱን ችሎ ይጠና ዘንድ ከሌሎች የሚለይበት መገለጫ ሊኖረው ይገባል ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳል፡፡ የቆሎ ተማሪዎችም እንደ አንድ የህብረተሰብ ክፍል ተቆጥረው ለጥናት ሲመረጡ ከላይ በተነሳው ሀሳብ መነሻነት ነው፡፡

በሌላ በኩል አንድ ቡድን ከላይ የተቀመጡትን ጉዳዮች አሟልቷል ተብሎ ሲጠና ያ ቡድን እራሱን እንዴት ከሌላው ማህበረሰብ እንደሚለይና ማንነቱን እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚገልጽ መረዳት ይቻላል፡፡ በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚመሰረቱ ቡድኖች እራሳቸውን ከሌሎች የሚለዩበት ድንበር ያበጃሉ፡፡ ይህ እራሳቸውን የሚገልጹበትና ከሌሎች የሚለዩበት ዘዴ ደግሞ በእለት ከእለት ህይወታቸው ይገለጻል፡፡ ህይወታቸው የሚታወቀውና የሚጠናው ደግሞ በፎክሎር ነው (Georges and Jones; 2005, 225)፡፡ ስለዚህ በአንድ ቡድን (group) ላይ የሚካሄድ ጥናት የዚያን ቡድን ማንነት ያሳያል ማለት ይቻላል፡፡ Georges እና Jones ከላይ ባስቀመጡት ሀሳብ መሰረት አንድ ቡድን (group) እራሱን ችሎ ይጠናል ቢባልም ቡድን ለብቻው በተለየ አለም እስካልተገኘ ድረስ በዙሪያው ካሉ ሰዎች ወይም ቡድኖች ጋር ግንኙነት መፍጠሩ አይቀርም፡፡

ይህንን ሀሳብ የበለጠ ለማጠናከር የMarthaና Martineን ሀሳብ ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል፡፡ “group identity depends not only shared communication within the group, but also an interaction with other groups” (2005, 36):: በዚህ ሀሳብ መሰረት ሁለት ነገሮችን ማንሳት ይቻላል፡፡ አንድም የአንድን ቡድን ማንነት ለማወቅ በቡድኑ አባላት መካከል (intra group) ያለውን ግንኙነት መመርመር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች (inter group) ጋር ያላቸውን ማስተጋብርና ግንኙነት ማወቅ ናቸው፡፡ አንድ ቡድን እራሱን ችሎ ይጠናል ቢባልም እንደ አንድ ቡድን ለማጥናት ግን ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ማየቱ ጥናቱን የበለጠ ያጠናክረዋል፡፡ በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የቆሎ ተማሪዎች በአንድ ቡድን ስር ተጠቃለው የሚኖሩ ቢሆኑም የእነሱን ማንነት ለማጥናት ግን ከእርስ በእርስ ግንኙነታቸው ባለፈ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ማጥናት ማንነታቸውን ያሳውቃል፡፡

ከዚህ በመነሳት የአንድን ቡድን ማንነት ሳይመረመሩ የዚያን ቡድን ፎክሎር መግለጽ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም አንድን ቡድን የሚያጠና ፎክሎረኛ በቡድን ውስጥ የሚከናወኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ሁሉ ለተመረጠው ቡድን ምን ትርጉም እንደሚሰጡ መመርመር ይገባዋልና ነው፡፡ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው አንድ ቡድን መፈጠሩ ብቻ ሳይሆን ከቡድኑ መፈጠር ጋር አብረው የሚመጡ ጉዳዮች ማለትም የጋራ እምነት፣ የጋራ ክንውኖች ወዘተ በጥልቅ መተርጎም ይኖርባቸዋል፡፡ Marthaና Martine እንደሚሉት አንድ ፎክሎረኛ በሚያጠናው ቡድን ውስጥ የሚገኙ ቃላዊ፣ ልማዳዊና፣ ቁሳዊ ነገሮችን የቡድኑ አባላት እንዴትና ለምን እንደሚጠቀሙባቸው ማጤን ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም እነዚህን ጉዳዮች እንዴት እንደሚጋሯቸው ማሳየት መቻል ይኖርበታል (2005,174)

በአንድ የህብረተሰብ ክፍል ስር የሚጠቃለሉ ግለሰቦች በጋራ የሚታወቁበትና እራሳቸውን የሚገልጹበት ጉዳይ እንዳላቸው ተገልጿል፡፡ ይህ የቡድኑ አባላት የጋራችን ብለው የሚያደርጉትና የሚግባቡበት ጉዳይ ደግሞ እምነት የጋራቸው እምነት ይሆናል ፡፡ በፎክሎር ጥናት ውስጥ እምነት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሁለት ነገሮችን ይይዛል፡፡ አንድም የምናምነው ነገር ሲሆን የምናምንበት መንገድ ደግሞ ሌላው ጉዳይ ነው (Martha and Martin; 2005,57) ከዚሁ ጋር አያይዘው ሀይማኖታዊ ቡድኖችን (religious groups) ማጥናት በውስጡ ብዙ እምነቶችን ማጥናት ነው ይላሉ፡፡ የቆሎ ተማሪዎችም በሀይማኖታዊ ተቋም ስር የታቀፉ ሀይማኖታዊ ቡድኖች ስለሆኑ ብዙ የእምነት መገለጫዎች ይኖሯቸዋል፡፡ Martha እና Martine Don yoderን በመጥቀስ ሀይማኖታዊ እምት (religious belife) እና ሀገረሰባዊ እምነት (folk belief) ተነጣጥለው የማይታዩ የእምነት ስርአቶች መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ "religious belief and folk belif are part at a unified organic system at belief" all of which occur in particular context" (2005፣59)፡፡ በሌላ በኩል ፈቃደ አዘዘ "የስነ ቃል መምሪያ" በሚለው መጽሐፉ የሁለቱን እምነቶች ግንኙነት የገለጸበት መንገድ ከላይ ከተነሳው ሀሳብ ጋር የሚዛመድ ነው፡፡

> *...ለምሳሌ በሀይማኖት ስርዓቶች ላይ የሚደረገው ጥናት ትኩረቱ በታወቁ የሀይማኖት መጽሐፍት ውስጥ ከታዘዘው ውጭ ሰዎች በራሳቸው (የሀይማኖት አማኝና ተከታይ መሆናቸው ሳይቋረጥ ማለት ነው) በሚከተሏቸው እምቶችና በሚፈጽማቸው እምነታዊ ድርጊቶች ላይ ነው (1991፡14)*

ስለዚህ የቆሎ ተማሪዎች በሀይማኖታዊ ተቋም ስር ያሉ እና የሀይማኖቱ ተከታዮች ቢሆኑም እንደተባለው ሀይማኖታቸውን ሳይለቁ በግልም ሆነ በቡድን የሚፈጽሟቸው

ሀገረሰባዊ እምነቶች አሏቸው፡፡ በዚህ እምነታቸውም እንደ ቡድን ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ የአንድን ቡድን እምነት የሚያጠና ተመራማሪም እምነቱ ትክክል ነው ወይም ስህተት ነው ከማለት ተቆጥቦ እምነቱን በስነቃል፣ በልማድ ወይም በቁሳዊ ባህል አማካይነት እንዴት እንደሚገልጹት ማሳየት ይጠበቅበታል (Martha and Martine; 2005,57) ስለዚህ አንድን ቡድን በማጥናት ያቡድን እምነቱን በሶስቱ የፎክሎር ዘርፎች እንዴት እንደሚገልጸው ማወቅ ይቻላል፡፡ ስለ ሀገረሰባዊ እምነት ሲነሳ አብሮ የሚመጣው rites of passage (ወግ ማድረግ) ነው፡፡ ምክንያቱም ወግ ማዕረግ አንዱ የእምነት መገለጫ በመሆኑ ነው፡፡ ማንኛውም ቡድን ይሁን ግለሰብ በህይወቱ የሚያልፍባቸው የህይወት ደረጃዎች ይኖሩታል፡፡ እነዚህ ደረጃዎችም ለቡድኑም ሆነ ለግለሰቡ የራሳቸው የሆነ ፋይዳ ይኖራዋል፡፡ (Dorsen; 1972,159)

የቆሎ ተማሪዎችም በትምህርት ቤት ህይወታቸው የተለያዩ የህይወት ደረጃዎችን ያልፋሉ፡፡ ለትምህርት ቤተሰቦቻቸው ጥለው ይሰደዳሉ ከስደት መልስም በአካባቢው የተከበሩ የሀይማኖት መሪዎች ይሆናሉ፡፡ ይህንን የተማሪዎችን ወግ ማዕረግ በሁለት መልኩ ማየት ይቻላል፡፡ አንዱም Marthaና Martine እንደሚሉት ወግ ማዕረግ የሚባለው ነገር የግለሰቡ ህይወት ላይ ትልቅ አሻራ አሳርፎ የሚያልፍ ነው (2005፣110) የቆሎ ተማሪዎች ከተማሪነት፣ ከስደትና ከችግር ወደ መሪነት የሚሸጋገሩበት ደረጃ በህይወታቸው ትልቁን ቦታ ይይዛል በሌላ መልኩ የቆሎ ተማሪዎች ወደ ማዕረግ የሚደርጉት ጉዞ ከሚታዊ ጉዞ ጋር ሊዛመድ ይችላል፡፡ ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፣45) እንደገለጸው ማንኛውም ተጋዳሊ ለገድል ሲጠራ የሚያልፍባቸው ሶስት ምዕራፎች አሉ፡፡ ከወገን መለየት፣ ወደ ጥብቅ ስፍራ መዝለቅና ከስፍራው አንዳች በረከት ይዞ መመለስ እነዚህ ምእራፎች በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ከመለየት፣ ከመዝለቅና በረከት ይዞ ከመመለስ ጋር ተያይዘው ከሚነሱ ጭብጦች መካከል አንዱ ፍለጋ ነው (ቴዎድሮስ፣ 2001፣45)

የቆሎ ተማሪዎችም ለጉዟቸው ምክንያት የሚሆናቸው ፍለጋ ነው፡፡ የቆሎ ተማሪዎች ከቤተሰብ ተነጥለው ጋራ ሸንተረሩን አቆራርጠው እውቀትና ጥበብ ፍለጋ እጅግ አድካሚ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ቴዎድሮስ እንደገለጸው የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት የሚደረገው ጉዞ ዓላማዊም ሃይማኖታዊም መሰረት ሊኖረው ይችላል (2001፣60) የቆሎ ተማሪዎች ጉዞም ሁለቱን ነገሮች አጣምሮ የያዘ ነው፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው አንድ ቡድን የተለየ ማንነት (Identity) ይኖረዋል፡፡ ማንኛውም አጥኝ የሚያጠናውን ቡድን ማንነት (Identity) የግድ መመርመር አለበት ባይባልም በተዘዋዋሪ መልኩ ግን የቡድኑን ታሪክ፣ ባህል፣ ማህበራዊ ህይወት ወዘተ ሲያጠና የዚያን ቡድን ማንነት ማሳየቱ አይቀርም፡፡ ማንነት የሚለው ጽንስ ሀሳብ የአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ባህርይ፣ የእለት ከእለት ክንውን ወይም ልምድ ለየብቻቸው ተነጥለው ሳይሆን የእነዚህ ጉዳዮች ውህደት የሚፈጥረው ጉዳይ ነው፡፡ (Oring; 1974፡4) የአንድ ቡድን ማንነት ከሚገለጽባቸው የፎክሎር ዘርፎች መካከል ደግሞ ተረቶች ይጠቀሳሉ፡፡ ተደጋግመው የሚነገሩ ተረቶች የአንድን ቡድን ብሎም የተራኪውን ማንነት ማሳወቅ ይችላሉ (Martha and martine; 2005, 165) ከላይ እንደተጠቀሰው በቡድኑ ውስጥ በተደጋጋሚ ከሚነገሩት ተረቶች በመነሳትም የቡድኑን አጠቃላይ አመለካከት መረዳት ይችላል፡፡ ፈቃደ አዘዘ እንደሚለው ከስነቃል ተግባራት መካከል አንዱ የማምለጥ ተግባር ነው፡፡ የሰው ልጅ ከአሰልቺውና ከተደጋጋሚ የህይወት ውጣ ውረድ በመውጣት የእራሱን አዲስ አለም ይፈጥራል፡፡ ይህንን የሚያደርገው በሳቅና በጨዋታ አዋዝቶ እያቀረበ በማምለጥ ነው (1991፤18)፡፡ ስለዚህ ስነቃል ማምለጫ ነው ሲባል አንድ ቡድን በተደጋጋሚ በሚተርተው ተረቶች አማካይነት ከተለመደው ህይወት ለማውጣት በሚያደርገው ጥረት አማካይነት ነው፡፡ የቆሎ ተማሪዎች በሚተርኳቸው ወይም እነሱ ገጸባህርይ ሆነው በሚሳሉባቸው ተረቶች ማንነታቸውን መረዳት ይቻላል፡፡ የቆሎ ተማሪዎች ለብልጣብልጥ ተረቶች ገጸባህሪይ ሆነው ይስላሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህ ጉዳዮች ለምን እንደሚደጋገሙ በማየት የቆሎ ተማሪዎችን ማንነት መረዳት ይቻላል፡፡

እነዚህን የብልጠት ተረቶችም እንደ አንድ ዘርፍ ቆጥሮ ማጥናት እንደሚቻል የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ፡፡ ተረቶችን በተለያዩ መልኩ ከፋፍሎ ማጥናት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ መንገዶች አንዱ የተረቶቹን ባህሪይ መሰረት በማድረግ የሚከናወን ነው ባህሪያቸውን መሰረት አድርገው ሲከፋፈሉም “የትለያ ተረቶች” (trickster tale) አንድ ምድብ ይዘው ይገኛሉ (ፈቃደ፣ 1991፣ 45-55)። በሌላ በኩል ተረቶች ከሚያነሱት ሀሳብና ከሚያስተላልፉት ጭብጥ በመነሳት ሊመደቡና ሊጠኑ ይችላሉ፡፡ የብልጠት ተረቶች እንደ አንድ ንዑስ ክፍል ተቆጥረው መጠናት ይችላሉ (Finnegan; 1992,154) ከላይ ከተነሱት ሃሳቦች በመነሳት የቆሎ ተማሪዎች በገጸባህርይነት የተሳሉባቸውን ተረቶች በመውሰድና በመመርመር ስለ ተማሪዎች ህይወት መናገር ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## 4. የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ፎክሎራዊ እይታ

በዚህ ምዕራፍ በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ህይወት ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ በመስክ ቆይታ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ትንተና ተካሂዶባቸዋል። ቀሪዎቹም እንደአስፈላጊነቱ ቀጥታ ተጠቅሰው ቀርበዋል፡፡

### 4.1. ጉዞ

በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ውስጥ ጉዞ የመጀመሪያው ክስተት ነው፡፡ በተማሪዎች ህይወት ውስጥ ከንባብ ቤት ተማሪዎች በስተቀር በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ያሉ ተማሪዎች በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት አድካሚና እልህ አስጨራሽ ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎች የሚያደርጉት ጉዞ ሀይማኖታዊም ስነልቦናዊም ምክንያት አለው፡፡ ተማሪዎች ጉዞ ከሚያደርጉባቸው ምክንያቶች መካከልም ደጋግመው የሚጠቅሷቸው፡- ከቤተሰቦቹ ጋር በምቾት እየተኖረ ትምህርት አይገባም በሚል እምነት የተነሳ፣ በግብርና ስራ ሳይጠመዱ ሙሉ ጊዜያቸውን በትምህርት ለማሳለፍና የተሻለ መምህር ፍለጋ የሚሉት ናቸው፡፡ ይህንን ሃሳብ አስመልክቶ ተማሪ ሙሴ ተሻገር የሰጠውን ሀሳብ ማቅረቡ የጉዞውን ምክንያት የበለጠ ይገልፃል፡፡

> *ተማሪ ሁልጊዜ እንደተንከራተተ ነው የሚኖረው ከአገር አገር ከመምህር መምህር ሳይቀያየር የተማረ ተማሪ ምኑን ተማሪ ሆነው ሆድ ሙሉ እየበሉና በእናት እጅ እየጎረሱ ትምህርት አይገባም፡፡ ጌታችንም እናንተ ልፉ እኔ እጨምርላችኋለሁ ነው ያለው ስለዚህ ተማሪ አብዛኛውን ህይወቱን በራሱ ፈቃድ የተሰደደ ስደተኛ ሆኖ ነው የሚኖረው አሁን እዚህ እኛ ዘንድ ያሉት ተማሪዎች ከወሎ፣ ከጎንደር፣ ከሸዋ የመጡ ናቸው፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣ ሚያዚያ 29፣ 2003ዓ.ም)*

ከላይ በምክንያትነት ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው በተማሪዎች ስነልቦና ትምህርት መስዋዕትነትን፣ መፈተንና መቸገርን ይፈልጋል፡፡፡ በምቾትና በድሎት እየተኖረ ትምህርት አይገባም የሚል ነው፡፡ የተሻለ ነገር ለማግኘት ከፍ ብሎ ለመገኘትና ዓላማን ለማሳካት ፈተናዎችን ማለፍና በችግር አለንጋ መገረፍ አለብን ብለው ስለሚያምኑ ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ጉዞ ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎች እውቀት ተርበው ጥበብን ፈልገው ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ሲወጡ የሚያደርጉትን ጉዞ ለዓላማ መሳካት የከፈሉት መስዋዕትነት አድርገው ይቆጥሩታል፡፡

ተማሪዎች በጉዟቸው ወቅት ርሀብ፣ ጥም፣ በሽታ፣ እሾህ አሜካላ እንደሚያጋጥማቸው ቢያውቁም ጉዟቸው በአንዳንች ሀይል እንደሚመራ ያምናሉ፡፡ ይህ ኃይልም ከአደጋ ይጠብቀናል ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ጉዞውን የሚያደርጉት በልበ ሙሉነት ነው፡፡ ምክንያቱም ገና ከመነሻው ለጉዞ ሲዘጋጁ እራሳቸውን ለአንዳንች ሀይማኖታዊ አገልግሎት የተመረጠ አድርገው ይቆጥራሉ፡፡ በመስክ ቆይታዬ በአራቱም ጉባኤዎች ያሉ ተማሪዎች እንደተናገሩት (ሚያዚያ 30፣ 2003) በመንገዳቸው "እመቤታችን ማርያም ከመዓትና ከችግር ታወጣናለች፣ ታዝንልናለች፣ ታበረታታናለች" ብለው ያምናሉ፡፡ በጉዞ ወቅት የእሷን ስም ጠርተው ከለመኑ የሚያሳድራቸውም ሆነ የሚያበላቸው እንደማያጡ ያስባሉ፡፡ ስለዚህ ጉዟቸው ሙሉ በሙሉ በሌላ ሀይል የሚደገፉና እነሱም ለጉዞ የተመረጡ እንደሆኑ ያምናሉ፡፡ ሌላው ቀርቶ በመንገድ የሚገጥማቸው ፈተና ሁሉ ጉዞውን ያዘጋጀልን ሀይል ሊፈትነን ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ በፈተና ተደናቅፎ ትምህርት አቋርጦና ከጓደኛ ተለይቶ በችግር ተፈቶ ወደ ቤት መመለስ እምነትን እንደማጉደል ይቆጠራል፡፡ የተሻለ መምህር ወዳለበት አካባቢ የሚመራቸውም ይህ ሀይል መሆኑን ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ጉዞ ሲያደርጉ ለአንድ ትልቅ ጉዳይ ከነሱ በላይ በሆነ ሃይል የተመረጡ መሆናቸውን አምነው በመቀበል ነው፡፡

እነዚህ ተማሪዎች የንባብ ቤት ትምህርታቸውን በአካባቢያቸው በሚገኙ መምህራን ካጠናቀቁ በኋላ በህይወታቸው ትልቅ ለውጥ የሚያመጣውን ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ ጉዟቸውም በችግርና በፈተና የተሞላ ነው፡፡ ጉዞ ሲጀምሩ ከለመዱትና ከሚያውቁት ቤተሰብ እንዲሁም ማህበረሰብ መጥተው ወደ ሌላ አዲስ ህይወት ይቀላቀላሉ፡፡ ከዚህ በፊት ያልለመዱት አዲስ ህይወት መኖር ይጀምራሉ፡፡ ይህ ጥናት በተካሄደበት ጎጃም ፍኖተ ሰላም አካባቢ ባታ ደብር የቅኔ ትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎች ሁለት ተማሪዎች ከጎንደር፣ አንድ ከወሎ ዋድላ እና በወረዳው ካሉ እሩቅ ቦታዎች የመጡና ቤተሰቦቻቸውን ጥለው ከወጡ ብዙ አመት ያስቆጠሩ ናቸው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው እነዚህ ተማሪዎች ይህንን አስቸጋሪ ጉዞ ወደውና ፈቅደው ሲያደርጉት ከጉዞው መልስ ሀሳባቸውን አሳክተውና በእውቀት በልፅገው ወደ ቤተሰቦቻቸው እንደሚመለሱ በማሰብ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው በችግር ከአገር አገር ተንከራትተው ከተማሩ በኋላ ጥለውት ወደ መጡት ማህበረሰብ በመመለስ ትልቅ ሀይማኖታዊ ሀላፊነት ተሰጥቷቸው ይቀመጣሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት የእነዚህ ተማሪዎች ጉዞ ቴዎድሮስ ገብሬ ( 2001፡45) እንደሚለው ከሚታዊ ተጋዳሊ ጋር ሊመሳሰሉ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም በተማሪዎች

ተደጋግመው የሚከሰቱት ክንውኖች ከሚታዊ ተጋዳሊያን ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ በሚታዊ ተጋዳሊያን ዘንድ ከወገን መለየት፣ መዝለቅና በረከት ይዞ መመለስ ከጉዞ ጋር አብረው የሚከሰቱ ክንውኖች ናቸው፡፡ የእነዚህ ተማሪዎች ጉዞም እነዚህን ምዕራፎች የግድ ያልፉል፡፡ ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ሲወጡ ዋና ዓላማ አድርገው የሚነሱት ፍለጋ ነው፡፡ ፍለጋውም እውቀትና ጥበብን ነው፡፡ ይህንን የፈለጉትን ለማግኘትም ከወገን ተነጥለው አስቸጋሪ የሆነውን ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ አድካሚውን ጉዞ አድርገው የሚፈልጉትን ካገኙ በኋላም ከትልቅ ማዕረግ ጋር መጀመሪያ ወደተነሱበት ማህበረሰብ ይመለሳሉ፡፡ ተማሪዎች የሚፈልጉትን እውቀት ካገኙ በኋላ ጥለውት ለመጡት ማህበረሰብ ሀይማኖታዊ በረከት ይዘው ይመለሳሉ፡፡ ምክንያቱም የዛሬዎቹ ተማሪዎች ናቸው ማህበረሰቡን በሀይማኖት መሪነት የሚያገለግሉት፡፡

በሌላ በኩል የተማሪዎች ጉዞ እንደወግ ማዕረግ (rites of passage) ሊቆጠር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ጉዞ ከጀመሩበት ደቂቃ ጀምሮ ከነባር ሁኔታ ወደ አዲስ ሁኔታ ከነባር የአኗኗር ዘይቤ ወደ ሌላ የኑሮ ሁኔታ ይሸጋገራሉ፡፡ በቤተሰቦቻቸው ጥላ ስር ከመተዳደር ወጥተው እራሳቸውን ማስተዳደር ይጀምራሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ጉዞ እንደአንድ ሽግግር ሊቆጠር ይችላል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ከወጡ በኋላ የእለት ምግባቸውን ፈልጎ የማግኘት፣ እራሳቸውን ከተለያዩ አደጋዎች የመጠበቅ፣ ልብሳቸውን የማዘጋጀትና የእራሳቸውን ጎጆ እስከመቀለስ የደረሰ ሀላፊነት በራሳቸው ፈቃድ ይሸከማሉ፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ ከቤተሰብ ጥላ ስር ወጥተው እራሳቸውን ማስተዳደር መጀመራቸውን ያሳያሉ፡፡

በሌላ በኩል እነዚህ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታቸውንና ከአገር አገር መንከራተታቸውን አጠናቀውና የሚፈልጉትን አግኝተው ወደ ተነሱበት ማህበረሰብ ሲመለሱ የሚሰጣቸው ክብርና ሃላፊነት ሌላው የወግ ማዕረግ መገለጫ ሊሆን ይችላል፡፡ በእያንዳንዱ የገጠር ቤተክርስቲያን አገልጋዮች የዛሬዎቹ ተኳኝ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከአገር አገር ከመምህር መምህር ተዟዙረው ያገኙትን እውቀት ይዘው ሲመለሱ ማህበረሰቡ በደስታ ይቀበላቸዋል፡፡ ሀይማኖታዊ ተቋማትን እንዲመሩ ሃላፊነት ይሰጣቸዋል፡፡ ከዚህ በኃላ ማህበረሰቡን ከፈጣሪው ጋር የሚያገናኙ፣ የተጣሉትን አስታራቂና አድራጊ ፈጣሪ ይሆናሉ፡፡ ይህንን ሁሉ እንዲያደርጉ የሚሰጣቸው ክብር ከጉዞው በኃላ የመጣ ስለሆነ እንደ አንድ የህይወት ሽግግር ይታያል፡፡ ከእዚህ በኃላም ህይወታቸው አዲስ መልክ ይይዛል፡፡

### 4.2. ስም ቅየራ

በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ተደጋግመው ከሚመጡ ክስተቶች መካከል ስም ቅየራ አንዱ ነው፡፡ ማንኛውም በቆሎ ትምህርት ቤቶች የሚገኝ ተማሪ ቤተሰቦቹ ያወጡለትን ስም ቀይሮ በሌላ ስም ይጠራል፡፡ ከተማሪዎች በተገኘ መረጃ መሰረት ስማቸውን የሚቀይሩበት ብዙ ምክንያቶች አሏቸው፡፡ ምክንያቶቹም ማህበራዊና ሀይማኖታዊ መሰረት የያዙ ናቸው፡፡

#### 4.2.1. ከቤተሰብ ለመደበቅ

ተማሪዎች ስማቸውን ከሚቀይሩባቸው ምክንያቶች መካከል ከቤተሰብ ለመደበቅ ሲሉ የሚያደርጉት ይጠቀሳል፡፡ ይህ ምክንያት ቀደም ብሎ ከተነሳው ከጉዞ ሀሳብ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ተማሪዎች ጉዞ ሲያደርጉ ከቤተሰቦቻቸው ፍቃድ አያገኙም፡፡ ከተማሪዎች እና ከወላጆች በተገኘ መረጃ መሰረት ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ፈቅደው ቢልኳቸውም የእነሱ ዓላማ በአካባቢያቸው በሚገኙ የንባብ ቤቶች ፊደል ቆጥረውና ዳዊት ደግመው እንዲያበቁ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ከፍ ወደሚል ደረጃ ጉዞ የሚያደርግ ተማሪ ከወላጆቹ ፈቃድ አያገኝም ስለዚህ ጉዞውን የሚያደርገው ከቤተሰቦቹ በመደበቅ ነው፡፡ ቤተሰቦቹም የጠፉ ልጃቸውን በየጉባኤው ሰው እየላኩ ማፈላለግ ይይዛሉ፡፡ ስለዚህ ቤተሰብ ለልጁ ባወጣለት ስም እየጠራ ቢፈልግም ልጁ ገና ወደ ጉባኤው ሲቀላቀል ስሙን ስለሚቀይር አየሁ የሚለው ሰው አያገኝም፡፡ ወላጆች ልጆቻቸው እነሱን ጥለው እንዳይሄዱ የማይፈቅዱበት ሁለት ምክንያቶች አሏቸው፡፡ የመጀመሪያው ለልጆቻቸው ካላቸው ፍቅር የተነሳ በሌላ አገር ሄደው ለምነው እየበሉ እንዲኖሩ አይፈቅዱላቸውም፡፡ ከእነሱ እንዲርቋቸውም አይፈቅዱም፡፡ ተማሪዎች ሩቅ አገር አቆራርጠው ስለሚሄዱና እንደወጡም ሳይመለሱ ስለሚቀሩ ልጆቻቸውን ወደ ሌላ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ መርቀው አይሸኟቸውም፡፡ በሌላ በኩል ወላጆች ልጆቻቸው ከእነሱ ጋር ሆነው ስራ እያገዙ አብረው እንዲኖሩ ይፈልጋሉ፡፡ ልጆቻቸው የእነርሱን ፈለግ እንዲከተሉም ይፈልጋሉ ስለዚህ ልጆቻቸው የተሻለ ትምህርት ፍለጋ እንዲሄዱ አይፈቅዱም፡፡ ከዚህ የተነሳም ተማሪዎች ከወላጆች ጠፍተው ስለሚወጡና ወላጆቻቸው እንደሚፈልጓቸው ስለሚያውቁ በስማቸው አፈላልገው እንዳያገኟቸው ስማቸውን ይቀይራሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ስማቸውን ሲቀይሩ ለትምህርታቸው የሚከፍሉት መስዋዕትነት አንዱ ገፅታ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሚያዚያ 29፣ 2003ዓ.ም ከባከል ገብርኤል የዜማ ተማሪዎች መካከል ተማሪ ሙሴ ተሻገር እንደገለፀው ወደ አዲስ ጉባኤ (ትምህርት ቤት) የሚቀላቀል ተማሪ በምንም መንገድ ትክክለኛ ስሙን አይናገርም፡፡ በጣም የሚቀራረቡና አብሮ አደግ ጓደኞቸ ቢኖሩም እንኳን ትክክለኛ ስማቸውን ላይጠሩና ይማማላሉ፡፡ በስህተት ቢጠራው እንኳን በዘዴ ማለፍ ይኖርበታል፡፡

### 4.2.2. እራስን ከመተት ለመከላከል

ተማሪዎች ስማቸውን የሚቀይሩበት ሌላው ምክንያት ከእምነት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ተማሪዎች በጋራ ኑሯቸው በተለያዩ ምክንያቶች ግጭት ውስጥ ይገባሉ፡፡ በትምህርት መበላለጥ ምክንያት ቢቀናኑ አልያም በሌላ ምክንያት ቢጋጩ እርስ በራሳቸው የሚጎዳዱበት መተት (ድግምት) ይሰራሉ፡፡ ሰኔ 14፡2003ዓ.ም ከባታ ደብር ቅኔ ተማሪዎች መካከል ተማሪ ዕጌ ተገኝ በሰጠው መረጃ መሰረት ድግምት ወይም መተት ደግሞ በትክክል የሚሰራው በትክክለኛ ስማቸው ከተደረገባቸው ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ድግምት (መተት) ቢሰራባቸው እንዳይደርስባቸው ለመከላከል ስማቸውን ይለውጣሉ መተት እንደተደረገባቸው ቢያውቁም እንኳን በትክክለኛ ስማቸው ስላልሆነ አይደርስም ብለው ያምናሉ፡፡ምክንያቱም የተደረገው ነገር እነሱ ላይ አያርፍምና ነው። ስለዚህ ትክክለኛ ስማቸው ካልታወቀ በቀር ማንኛውንም ድግምት (መተት) አይፈሩም፡፡ ተማሪ አምሀ በድሉ የሰጠውን ሀሳብ ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል፡፡

> *እዚህ ከመምጣቴ በፊት እስቴይ ቅኔ ቤት ነበርሁ፡፡ አንድ ከደባርቅ የመጣ ተማሪ ነበር እኛ የምናውቀው ስሙ ዕጌ ነበር አንድ ቀን ከጓደኛው ጋር ከደብር ሲወጡ ተቀምጣ የምትለምን ሴትዮ ታገኛቸውና ኧረ አይናለም ብላ አገላብጣ ትስመዋለች ጓደኛውም ያልሰማ መስሎ ዝም ይላል፡፡ ከብዙ ጊዜ በኋላ ሁለቱ ጓደኞች በሆነ ምክንያት ይጣላሉ፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛው ለሁለት ወር ጎጃም ቆይቶ መጣ ለካስ በትክክለኛው ስሙ አሰርቶበት ኑሮ ዕጌ እፍ ብሎ ከትምህርት ቤት ጠፍቶ ቀረ፡፡ ይህንን በአይኔ አይቻለሁ እና እንዴት ብለን ስማችንን እንናገራለን ድንገት ስማችን ቢታወቅ እንኳን ጉባኤውን ለቀን እንጠፋለን (ሰኔ 18፡ 11 2003ዓ.ም)*

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ምንም እንኳን በሀይማኖታዊ ተቋም ስር የሚኖሩ ቢሆኑም ከሀይማኖታቸው ስርዓት የወጣ የእራሳቸውን እምነት ያራምዳሉ፡፡ ተማሪዎች ነገ ከነገ ወዲያ በሀይማኖት መሪነት የሚያገለግሉ ቢሆኑም ድግምት እንደሚደርስ አምነው ስም እስከመቀየር ይደርሳሉ፡፡ ከዚህ ለማምለጥም የእራሳቸውን መፍትሄ ወስደዋል፡፡

### 4.2.3. ከመጽሐፍ ቅዱስ በመነሳት

ለተማሪዎች ስም ቅየራ በምክንያትነት ከሚጠቀሱት መካከል ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው ሌላው ምክንያት ነው፡፡ ተማሪዎች የስማቸውን መለወጥ ከሀይማኖታቸውና ከስብዕናቸው መለወጥ ጋር ያያይዙታል፡፡ ዓለማዊ ህይወት ትተው ወደ መንፈሳዊ ህይወት መግባታቸውን መሰረት በማድረግ ቤተሰብ ያወጣላቸውን ዓለማዊ ስም ይለውጣሉ፡፡ በስማቸው መለወጥ ምክንያት ማንነታቸው መለወጡን አምነው ይቀበላሉ፡፡ ይህ ከስብዕና እና ከሀይማኖት ጋር የተያያዘ ስም ቅየራ ደግሞ መሰረቱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሲመርጥ ስማቸውን እንደለወጠው ሁሉ እነሱም ለመምህራቸው እራሳቸውን እንደ ደቀ መዝሙር ስለሚቆጥሩ ስማቸውን ይለውጣሉ፡፡

በሌላ በኩል በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰው ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሲመርጥ ከሀይማኖታቸው መለወጥ ጋር በተያያዘ ስማቸውን ቀይሯል፡፡ ተማሪዎችም ስማቸውን ሲለውጡ በዘፈቀደ አይደለም የሚለወጠው ስማቸው የወደፊት ፍላጎታቸውን፣ ምኞታቸውን፣ አድናቆታቸውን ሁሉ ሊጠቁም ይችላል፡፡ በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ስም ሲቀየር የሚለወጠው ስም በራሱ ወይም ከአባታቸው ስም ጋር ሆኖ አንድ አይነት ፍቺ መስጠት አለበት፡፡ ይህ ስም ትርጉም እንዲሰጥ አድርጎ መለወጥም ሀይማኖታዊ መሰረት እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ የሉቃስ ወንጌልን መጥቀሱ ነገሩን ያስተማምናል፡፡ «ሲነጋም ደቀ መዛሙርቱን ወደ እሱ ጠራቸው፡፡ ከውስጣቸውም ዐስራ ሁለቱን መረጠ፤ ሐዋርያት ብሎም ሰየማቸው (ሉቃ. 6÷13) ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ጠርቶ አላበቃም፤ ይልቁንስ የጋራ መጠሪያ ሰጣቸው፡፡ ስለዚህ ይህንን የጋራ ስያሜ ያገኙት የእሱ ተከታዮች ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ነው፡፡

ስለዚህ በመፅሐፍ ቅዱስ የሚከሰት የስም ለውጥም ዝም ብሎ የሚመጣ ሳይሆን ከማንነት መለወጥ ጋር ወይም ሀይማኖት ከመለወጥ ጋር አብሮ የሚመጣ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በማርቆስ ወንጌል እንደተገለፀው ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠው የስም ለውጥ ከአንዳች ፍቺ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ «የዘብዴዮስ ልጅ ያዕቆብንና የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስንም «ቦአኔርጌስ» ብሎ ሰየማቸው፤ «የነጎድጓድ ልጆች» ማለት ነው፡፡ (ማርቆስ. 3÷13) ከላይ በቀረቡት ሁለት ጥቅሶች መረዳት እንደሚቻለው ስም በግልም በቡድንም ሊለወጥ ይችላል ነገር ግን ስያሜው ከባህርይ እና ከግብር ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ ተማሪዎችም ከዚህ

ሀይማኖታዊ መሰረት በመነሳት ስማቸውን ሲለውጡ ትርጉሙን በማሰብ ነው፡፡ በመስክ ስራ ጊዜ ቤተሰብ ያወጣለትን ስም ያልነገረኝ ነገር ግን የአባቱ ስም አንተነህ የሚባል ተማሪ ስሙን ‹‹ለይከ ማሪያም አንተነህ›› ብሎ ለውጦታል፡፡ ትጉሙም ‹‹የማሪያም ተማሪ ነህ›› እንደማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ስያሜ ከተማሪው ሕይወት ጋር የተያያዘ ፍቺ ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች የድንግል ማርያምን ስም ጠርቶና እሷን አምኖ የሚኖሩ መሆኑን በስሙ መግለፅ ችሏል፡፡ ብዙዎቹ ተማሪዎች የሚጠሩባቸው ስሞች ከመፅሐፍ ቅዱስ የተወሰዱ ወይም ደግሞ የጻድቃን ስሞች ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ስማቸው በግዕዝ ቋንቋ የተሰየመ ነው፡፡ በአጠቃላይ በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ውስጥ ስም ቅየራ አንድ ጊዜ ብቻ የሚከናወን አይደለም ምክንያቱም እንደአስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ሲዘዋወሩም ስማቸውን አብረው ይለውጣሉ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች በሚማሩበት ጉባኤ አስነዋሪ ድርጊቶችን ሊፈፅሙ ይችላሉ በዚህ ድርጊታቸው ተወግዘው ጉባኤ ለቀው ሲሄዱ የነደፈ ስማቸውን ለውጠው በሌላ ስም ይጠራሉ፡፡ ስማቸውን በመቀየርም እንደመደበቂያ (ማምለጫ) ይጠቀሙበታል። በአጠቃላይ በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ውስጥ ስምን መለወጥ ስነልቦናዊ፣ ማህበረሰባዊና ሀይማኖታዊ ምክንያቶችን የያዘ ነው፡፡

## 4.3. ልመና

ልመና የቆሎ ተማሪዎች ተለይተው የሚታወቁበት ተግባራቸው ነው፡፡ የቆሎ ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚያሳልፉትን ህይወት የሚማሩት ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› ብለው ለምነው በሚያገኙት ቁራሽ ነው፡፡ ልመና በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ የእራሱ የሆነ ደንብና ስርዓት አለው፡፡

### 4.3.1. የመለመኛ ሰዓት

በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ማንም ተማሪ በፈለገው ሰዓት ወጥቶ መለመን አይችልም የቆሎ ተማሪዎች ለልመና የሚንቀሳቀሱት በአማካይ ከምሽቱ አስር ሰዓት በኋላ ነው፡፡ ይህ የተወሰነ ሰዓትም የቆሎ ተማሪዎች ከሌላው በልመና ከሚተዳደር ሰው ተለይተው ይታወቁበታል፡፡ ከተማሪዎች በተገኘ መረጃ መሰረት የመለመኛ ሰዓታቸው ምሽት ላይ መሆኑ በዋናነት ሁለት ምክንያቶችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት ከሚለምኑት ማህበረሰብ የስራ ባህል ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ጥናት በተካሄደበት አካባቢ በጥዋት ተነስቶ በየስራው ተሰማርቶ የሚውለው ገበሬ ወደ ቤቱ የሚመለሰው ፀሐይ ስታሽቆለቁል ነው፡፡ ተማሪዎች ከዚያ በፊት ለልመና ቢነሱ በየተመደቡበት መንደር ቤት ተዘግቶ

አልያም ህፃናትን ብቻ ነው የሚያገኙት፡፡ ስለዚህ ለልመና ወጥተው ባዶ እጃቸውን እንዳይመለሱ በመፍራት የገበሬዎቹን ወደ ቤት የመመለሻ ሰዓት ጠብቀው ይንቀሳቀሳሉ፡፡

ሌላውና ሁለተኛው ምክንያት ከተማሪዎች የትምህርት ስርዓት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በቆሎ ተማሪዎች ከሰዓት በፊት ያለው ሰዓት አብዛኛው የትምህርት ሰዓታቸው ነው። ስለዚህ ለልመና የሚነሱት ከትምህርት ሰዓታቸው መጠናቀቅ በኋላ ነው ለምሳሌ በቅኔ ቤት ያሉ ተማሪዎች በጥዋት ተነስተው የእለቱን ቅኔ የሚቆጥሩበት ታሪክ በመምህራቸው ይነገራቸዋል፡፡ ይህንን ታሪክ ይዘው በአማካይ ከሶስት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ለቅኔ ቆጠራ ፀጥ ወዳለ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ ከአምስት ሰዓት ጀምሮ በየተራ ለመምህራቸው የቆጠሩትን ቅኔ ይነግራሉ ስለዚህ ከሰዓት በፊት ያለው ሰዓት ሁልጊዜም በዚህ መንገድ ያልፋል፡፡ በመሆኑም ለልመና ከሰዓት በኋላ የሚነሱበት ምክንያት ከግማሽ ቀን በላይ በትምህርት ስለሚውሉ ነው። በመሆኑም ለልመና የሚሰማሩት ይህንን ሁሉ ከፈፀሙ በኋላ በተመሳሳይ ሰዓት ነው፡፡



ፎቶግራፍ 1፡- ተማሪዎች ሰዓታቸውን ጠብቀው ወደ ልመና ሲሰማሩ

### 4.3.2. የመንደር ድልድል

የቆሎ ተማሪዎች በልመና ጊዜ በጥንቃቄ ከሚፈፅሟቸው ስርዓቶች መካከል የመንደር ድልድል አንዱ ተጠቃሽ ነው፡፡ ተማሪዎች በሚማሩበት ጉባኤ ስር የሚጠቃለሉ የገጠር ቀበሌዎች በሙሉ በእጣ እየተደለደሉ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ፡፡ የመንደር ድልድሉም የሚካሄደው በእጣ አማካይነት ነው እያንዳንዱ ተማሪም በእጣ የደረሰውን መንደር ብቻ

የመለመን ግዴታ ይጣልበታል፡፡ ይህንን ድልድል የሚያካሂዱት በጉባኤው የተመረጡ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ለመመረጥም በጉባኤው ያላቸው የተሻለ ባህርይ፣ እድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፣ ስነምግባር ወዘተ ግንዛቤ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህ ስርዓት በየሳምንቱ ሁልጊዜም ይካሄዳል፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ተማሪ በተመደበበት መንደር አንዱ ተጠቃሚ ሌላው ተጎጂ ሊሆን ስለሚችል ድልድሉ በየሳምንቱ እየተቀየረ ሁሉም ተማሪ ሁሉንም መንደር የማግኘት እድል ይኖረዋል፡፡ በዚህም አንድ ጊዜ የሄደበት መንደር ላይ ተጠቃሚ ባይሆን በሚቀጥው ይካሳል ማለት ነው። በዚህ መልኩም ድልድሉን ሚዛናዊ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡

### 4.3.3. የመለመኛ ቁሳቁሶች

ተማሪ ለልመና ሲነሳ ይዟቸው ከሚነሱ ቁሳቁሶች መካከል አኮፋዳውና ረጅም በትሩ ይጠቀሳሉ፡፡ ረጅም በትሩ ተማሪው ከውሻ ጋር ግብግብ ሲገጥም እራሱን የሚከላከልበት ብቸኛው መሳሪያው ነው፡፡ መቋሚያውም ውሻውን ከእርቀት ለመከላከል ሲባል ረጅም መሆን ይጠበቅበታል፡፡ አንድ ተማሪ በልመና ላይ እያለ የቱንም ያህል ውሻ ቢያስቸግረው እራሱን መከላከል እንጂ ውሻውን መደብደብ አይችልም፡፡ ይህንን ካደረገ የሚለምነውን ሰው እንደናቀ ይቆጠርበታል፡፡ ተማሪና ውሻ ምንጊዜም ባላንጦች ናቸው። በየገጠሩ ውሻ የሚመገበው የእራሱ ምግብ ተዘጋጅቶለት ሳይሆን የተራረፈ ነገርን ነው፡፡ የቆሎ ተማሪዎችም ብዙውን ጊዜ የሚሰጣቸው ትርፍራፊ ነገር ነው፡፡ ስለዚህ የውሻውን ምግብ እንደሚወስድበት ስለሚያውቅ ሌላ እንግዳ ሲመጣ የማይጮህ ውሻ ተማሪ «በእንተ ስማ ለማርያም» ሲል ከሰማ ዝም ብሎ አይቀመጥም፡፡ ይህንን አጥኚው በመስክ ቆይታው ማረጋገጥ ችሏል፡፡ አጥኚው በእንግድነት ወደ ቤት ሲገባ ከተኛበት ያልተነሳ ውሻ ትንሽ ቆይቶ ተማሪ ለልመና ሲመጣ ከተኛበት ተነስቶ ተማሪውን ላለማስጠጋት ትልቅ ፍትጊያ ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ተማሪ ምንጊዜም ቢሆን ውሻ እንደሚነሳበት ስለሚያውቅ መቋሚውን አስቀድሞ በጥንቃቄ ይንቀሳቀሳል፡፡

ባለቤቶቹም ሌላ እንግዳ ወይም መንገደኛ ሲመጣ ውሻው ሊናከስ ሲል እንደሚከላከሉት ሁሉ ለተማሪዎች ግን ይህንን አያደርጉም፡፡ ውሻው ሲያስቸግር ቢያዩትም ቁጭ ብለው ይመለከታሉ እንጂ ተማሪውን ለማስጣል የሚያደርጉት ነገር የለም፡፡ ቤት ውስጥ ቁጭ ብለው እያለ ውሻ ሲጮህ ሮጠው ይወጡና ተማሪ ከሆነ ግን ተመልሰው ይገባሉ፡፡ ምክንያቱም ተማሪ በአንድ እጁ እራሱን እየተከላከለ በሌላ እጁ የለመነውን ተቀብሎ

መሄድ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መንገድ ከውሻ ጋር ታግሎ ካልለመነ ውሻ በመፍራት የተመደበበትን መንደር አለመለመን ወይም በውሻ ተነክሶ መምጣት በተማሪዎች ዘንድ እንደ ውርደት ይቆጠራል፡፡ እራሱን ከውሻ ያልተከላከለ ምኑን ተማሪ ሆነ እየተባለ ይሳቅበታል፡፡

ተማሪዎች ለልመና ከሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች መካከል አኮፋዳ ሌላው ተጠቃሽ ነው፡፡ አኮፋዳ ከዘምባባ (በአካባቢው ስያሜ ከጮፋር) የሚሰራ የሚለምኑትን ነገር የሚያስቀምጡበት ነው፡፡ ነገር ግን አኮፋዳ የሚለምኑትን ነገር ከማስቀመጥ ባለፈ በተማሪዎች ዘንድ ትልቅ ትዕምርት አለው፡፡ ትዕምርቱም ከሀይማኖታቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ተማሪዎች እንደሚሉት መንፈስ ቅዱስ ከእመቤታችን አድሮ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተወለደ ሁሉ (እመቤታችን ማደሪያ እንደሆነችው ሁሉ) ለልመና ሲነሱ አኮፋዳው ከቁሳቁስ ማስቀመጫ ባለፈ የእመቤታችን ድንግል ማርያም ማደሪያ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለልመና ሲነሱ የድንግል ማርያምን ስም ሲጠሩ የሰዎችን ልቦና በማራራት፣ ከውሻና ከአደጋ በመጠበቅ ወደ ቤታችን በሰላም ትመልሰናለች ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ ለልመና ከጎጇቸው ወጥተው ዞረው እስኪመለሱ ‹‹እመቤታችን አብራ ትከተለናለች ማደሪያዋም አኮፋዳው ነው›› ብለው ስለሚያምኑ ለአኮፋዳቸው ትልቅ ክብር ይሰጣሉ፡፡ ምንጊዜም ለልመና ከወጣ ተማሪ ጋር ድንግል ማርያም አብራ ትከተላለች ተማሪዎችም አጥተን አንመለስም ብለው ያምናሉ የሚያገኟት ትንሽ ነገርም አኮፋዳ ከነካት ድንግል ማርያም ስለምትባርከው ረድኤት ይኖረዋል ብለው ያምናሉ። ከዚህ የተነሳም ድግስ ወደ ለልመና ወጥተው ያገኙትን ነገር አኮፋዳቸውን ሳያስነኩ አይመለሱም፡፡ ድግስ ወደ ሚበዛበት አካባቢ እንኳን ሲሄዱ ሁለት አኮፋዳ ይይዛሉ፡፡ የለመኑት ነገር ከአኮፋዳው የመያዝ አቅም በላይ ከሆነ ትተውት ይመጣሉ እንጂ በሌላ ነገር አይዙትም ምክንያቱም አኮፋዳ ካልነካው የለመኑት ነገር ረድኤት የለውም፤ አልተባረከምም ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ከ የባዱ ሚካኤል የንባብ ቤታ ተማሪዎች በተገኘ መረጃ መሰረት ገና ለልመና ሲነሱ፡-

ድንግል እመቤቴ ድንግል እመቤቴ
አንቺነሽና ምሳና እራቴ
በሰላም መልሽኝ ወደ ቤቴ

በማለት ነው የሚንቀሳቀሱት። ከዚህ አባባላቸው መረዳት እንደሚቻለው የእለት ጉርሳቸውን የምታዘጋጅም ሆነ ከክፉ ነገር የምትጠብቃቸው «ድንግል ማርያም» ናት። ስለዚህ ለልመና ሲነሱ ከእሷ ጋር መሆናቸውን በልበ ሙሉነት በመቀበል ነው፡፡ የእሷን ስም ጠርተው ለምነው ሲያገኙ እነሱም የእለት ጉርሳቸውን ያገኛሉ ሰዎቹም ስለ ድንግል ማርያም ስም ብለው ስለሚሰጡ ፅድቅን ያገኛሉ ብለው ያምናሉ፡፡

ይህንን እምነታቸውን ለመግለፅም ማንም ተማሪ ለልመና ወጥቶ በመንገድ ላይ እያለ ቢርበው አኮፋዳው ውስጥ ካለ ነገር አውጥቶ መብላት አይችልም። ምክንያቱም ከአኮፋዳው አብራቸው ስትንከራተት የዋለችው «ድንግል ማርያም» አብራ አለች፡፡ ስለዚህ በሰላም ጎጇቸው ደርሰው ድንግል ማርያምን የመሸኘት ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ይህ ድንግል ማርያምን የመሸኘት ስርዓትም እራሱን የቻለ ደንብ አለው፡፡ አንድ ተማሪ ዛሬ ላይ በሰላም የመለሰችው ድንግል ማርያም ነገ ሰዓቱ ደርሶ እስከምትመጣ በሰላም መሸኘት አለበት። አንድ ከልመና የመጣ ተማሪ የያዘውን አኮፋዳ እንደያዘ ወደ ጎጆው ዘልቆ አይገባም ከዚህ ይልቅስ በጎጆው አካባቢ ለአገኘው ለማንኛውም ተማሪ በአኮፋዳው ከያዘው የሚቀመስ ነገር «ስለማርያም የማርያም መሸኛ» በማለት ያቀምሳል፡፡ ከዚህ በኋላ ድንግል ማርያም በሰላም ወደ ቤቱ አድርሳዋለችና ከአኮፋዳው የፈለገውን ነገር መመገብ ይችላል፡፡ ይህንን ሳያደርግ በመንገድ ከአኮፋዳው የሚበላ ነገር የቀመሰ ተማሪ ማንም ባያየውም እንኳን ሰይጣን አሳስቶኝ ብሎ መጥቶ ለጓደኞቹ ያናዘዛል እንጂ ዝም ብሎ አይቀርም፡፡



ፎቶግራፍ 2፡- ተማሪው ከልመና መልስ ወደ ውስጥ ከመግባቱ በፊት ማርያምን ለመሸኘት የለመነውን ቁራሽ ለጓደኞቹ ሲያቃምስ

### 4.3.4. ማህበረሰቡ ለልመና ያለው አመለካከት

በመስክ ስራው ሂደት በተገኘ መረጃ መሰረት ከተማሪዎች ልመና ጋር በተያያዘ ማህበረሰቡ ሁለት አይነት አመለካከት አለው፡፡ ማህበረሰቡ ለልመና ያለው አመለካከት በአዎንታዊም በአሉታዊም መልኩ ተገልጿል፡፡

#### 4.3.4.1. አዎንታዊ አመለካከት

ተማሪዎች እውቀት ተጠምተውና ጥበብ ፍለጋ የድንግል ማርያምን ስም ጠርተው የሚኖሩ የፈቃድ ስደተኛ መሆናቸውን አምኖ የሚቀበል የማህበረሰብ ክፍል አለ፡፡ ስለሆነም ነገ ከነገ ወዲያ የቤተክርስቲያን አገልጋይ እንደሚሆኑና እነሱን ከአምላካቸው ጋር የሚያገናኙ መሸጋገሪያ መሆናቸውን ስለሚያምኑ የተማሪዎችን ልመና በደስታ ይቀበላሉ፡፡ የመኖር ህልውናቸውንም ይጠብቃሉ፡፡ በእነሱ አነጋገር የዛሬዎቹ ተማሪዎች ነገ ‹‹የእግዚአብሔር አይኖች›› ስለሆኑ ለእነዚህ ተማሪዎች ሲለምኑ መስጠት እንደ ዕድት ሳይሰጡ መቅረት ደግሞ ረድኤት እንደማጣት ይቆጠራል፡፡ ተማሪዎችን የእግዚአብሔር አይን ብለው የሚጠሯቸውም ከዚህ ህይወታቸው በኋላ በማንኛውም መንፈሳዊ ህይወት ከፈጣሪያቸው ጋር የሚገናኙት በእነሱ በኩል በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የነገውን መድረሻቸውን በማሰብ ለተማሪዎች ትልቅ ክብር ይሰጣሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ተማሪ ሳይለምን ከቀረ ረድኤት ቀረብን፣ በረከት ተለየን ብለው ያምናሉ፡፡ እዚህ ላይ በመስክ ስራ ጊዜ የገጠመኝን እንዳለ ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል፡፡ ግንቦት 5 ቀን የልምዳር አቦ ቤተክርስቲያን ከተማሪዎች ጋር ተገኝቼ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት አንድ አዛውንት ወደ መሪጌታውና ጥቂት ተማሪዎች ወደተቀመጡበት ጠጋ ብለው ሰላምታ ከሰጡ በኋላ ‹‹አንተ ተሜ በእኛ ጎጥ የምትለምነው አይደለህ?›› ብለው ጠየቁ ተማሪውም መሆኑን ሲገልፅላቸው በየኔታ ፊት የምጠይቅህ ጥያቄ ነበረኝ ብለው ወደ መሪጌታው ተጠጉ፡፡ ‹‹አለሚ ምን አጥፍቼ ነው መጥተህ መጥተህ እኔ ቤት ዘንድ ስትደርስ ሳትለምን የምታልፈው? ምን ነገር ሰማህብኝ? ክርስቲያን አደለም አሉህ? በል እስቲ ካጠፋሁም እንድክስ በየኔታና በዚህ በእንግዳው ፊት እውነቱን ንገረኝ›› ብለው በስሜት ጠየቁት ተማሪውም በተደጋጋሚ ሲለምን ልጆቹ እየወጡ አትቁም እንደሚሉት ገልጾ አዛውንቱም ልጆቹን እንደሚቆጣ ገልጸ ተለያዩ፡፡ አዛውንቱም እኔ አልዘክርም ወይ? ክርስቲያን አይደለሁም? ለምን ክብር ይለፈኝ ብለው እንደሚቆጩ ገልፀውልኛል፡፡

ስለዚህ ማህበረሰቡ ለተማሪዎች ልዩ አመለካከት ስላለው ልመናቸውን በበጎ ይቀበለዋል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነውም ተማሪዎችን ከሌሎች በልመና ከሚተዳደሩ ሰዎች ለይተው የሚመለከቱበት መንገድ ነው፡፡ ሌሎች ለማኞች ሲቆሙ «ለማኝ ቆሟል» ሲባል ተማሪ ለልመና ሲቆም ግን «ተማሪ ቆሟል» ነው የሚባለው በዚህም ተማሪዎች አጥተው ወይም መስራት ሳይችሉ ቀርተው ሳይሆን ለትምህርት ሲሉ የወጡ መሆናቸውን መረዳት ችለዋል ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል በማህበረሰቡ ተማሪ እግሩ እርጥብ ነው፤ ለምኖ የሚሰጡት ቁራሽ እንጀራም ረድኤት ይዞ ይመጣል ብለው ያምናሉ፡፡ ተማሪ «በእንተ ስመ ለማርያም» ብሎ ካልቆመም ቤታችን ረድኤት ይጎድለዋል፤ እኛም ቤታችን ላይ ተማሪ ካልቆመ ክርስቲያንነታችን አይታወቅም ብለው ስለሚያምኑ ለተማሪ መስጠትን እንደ ፅድቅ መንገድና እንደ ክርስቲያንነት ምልክት ይቆጥሩታል፡፡

4.3.4.2. አሉታዊ አመለካከት

በሌላ በኩል ተማሪ ለልመና በሚሄድበት ጊዜ ሲለምን ቢሰጡትም እንኳን ልመናውን በፀጋ የሚቀበሉበት መንገድ ግን ከላይ ከተነሳው ይለያል፡፡ በዚህ ወገን የሚመደቡት የህብረተሰብ ክፍሎች ተማሪ ሲለምን የሚሰጡት ከፍርሃት የተነሳ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ተንኮለኛ፤ ድግምትና ጥንቆላ የሚያደርሱ ተደርገው ስለሚቆጠሩ ነው ለምነው አጥተው ቢመለሱ በልጆቻችን ላይ «ምናምን ነገር» ያደርሱባቸዋል ከሚል እምነት የተነሳ ሳይሰጡ አይመልሷቸውም፡፡ ተማሪዎች በማህበረሰቡ ዘንድ አዋቂዎች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ በተለይም የቅኔ ተማሪዎች ተንኮለኛና ክፉ ነገር አድራጊ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ስለዚህ እነዚህን ተማሪዎች ሲለምኑ እምቢ ማለት በእራሳቸው ላይ ተንኮል እንዲያስቡ ማነሳሳት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ «በቤታችን እንደርብ ያወርዳሉ፤ በልጆቻችን ላይ የ‹ፊስ›››ይደግሙባቸዋል ብለው ስለሚያምኑ ከፍርሃት የተነሳ ተማሪዎች ለልመና ሲወጡ በጥንቃቄ ተንከባክበው ይመልሷቸዋል፡፡ ግንቦት 11 ቀን 2003ዓ.ም ከወይዘሮ ሽታዬ ደለለ ጋር በተደረገ ውይይት መረዳት እንደተቻለው ተማሪ ሲለምን አንገታቸውን ወጣ አድርገው አይተው ትላልቅና የቅኔ ተማሪዎች መሆናቸውን ከተረዱ በምንም መንገድ ሳይሰጡ አይመልሷቸውም፡፡ «የበሰለ ነገር ባይኖር እንኳ ጥሬም ቢሆን አፍሰን እንሰጣቸዋለን፡፡ ምጣድም አልጣድን ብንላቸው ተንኮል ያስቡብናል» በማለት ፍርሀታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ይህ አመለካከት በሌላ መልኩ ሲታይ የተማሪዎችን አዋቂነትና ከማህበረሰቡ የተሻለ ሁሉንም ነገር የማድረግ ችሎታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቅኔ ተማሪዎች ከሌሎች በተለየ ይፈራሉ፡፡ ምክንያቱም የቅኔ ተማሪ ከአገር

አገር ተንከራትቶ ብዙ ነገር ያውቃል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው በዚህም በማህበረሰቡ ያላቸውን ደረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ከእነሱ በተሻለ ብዙ ነገር የማድረግ ችሎታ አላቸው ብለው ያምናሉ፡፡

ተማሪዎችን የሚፈሯቸው ከልመና ጋር በተያያዘ ብቻም አይደለም። በአካባቢው ለሚከሰቱ ተፈጥሮአዊ ክስተቶችም ተጠያቂ ያደርጓቸዋል። በዚህ አመለካከታቸውም ተማሪዎችን ከሌላው ማህበረሰብ ነጥለው አዋቂነታቸውን አምነው ተቀብለዋል ማለት ይቻላል፡፡ ከሌላው ህዝብ በተለየ ብዙ ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ታምኖባቸዋል፡፡ከዚህ ፍራቻቸው የተነሳም ተማሪዎች ዝናብ ያቆማሉ፣ በረዶ ያወርዳሉ ወዘተ በማለት በእለት ከእለት ህይወታቸው ለሚፈጠረው ክስተት ሁሉ ተጠያቂ ያደርጓቸዋል፡፡ መሪጌታ አብዩ ጊዮን የሰጡትን ሀሳብ ማቅረቡ ሀሳቡን የበለጠ ያጠናክረዋል፡፡

> *ይገርማል እኮ እናንተ ጋተጎን ሳለሁ ዘጠኝ ደብር አገር ወረዳ አስተዳደር መጥቶ ከሰኛል፡፡ ሲከሱኝም የሚያስተምሯቸው ተማሪዎች በእድሜ ከእሳቸው በላይ ናቸው እንፈራቸዋለን ጠጉር ልውጥ ናቸው ከሸዋ፣ ከጎንደር ከወሎ ሁሉ የመጡ ናቸው፡፡ ቋንቋቸውም ልዩ ነው ከእኛ ጋር አይገጥምም ካስተማሩም የእኛን አካባቢ ብቻ ያስተምሩ ብለው ነበር እነሱ ከመጡ ጀምሮ ድርቅ ነው በረዶም የእኛን ጎጥ ብቻ ነጥሎ ይመታል ብለው አቤት አሉ፡፡ ከሌላ አካባቢ የወረዳው ሀላፊም ይህ ክስተት የተፈጥሮ እንጂ የተማሪዎች አይደለም፡፡ ከሌላ አካባቢ የወረዳው ሀላፊም ይህ ክስተት የተፈጥሮ እንጂ የተማሪዎች አይደለም፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ላሉትም መንግስት የሚለው ያልተማረ ይማር የተማረ ያስተምር ነው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ናቸው ብለው መለሷቸው ከዚህ በኋላ ወደ አካባቢያቸው ተመልሰው በክላሽ ነው የምንፈጃችሁ ብለው ስላስፈራሯቸው የኔታ እንግዲህ ከምንሞት እንሂድ እንጂ ብለው ብዙ ተማሪዎች ተበተኑ (ቃለ መጠይቅ፡ አብዩ ጊዮን ግንቦት 9 -2003ዓ.ም)*

በዚህ አኩርፈውም መምህሩ በአሁኑ ጊዜ በፍኖተሰላም ባታ ደብር በመቃብር ቤት እያስተማሩ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን በማህበረሰቡ ሁለት አይነት አመለካከት ስላለ ግማሹ ሰው ከሳሽ የመሆኑን ያህል ሌላው ህዝብ ደግሞ ጥለውን ስለሄዱ ረድኤት ራቀን፣ ለምን ጥለውን ሄዱ? በማለት በወረዳው ቤተክህነት ሀላፊዎች አማላጅነት መምህሩንና ተማሪዎችን እየለመኗቸው ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ በአካባቢው ስለልመናም ሆነ ስለተማሪዎች ያለው አመለካከት ሁለት አይነት ነው፡፡ በአንድ በኩል ተማሪዎችን ፍፁም የረድኤትና የዕድቅ ምልክት ሲያደርጓቸው በተቃራኒው ደግሞ ተንኮለኛና መጥፎ ነገሮችን ሁሉ የሚፈፅሙ አድርገው አሊያም የተፈጥሮ ስርዓትን ሁሉ የሚያዛቡ አድረገው ይቆጥሯቸዋል፡፡

### 4.4. መረዳዳት

በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ መረዳዳትና መተጋገዝ የተለመዱ ክንውኖች ናቸው፡፡ በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ሁሉም ነገር የጋራ ነው የግል የሚባል ንብረት የለም፡፡ ምንም እንኳን እያንዳንዱ ተማሪ የራሱ ጎጆ ቢኖረውም የሚኖሩት፣ የሚመገቡትና የሚለምኑት በጋራ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም እርስ በእርስ መከባበር፣ ለእራስ ሳይሆን ለሌላ ቅድሚያ መስጠት በጉልህ የሚታዩባቸው ባህሪያት ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል ለአዲስ ተማሪ የሚደረግ አቀባበልና ለአካል ጉዳተኞች የሚደረግ እንክብካቤ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

#### 4.4.1. አዲስ ተማሪ አቀባበል

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከአንድ ጉባኤ ወደ ሌላ ጉባኤ ይዘዋወራሉ፡፡ ይህም በትምህርት ቤት ቆይታቸው አንዱ መገለጫቸው ነው ቀደም ሲል ‹‹ጉዞ›› በሚለው ርዕስ እንደተጠቀሰው ተማሪዎች አድካሚ የእግር ጉዞ በማድረግ ከትምህርት ቤት ትምህርት ቤት ይቀያይራሉ፡፡ ተማሪዎች አንዱን ጉባኤ ትተው ወደ ሌላው የሚሄዱባቸው ሁለት መንገዶች አሉ የመጀመሪያው አንዱን የትምህርት ደረጃ ጨርሰው ወደ ሌላው ሲተላለፉ የሚያደርጉት ጉዞ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ የትምህርት ደረጃ አንድ መምህር ብቻ ስለሚመደብ አንዱን የትምህርት ደረጃ የጨረሰ ተማሪ የግድ ጉባኤውን መልቀቅ ይኖርበታል፡፡ የንባብ ቤትን ትምህርት ያጠናቀቀ የዜማ መምህር ፍለጋ፣ የዜማን ትምህርት ያጠናቀቀ የቅኔ መምህር ፍለጋ ጉባኤ መቀየሩ የግድ ነው፡፡ ይህ ወቅት በተማሪዎች ህይወት ዘንድ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ ምክንያቱም ደረጃቸውን ከፍ የሚያደርጉበት ክንውን በመሆኑ ነው። የንባብ ቤት ትምህርቱን በአካባቢው በሚገኙ መምህራን እና ከቤተሰብ ጋር ሆኖ ሲማር የነበረ ተማሪ ወደ ዜማ ቤት ሲቀላቀልና እራሱን በእራሱ ማስተዳደር ሲጀምር ለእራሱ ያለው አመለካከት ይቀይራል፡፡

ሌላው ምክንያት ደግሞ ተማሪዎች በእራሳቸው የግል ምክንያት በአንድ የክፍል ደረጃ እያሉ ጉባኤ ሊቀይሩ ይችላሉ፡፡ አንድ ተማሪ ከዜማ ቤት ወደ ዜማ ቤት ወይም ከቅኔ ቤት ወደ ቅኔ ቤት እንደአስፈላጊነቱ ሊዘዋወር ይችላል፡፡ ከተማሪዎችና ከመምህራኑ በተገኘ መረጃ መሰረት ተማሪዎች ይህንን የጉባኤ ለውጥ በዋናነት ለተሻለ መምህር ፍለጋ ሲሉ የሚያደርጉት ነው፡፡ መምህሩ ተቆጣጥረው የማያስተምሩ ከሆኑ፣ የግላቸውን ጉዳይ የሚያስቀድሙ ከሆነ እና መምህሩ የእውቀት ማነስ ከታየባቸው በእነሱ አነጋገር መምህሩ ‹‹ቋጠሮ›› ከሆኑ ጉባኤውን ለቀው ይሄዳሉ፡፡ እንዲሁም ሁሉም አካባቢ እኩል ምርታማ

ላይሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ በአካባቢው ምግብ እንደልብ የማያገኙ ከሆነ አካባቢውን ይለውጣሉ፡፡ እንዲሁም በጉባኤው መጥፎ ነገሮችን ሰርተው በተማሪዎች ዘንድ የተጠሉ ከሆኑ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ማንንም ሳይሰናበቱ ይጠፋሉ፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ትምህርት ቤት የቀየረ ተማሪ በየደረሰበት ጉባኤ የሚደረግለት የአቀባበል ስርዓት አለ፡፡ ማንኛውም ተማሪ ወደ ጉባኤው ገብቶ ለመቀላቀል የሚያልፍባቸው መንገዶች አሉ፡፡ ወደ አዲስ ትምህርት ቤት የመጣ ተማሪ በመጀመሪያ ተማሪዎች በሚያዘወትሩበት አካባቢ በተለይም ቅኔ በሚቆጥሩበትና ዜማ በሚለማመዱበት አካባቢ ይቀመጥና ተማሪዎችን ይመለከታል፡፡ ለተማሪዎች ጎንበስ ብሎ ሰላምታ ይሰጥና ለትምህርት መምጣቱን ይገልፅላቸዋል፡፡ አያይዞም ከመምህሩ ጋር እንዲያገናኙት ይማፀናቸዋል፡፡ ተማሪዎችም ይሁንታቸውን ገልፀው ከቆጠራ መልስ ወይም ከዜማ ልምምድ መልስ ወደጎጇቸው ይዘውት ይሄዱና ከመካከላቸው አንዱ ተመርጦ አዲስ ተማሪ እንደመጣ ለመምህሩ ይገልፃል፡፡ መምህሩም ‹‹እስኪ ወዲህና በሉት›› ብለው አስጠርተው የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቁታል፡፡



ፎቶግራፍ 3፡- አዲስ የመጣ ተማሪ መምህሩ እንዲቀበሉት ሲጠይቅ

ነገር ግን ለጥያቄ ተጠራ ማለት በጉባኤው ተቀባይነት አገኘ ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ የሚወሰነውም መምህሩ ከሚጠይቁት ጥያቄ በኋላ ነው ። ተማሪውም በመምህሩ መጠራቱ ሲነገረው ‹‹ትዕምርተ መስቀል›› አጣፍቶ ለብሶ መምህሩን እጅ በመንሳት ፊት ለፊት ይቆማል፡፡

መምህሩም ከየት ሀገር እንደመጣ፣ የት የት እንደተማረ፣ ምን ሲማር እንደነበር፣ አንዱን የትምህርት ደረጃ ጨርሶ ወይስ የመምህር ለውጥ ፈልጎ መሆኑን ይጠይቁታል፡፡ ተማሪው አንድ የትምህርት ደረጃ ጨርሶ ወደ ሌላ ትምህርት ቤት መምጣቱን ከገለፀ ብዙም ችግር አይገጥመውም፡፡ ነገር ግን ባለበት የትምህርት ደረጃ የጉባኤ ለውጥ ከሆነ ያደረገው የመጣበትን ጉባኤ በምን እንደለቀቀ መስቀለኛ ጥያቄ ይጠየቃል፡፡ ያለፈውን ጉባኤ ለምን መቀየር እንደፈለገ አሳማኝ ምክንያት ካልተናገረ መምህሩ ላይቀበሉት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በመምህሩ ይሁንታን ከአገኘ ከተማሪዎች አንዱን ጠርተው «ወስዳችሁ እግሩን እጠቡት» ብለው ያዛሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አዲስ ተማሪን መቀበል እንደ ረድኤት ስለሚቆጠር ሁሉም ተማሪዎች እነሱ ጋር እንዲያርፍ ፍላጎት ያሳያሉ ብዙውን ጊዜ ግን መጀመሪያ ከሚዳ የመጡት ተማሪዎች ይቀበሉትና ወደ ጎጇቸው ይዘውት ይገባሉ፡፡

በተማሪዎች መንደር አዲስ ተማሪ የመጣበት ቀን ትልቅ የድግስና የመቀራረቢያ ቀን ነው፡፡ ሌሎች ተማሪዎችም ያላቸውን ነገር ይዘው ወዳረፈበት ጎጆ ይሄዳሉ፡፡ በእለቱ ጨዋታና ቀልድ ደርቶ ያመሻል፤ ከእንግዳው ተማሪ ጋር አብረው ያመሻሉ፡፡ የእንግዳነት ስሜት እንዳይሰማውም ገጠመኝ ካለው እንዲያወራ አልያም እነሱ እያወሩ እንዲጫወት ያበረታቱታል፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ የተማሪውን እግር አጥበው መተኛቸውን ለቀው ይሳድሩታል። እንግዳው ተማሪ በእድሜ ከተቀበለው ተማሪ ያነሰም እንኳን ቢሆን እግሬን ማጠብ አትችልም ብሎ መከልከል አይችልም ይህ በተማሪዎች ዘንድ ደንብ ነው፡፡ እየሱስ ክርስቶስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ዝቅ ብሎ እንዳጠበው ሁሉ ተማሪዎችም የአዲስ ተማሪዎችን እግር ሲያጥቡ የክብር ስሜት ይሰማቸዋል፡፡ ለማጠብ በመመረጣቸውም እራሳቸውን እንደ እድለኛ ይቆጥራሉ፡፡ በሁለተኛው ቀን ጀምሮ ተማሪው ጀማሪም ይሁን ነባር በጉባኤው የመገኘትና የመሳተፍ ግዴታ አለበት ለጀማሪ ተማሪ ተብሎ የሚዘጋጅ ሌላ ትምህርት አይኖርም። በጉባኤ ላይ የመገኘት ግዴታ ቢኖርበትም አካባቢውን በሚገባ እስከሚለምደው ግን ለልመና አይወጣም፡፡ የተቀበሉት ተማሪዎችም ሆኑ ሌሎች እየለመኑ ከሚያመጡት ይመግቡታል፡፡ እርሱም እቤት በሚውል ጊዜ ድርቆሽ እንጀራ በማሰጣጣት፣ ውሃ በመቅዳትና ጎጇቸውን በማፀዳዳት ሲያግዝ ይውላል፡፡ ተማሪው በደንብ አካባቢውን ተለማምዶ መንደር እንዲመደብለት እስካልጠየቀ ድረስ በእንክብካቤ ይዘውት ይቆያሉ፡፡

በዚህ ሁሉ ጊዜ ሌሎች በተመደቡበት መንደር አብሮ በመሄድና አጋዥ በመሆን ስፈሩን ይለማመዳል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ሲለምኑና ቁራሽ እንጀራ በሚቀበሉበት ጊዜ እሱ ውሻ


በመከላከል ያግዛል። ከዚህ ሁሉ በኋላ እንግዳነቱ ያበቃና እሱም ሌላ እንግዳ ተማሪ ተቀባይ ይሆናል፡፡

### 4.4.2. ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚደረግ እንክብካቤ

በቆሎ ትምህርት ቤቶች በሰው ሰራሽም ሆነ በተፈጥሮ አደጋ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎች በብዛት ይገኛሉ፡፡ ተማሪዎች ከገጠር ቤተሰብ የሚመጡ ስለሆኑ የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ ደግሞ ጋራ ወጥቶ ቁልቁለት ወርዶ አርሶ መኖር ስለሚያስቸግር ተምሮ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ሆኖ ለመኖር ሲሉ በብዛት ወደተማሪነት ይሰማራሉ፡፡ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንደሌሎች ተማሪዎች የተሻለ መምህር ፍለጋ ከአገር አገር አይዘዋወሩም። እነዚህ ተማሪዎችም አንድ ጊዜ በአረፉበት ጉባኤ ብዙ ስለሚቆዩና በጉባኤው በደንብ ስለሚታወቁ ብዙ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በጉባኤ ላይ ሲገኙ፣ በልመና ጊዜና በቤት ውስጥ ሁሉ ልዩ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል፡፡ አካል ጉዳተኝነታቸው ከባድ ከሆነ በቆዩበት ጊዜ ሁሉ ምግብ ለምኖ በማምጣትና ውሃ ከወንዝ በመቅዳት ያኖሯቸዋል፡፡ በአንፃሩ የአካል ጉዳተኝነታቸው ቀለል ያለ ከሆነና ተማሪዎች «በእንተ ስመ ለማርያም›› ብለን ለምነን መኖር እንፈልጋለን ካሉ በመንደር ድልድል ጊዜ ቅርብ ያሉ መንደሮች ያለ እጣ ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ እነሱም እራሳቸውን በእራሳቸው ያስተዳድራሉ የጥገኝነት ስሜት እንዳይሰማቸውም በጋራ ርብርብ ጎጆ ይቀለስላቸዋል፡፡

አንዳንድ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ሳንለምን መማር ተገቢ አይደለም ብለው ስለሚያምኑ ሁሉም ተማሪ ከልመና ከተመለሰ በኋላ አኮፋዳቸውንና መቋሚያቸውን በመያዝ በእንተ ስመ ለማርያም በማለት የተማሪዎችን ጎጆዎች ይለምናሉ፡፡ በጉባኤው የሚገኙትን ጎጆዎች እንደ አንድ መንደር በመቁጠር ይለምናሉ፡፡ በዚህ ተግባራቸውም ልመና በእነሱ ህይወት ውስጥ ትልቅ ቦታ እንደሚሰጠው ያሳያል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በመንደር ተዟዙረው መለመን እንደማይችሉ ቢያውቁም የራሳቸውን ዘዴ ፈጥረው በልመና አንደሚኖሩ እና ተማሪነታቸውን እየገለጹ እንደሆነ እራሳቸውን ማሳመን ችለዋል፡፡ በእነሱ እምነት በእንተ ስመ ለማርያም ብለው ካልኖሩ ተማሪነታቸው አይታወቅም፡፡ ስለዚህ እራሳቸውን እንደተማሪ ለመቁጠር ልመና አንዱ መገለጫ በመሆን ያገለግላል፡፡ በዚህ መንገድም ይኖራሉ፡፡ በደንቡ መሰረት የለመኑበትን ጎጆ አመስግነው ተለማኝ ተማሪዎችም በር ላይ በመቆም ምርቃታቸውን ተቀብለው ይለያያሉ፡፡ ይህንን የሚያደርጉት የአካል

ጉዳተኝነታቸው የከፋ ከሆነና መንደር ሄደው የማይለምኑ ሲሆኑ ነገር ግን የማርያምን ስም ጠርቼ መለመን አለብኝ ብለው ሲያስቸግሩ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ልመናን እንዳ የህይወታቸው ክፍል አድርገው ይቆጥሩታል። እነዚህ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የቱንም ያህል ጉዳተኛ ቢሆኑ በተማሪዎች እገዛ በጉባኤዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ በጉባኤው ላይም ለእነሱ የሚመች ቦታ በማዘጋጀትና ቦታ በመልቀቅ እንክብካቤ ያደርጉላቸዋል፡፡



ፎቶግራፍ 4፡- ማየት የተሳነው ተማሪ በማታ ጉባኤ ላይ እንክብካቤ ሲደረግለት

## 4.5. ትምህርትና ወቅት

በቆሎ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ ውስጥ ሁለት ወቅቶች የአመቱ የትምህርት ወቅቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በእነዚህ ወቅቶች ተማሪ ከጉባኤ ወጥቶ ወደሌላ ቦታ አይንቀሳቀስም፡፡

### 4.5.1. ክረምት

በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ዋና የትምህርት ወቅት ተደርጎ የሚወሰደው የክረምት ወቅት ነው፡፡ ከአመቱ አራት ወቅቶች መካከል ክረምት ተማሪዎች ሀሳባቸውን ሁሉ ሰብስበው ለትምህርት እራሳቸውን የሚያዘጋጁበት ጊዜ ነው፡፡ ከተማሪዎች በተገኘ መረጃ መሰረት ክረምት ለትምህርት ዋና ወቅት ተደርጎ የተመረጠበት ምክንያት ከተፈጥሮ ክስተት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ የንባብ ቤትን ያለፈ ተማሪ የአስተሳሰብ ነፃነት ተሰጥቶት በእራሱ አዲስ ፈጠራ እየታገዘ ትምህርቱን ይቀጥላል፡፡ አዲስ ነገር ለመፍጠር

ደግሞ የተፈጥሮ ክስተቶችን እንደ ግብዓት መጠቀም የተለመደ ነው፡፡ ክረምት ከሌሎች ወቅቶች በተለየ መልኩ ብዙ ነገሮች የሚከሰቱበትና የሚለዋወጡበት ጊዜ ነው፡፡ የነገሮቹ መለዋወጥና በነበሩበት አለመቆየታቸው ለዜማና ለቅኔ ተማሪዎች የፈጠራ ልምምድ ትልቅ ድርሻ ይጫወታል፡፡

ከተማሪዎች በተገኘ መረጃ መሰረት ከመስከረም 26 እስከ ታህሳስ 25 ያለው ወቅት ‹‹መጸው››፣ ከታህሳስ 26 እስከ መጋቢት 25 ያለው ወቅት ‹‹ሀጋይ››፣ ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 ያለው ወቅት ‹‹ፀደይ››፣ ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ያለው ወቅት ደግሞ ክረምት በመባል ይከፋፈላል፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ወቅቶች በተለየ በክረምት ደመና በሰማይ ላይ የሚያንዣብብበት፣ ጉም ወርዶ ወርዶ የሚረገረግበት፣ መብረቅና ነጎድጓድ ከወዲያ ወዲህ የሚሰማበት፣ ወንዞች ሞልተው ከልካቸው በላይ የሚፈሱበት፣ ዝናብ ያለማቋረጥ የሚዘንብበት ጊዜ ነው። በአጠቃላይ መሬቱ በልምላሜ የሚሞላበትና ለአይን የሚያታክቱ ተፈጥሯዊ ክስተቶች የሚቀያየሩበት ወቅት ነው፡፡ የቅኔም ሆነ የዜማ ተማሪዎች በዚህ ተፈጥሯዊ ክስተት ታግዘው አዲስ ነገር ይፈጥራሉ፡፡ የዜማ ተማሪ ከንፋሱ ሽውታ፣ ወንዞች ሲሞሉ ከሚያሰሙት ድምፅ፣ ከዛፎቹ እንቅስቃሴ ዜማውን ያዋህዳል፣ ይለማመዳል፡፡ የቅኔ ተማሪም አይኑን እስከሚታክተው ከሚመለከተው ነገር በመነሳት አዲስ ቅኔ ይፈጥራል፡፡ በአጠቃላይ የክረምቱ ወቅት ይዞት በሚመጣ ክስተት ምክንያት ለፈጠራ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ስለሆነም በዚህ ወቅት ተማሪ ከቦታ ቦታ አይንቀሳቀስም፡፡ ከጉባኤ ወጥቶ ወደ ሌላ ጉባኤ አይዞርም ከዚህ ይልቅስ ሙሉ ትኩረቱን ለትምህርት ብቻ ያውላል፡፡

ከዚህ በመነሳትም ተማሪዎች ፈጠራና ተፈጥሮ ግንኙነት እንዳላቸው ማሳየት ችለዋል፡፡ ምክንያቱም በሌሎች ወቅቶች በአብዛኛው ፀሐይ ጥዋት ወጥታ ማታ ትጠልቃለች፡፡ እንደ ክረምት ነገሮቹ ወዲያው ወዲያው አይለዋወጡም፡፡ ስለዚህ ክረምትን ለትምህርት ትልቅ ወቅት አድርገው መምረጣቸው ለፈጠራቸው ግብዓት የሚሆኑ ነገሮችን ከተፈጥሮ ክስተት እንደሚያገኙ ቀድመው ማወቅ በመቻላቸው ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ክረምት ለትምህርት የሚመረጥበት ሌላው ምክንያት ከላይ እንደተገለፀው በክረምት ወንዞች ይሞላሉ፣ መንገድ ሁሉ በጭቃ ይዋጣል፣ በሰላም የተሻገሩት ወንዝ ሲመለሱ ሞልቶ ሊጠብቅ ይችላል፡፡ እነዚህ ሁሉ ክስተቶች ተማሪዎች ከቦታ ቦታ እንዲዟዟሩ ወይም መምህር እንዲያማርጡ አያስችሏቸውም። ስለሆነም በዚህ ወቅት በጋ ላይ ለክረምት ብለው ያዘጋጁትን ድርቆሽ በመያዝ ባሉበት ጉባኤ ይቆያሉ፡፡



ፎቶግራፍ 5፦ ለክረምት መክረሚያ በበጋ የተሰበሰበ ድርቆሽ

### 4.5.2. አብይ ፆም

ሌላውና ሁለተኛው ወቅት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ «አብይ ፆም» ተብሎ የሚታወቀው ጊዜ ነው፡፡ ይህ የፆም ወቅት በአማካይ ወደ ሁለት ወር የሚወስድ የፆም ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ጉባኤዎች ከሌላው ጊዜ በተለየ መልኩ በተማሪዎች ይሞላሉ፡፡ እንደ ዋና የትምህርት ወቅትም በጉጉት ይጠበቃል፡፡ ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው ተማሪዎች በፆምና በፀሎት እየታገዝን ሃሳባችንን ሰብስበን ስንማር ትምህርት ይሰምርልናል ብለው ስለሚያምኑ በዚህ ምክንያት ይህ የፆም ወቅት ሊመረጥ ችሏል፡፡ ስለዚህ በፆም ወቅት ከቦታ ቦታ መዞርና የእግር መንገድ መሄድ አይፈቀድም፡፡ ሌላው ምክንያት በአብይ ፆም ጊዜ በሀይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ምንም አይነት ተዝካርና ሰርግ አይዘጋጅም፡፡ ይህ አለመደረጉ ደግሞ ተማሪዎች ድግስ ፍለጋ ከቦታ ቦታ እንዳይዞሩና ሀሳባቸውን ሰብስበው ለመማር ይጠቅማቸዋል፡፡ ምክንያቱም ሰርግ ወይም ተዝካር አለበት በተባለ አካባቢ መምህራኖቹ በጥሪ ተማሪዎች ደግሞ በእራሳቸው ጥረት ለልመና ስለሚሄዱ በጉባኤዎች ላይ የመገኘት እድላቸው ይጠባል፡፡ ስለሆነም በፆም ወቅት መምህራኖች ብዙ ቦታ ስለማይሄዱ ተማሪዎች እንደልብ አግኝተው የሚፈልጉትን መማር ይችላሉ፡፡ ከዚህ ባለፊም በጾም ጊዜ በሚካሄድ ቅዳሴ የዜማ ተማሪ በአብይ ጾም ወቅት በሚፈጠር ቅኔ ደግሞ የቅኔ ተማሪዎች በተግባር ይማራሉ፡፡

## 4.7. እውቀትና ማህበራዊ ደረጃ

በቆሎ ተማሪዎች ህይወት ውስጥ ተማሪዎች የትምህርት ደረጃቸው ከፍ እያለ ሲሄድ በሚማሩበት ጉባኤም ሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያገኙት ክብር አብሮ ይጨምራል፡፡ የንባብ ቤትን አልፎ ወደ ዜማና ቅኔ ቤት የሚገባ ተማሪ ብዙ አዲስ ነገሮች ይገጥሙታል፡፡ በንባብ ቤት ያለ ተማሪ ፊደል ከመቁጠር ጀምሮ ዳዊት እስከመድገም ድረስ ይማራል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎች የተፃፉ ነገሮችን እንዲያነቡ ወይም በቃላቸው እንዲሸመድዱ ይደረጋል እንጂ አዲስ ነገር እንዲፈጥሩ አይደረግም፡፡ ከዚህ ይልቅስ ከእድሜያቸው ጋር በተያያዘ ግብረ ገብነት፣ ሰው ማክበር፣ ጥሩ ስነምግባር ወዘተ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ ከዚህ የክፍል ደረጃ ሲያልፉና ወደ ሌላ የትምህርት ደረጃ ሲሸጋገሩ እውቀታቸውም ስለሚጨምር ማህበረሰቡም ሆነ እራሳቸው ለእራሳቸው የሚሰጡት ቦታ ይለያል፡፡ ከዚህ ባለፈም በአንድ የትምህር ደረጃ ላይ ሆነውም የተሻለ እውቀት ያላቸው ተማሪዎች በጉባኤው አባላት ዘንድ ከፍ ያለ ቦታ ይሰጣቸዋል፡፡

በቅኔ ጉባኤ ውስጥ የተሻለ እውቀት ያለው ተማሪ ‹የኔታ› ተብሎ በመምህራኑ ስም መጠራት ይጀምራል፡፡ ይህ ከተማሪነት ስም ወጥቶ የኔታ መባሉ ትልቅ የደረጃ ለውጥ ነው፡፡ እድሜያቸው ምንም ይሁን ምን በጉባኤው ዘንድ በሚያሳዩት እውቀት ሁሉም ነገር ለእነሱ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡ በዜማም ሆነ በቅኔ ቤት ከሌሎች የተሻለ እውቀት ያላቸው ተማሪዎች መለመን ያቆሙና የሚያስቀጽሏቸው ተማሪዎች እየለመኑ ያኖሯቸዋል፡፡ መምህራኖቹን ተክተውም ጉባኤውን ያስተምራሉ አንተ መባል ይቀርና ‹‹አንቱ›› ይባላሉ፡፡ ከእውቀታቸው ጋር ተያይዘው የሚመጡ ብዙ ማዕረጎችንም ያገኛሉ፡፡



ፎቶግራፍ 7፡- በእውቀት የተሻለው ተማሪ በመምህሩ ቦታ ተተክቶ ተማሪዎችን ዜማ ሲያስቀጽል

## 4.6. አዲስ ነገር ፈጠራ

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የቅኔና የዜማ ተማሪዎች የተፃፈ ነገርን በማንበብ ወይም በመድገም ከመወሰን አልፈው የእራሳቸውን የመፍጠር ችሎታ ተጠቅመው አዲስ ነገር ይፈጥራሉ፡፡ የሀሳብ ነፃነትም ይሰጣቸዋል፡፡ አዲስ ነገር ለመፍጠርም ብዙ ጊዜ በተመስጦ ውስጥ ይሆናሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ የሚመርጡት ቦታ ከአካባቢው ርቆ በመሄድና ሰው የማይበዛበትን ቦታ በመምረጥ ወደ ጫካ ይገባሉ ብቻቸውን በመሆንም ወደ ውስጣቸው ይመለከታሉ፡፡ አዲስ ነገር ለመፍጠርም ሲወድቁና ሲነሱ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ዛፍ ላይ ይወጣሉ፤ ወደ ሰማይ ያንጋጥጣሉ፣ ተሸፋፍነው ይተኛሉ ወይም አንገታቸውን በጉልበታቸው ቀብረው ይቀመጣሉ፡፡ በአጠቃላይ እያንዳንዱ ተማሪ ለብቻው በመሆን በሀሳብ ከአካባቢው ግርግር በመራቅ ወደ ውስጡ ለመመልከት ጥረት ያደርጋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በየቀኑ የሚደረግ ክስተት ነው። የቅኔ ተማሪ በጥዋት ታሪክ ይነገረዋል፤ የተነገረውን ታሪክ መሰረት አድርጎም ቅኔ ቆጥሮ እንዲመጣ ይጠበቃል፡፡ የፈጠረውን ቅኔም ለመምህሩ ነግሮ ማሳረም ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ ይህንን ቅኔ ለመፍጠር ለብቻው በመሆን ብቻውን ሲያወራ፣ እጁን ሲያወናጭፍ ወይም አንድ ቦታ ላይ አይኑን ተክሎ በሀሳብ ተውጦ ማየት የተለመደ ክስተት ነው፡፡ ምክንያቱም የተነገረውን ታሪክ ከሁኔታው ጋር አዛምዶ የእራሱን ቅኔ መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡ የዜማ ተማሪም ራቅ ወዳለ ቦታ በመሄድ ሲጮህ፣ ሲያንጎራጉር፣ የሚያለቅስ ሲመስል በአጠቃላይ ድምፁን ለመግራትና ዜማውን በሚገባ ለማዜም ያለማቋረጥ ብቻውን በመሆን ሲለማመድ ይታያል፡፡ አልገራ ያለ ድምፁን የሚገራው፣ የዜማ አወራረዱን ልክ የሚያመጣው ብቻውን በመሆንና ያለማቋረጥ በመለማመድ ነው፡፡ ዜማ የሚጠናው በጩኸት ነው አንዴ ወደላይ አንዴ ወደታች እየወረደ ያስቸገረው ድምፁን ለመግራት ብቻውን በመሆንና በስሜት በመመስጥ ይለማመዳል፡፡



ፎቶግራፍ 6፡- ተማሪው ጭር ወዳለ ቦታ ሄዶ በመመስጥ ቅኔ ሲቆጥር

ከዚህ ባለፈም በእውቀታቸው መሰረት ከመምህሮቻቸው ጋር ይቀመጣሉ፣ የቅርብ አማካሪ ይሆናሉ በተለያዩ ግብዣዎች ላይም በልመና ሳይሆን ከመምህራቸው ጋር በክብር ይገኛሉ፡፡ የተማሪነት ህይወትን እየተዉ ወደ መምህርነት ይሸጋገራሉ። በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ እውቀትና በጉባኤው ውስጥ የሚሰጥ ክብርና ማዕረግ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ከዚህ በኋላ እነዚህ ተማሪዎች ከሚማሩበት ጉባኤ አልፈው በማህበረሰቡ ዘንድ ‹‹የየኔታ እገሌ ተከታይ›› እየተባሉ የሚሰጣቸው ደረጃም ይጨምራል፡፡ ከእውቀታቸው ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ የሚጣልባቸው ግዴታም ይኖራል፡፡ የማህበረሰቡን ወግና ባህል ማወቅና መጠበቅ ይጠበቅባቸዋል። በተለያዩ ጥሪዎች (ግብዣዎች) ጊዜም ምንም አይነት ስህተት መስራት አይጠበቅባቸውም፡፡ ጠጥቶ መስከር ወዘተ የመሳሰሉት ነገሮች በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ቦታ ያሳድፉባቸዋል፡፡

እንዲሁም እውቀታቸው እየጨመረ ሲሄድ ለእራሳቸው የሚሰጡት ግምትም ይጨምራል፡፡ የቅኔ ተማሪ ያለማንም እገዛ መፅሐፍትን አንብቦ፣ ከሚሰማውና ከሚመለከተው ተነስቶ ችሎታውን በመጠቀም ቅኔ ይቆጥራል፡፡ ቅኔ ለመንገርም ሆነ ሲጠየቅ ለመመለስ ከፍተኛ በራስ መተማመን ይኖረዋል፡፡ ለመምህራቸው ቅኔ ለመንገር ይፈሩና ይንቀጠቀጡ የነበሩ ተማሪዎች እውቀታቸው እየጨመረ ሲሄድ ከመምህሩ ፊት ለፊት ቆመው መምህሩን ይሞግታሉ፣ ያላመኑበትን ነገርም አይቀበሉም፡፡ የተባለውን ተቀባይ ከመሆን አልፈው በተግባር የተደገፈ ትምህርት መማር ይጀምራሉ፡፡ በተነገራቸው ነገር ብቻ ሳይሆን የእራሳቸውን እውቀት መጠቀም ይጀምራሉ፡፡ ምክንያቱም የቅኔ ተማሪ የቋንቋውን ህግ ጠንቅቆ የሚያውቅ ነው ተብሎ ስለሚገመትና በቋንቋው ሀሳቡን መግለፅ ስለሚጠበቅበት ሁልጊዜ አዲስ ነገር ይፈጥራል፡፡ በቅኔ ቤት ማንም ተማሪ በሌላ ጊዜ የተባለን ቅኔ ማቅረብ ያስቀጣል፡፡ ስለዚህ ሁልጊዜ አዲስ ነገር እየፈጠሩ ነው የሚመጡት፡፡ በቅኔ ጉባኤ ውስጥ የተሻለ እውቀት ያለው ተማሪ ‹‹የማህበር ቅኔ›› የተባለውን ተማሪዎች ከመምህራቸው ውጪ እርስ በእርስ የሚማሩበትን ጉባኤ እንዲመራ ይመረጣል፡፡ ለዚህ ጉባኤ ብዙውን ጊዜ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኋላ ተማሪዎች ይሰበሰባሉ፡፡ በብዙዎቹ ጉባኤዎች ለዚህ አገልግሎት የሚውል ትልቅ ጎጆ ቤት ይሰራል፡፡ ልክ እንደ አዳራሽ የሚያገለግል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የቅኔ ችሎታ አለን የሚሉ ተማሪዎች ከጉባኤው መሃል እየተነሱ ቅኔ ይነግራሉ፡፡ ከሁሉም የተሻለ እውቀት አለው ተብሎ የተመረጠው ተማሪም ከጉባኤው መሃል ቁጭ ብሎ በተማሩት መሰረት ከፊደል ጀምሮ እስከ ሰምና ወርቅ

መገናኘት ቅኔ አድራጊ ተማሪውን ይከራከራል፡፡ በቅኔ አድራጊው እና በጉባኤው ተሳታፊ ተማሪዎች መካከል በመሆንም የሞቀ ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡



ፎቶግራፍ 8፡- ከግራወደቀኝ ሁለተኛው ቅኔ ተቀባይ ተማሪ ቅኔ አድራጊ ተማሪዎችን ሲከራከር

ሲከራከሩበት የነበረውን ጉዳይም በነጋታው ለመምህራቸው በመንገር ያሳርማሉ፡፡ ቅኔ ተናጋሪውም ሆነ ተቀባዩ የትኛው ትክክል እንደሆኑ የተነሳውን ክርክር አድምጠው መምህሩ እርማት ይሰጣሉ፡፡ ቅኔ ተቀባዩ በተከታታይ እየተሳሳተ ጉባኤውንም የሚያሳስት ከሆነ ይህ የአወያይነት ማዕረጉ ይነሳና ለሌላ በእውቀት ይሻላል ለተባለ ተማሪ ይሰጣል፡፡

የቅኔ ተማሪዎች ከዜማ ተማሪዎች በተለየ ምስጢር እንዲያገናዝቡ፣ ንግግራቸው ያማረና የሰመረ እንዲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ ይጠበቃል፡፡ ድንገት በተገኙበት ቦታ ሁሉ ቅኔ መናገር መቻል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ንግግራቸው ጠንከር ያለ እና ምስጢር አዘል መሆን ይኖርበታል፡፡ አንድ ተማሪ ከሰዎች ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ሁሉ ታይቶ ይህ ጠንካራ ተማሪ ነው ወይም ደካማ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ነገሮችን በዘዴና በጥንቃቄ የሚመለከትና ፈተናዎችን ማለፍ የሚችል መሆን ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህ ሁሉ ሀላፊነቶች ማህበረሰቡ አዋቂዎች ናቸው ብሎ ስለሚያምን የሚጥልባቸው ግዴታዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ የቅኔ ተማሪዎችን አዋቂዎች አድርገው ስለሚቆጥሯቸው ለሚፈጠርባቸው ችግር ሁሉ የመፍትሔ ሀሳብ እንዲሰጧቸው ያማክሯቸዋል፤ እንደ ሀይማኖት አባትም ይቆጥሯቸዋል፡፡ እያንዳንዱ ተማሪም አዋቂነቱንም ሆነ የተሰጠውን ክብር በተገኘበት ቦታ ሁሉ በተግባር ማሳየትና እራሱን ማስከበር ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ በጓደኞቹ ክብር ይሰጠዋል፡፡

በቤተክርስቲያንም ከሊቃውንት ጎን በመቀመጥ የተማሪነት ደረጃውን ከፍ ያደርጋል፡፡ በተገኘበት ቦታ ሁሉ ተፈጥሮን ተመልክቶ ወይም አዲስ ክስተት አይቶ ቅኔ ይፈጥራል፡፡ በዚህ እየተበረታታ አዋቂነቱ እየጨመረ ይሄዳል። በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ በእውቀት በልጦ መገኘት ምንጊዜም ቢሆን ከቀሪው ተማሪ በተለየ መልኩ ከፍ ብሎ መታየት ነው፡፡ ይህንን ሀሳብም የንባብ ተማሪዎች የሚያደርጉት የጥያቄና መልስ ውድድር የበለጠ ያሳያል፡፡ መሪጌታ ወንጌል እንዳለው ግንቦት 13-2003 እንደገለፁት አሁን እየቀረ መጥቷል እንጂ ቀደም ባለው ጊዜ በተለይም በንባብ ቤት ተማሪዎች ዘንድ እርስ በእርስ የተማሩትን ሲጠያየቁ አንደኛው ተማሪ ተጠይቆ የተማረውን አስታውሶ መመለስ ካልቻለ ጠያቂው ትከሻው ላይ በመቀመጥ እና ጆሮውን በመቆንጠጥ መልሱን እስከሚያገኝ ድረስ ‹‹በል መልሱን አምጣው›› እያለ ይጠይቀዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ተማሪው የተጠየቀውን ባለማወቁ ምክንያት እንደቅጣት የሚጣልበት ቢሆንም የንባብ ቤት ተማሪዎች ጀማሪዎችና በእድሜያቸውም ህፃናት ስለሆኑ ከዚህ ሁኔታ የሚማሩት ብዙ ነገር ይኖራል፡፡ ምክንያቱም ከሁኔታው መረዳት እንደሚቻለው በእውቀት በልጦ መገኘት አሸናፊነት ነው፡፡ ጠያቂው በእድሜም ሆነ በአካል ከተጠያቂው ያነሰ ቢሆንም ይህንን ማድረግ ይፈቀድለታል፡፡ ምክንያቱም በእውቀት በልጦ መገኘቱ ይህንን እንዲያደርግ አስችሎታልና ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ጀማሪዎች እንደመሆናቸው መጠን በእውቀት ከኋደኛ በታች መሆን በሌሎች ተረግጦ እና የበታች ሆኖ መኖር ማለት መሆኑን በውስጣቸው ይዘው ያድጋሉ፡፡ በእውቀትም በልጦ በሁሉም አሸናፊ ለመሆን የፉክክር መንፈስ ይዘው እንዲያድጉ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ እውቀት በጉባኤው ውስጥም ሆነ በቀሪው ማህበረሰብ ዘንድ አንድ ተማሪ ያለውን ቦታ ይቀይራል፡፡

## 4.8. የእርስ በእርስ መማማር

በእያንዳንዱ የቆሎ ትምህርት ቤት ጉባኤ ውስጥ የሚገኘው አንድ መምህር ብቻ ነው፡፡ አንድ መምህር ብቻ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ብዙውን ጊዜ በእውቀቱ የተሻለ ተማሪ እየተመረጠ የመምህሩን በመቀበል ለተማሪዎች ያስተላልፋል፡፡ መምህሩ በአቅም ደከም ያሉ ከሆኑም ተማሪውን እንደ ድምፅ ማጉያ ያጠቀሙበታል፡፡ የተመረጠው ተማሪም ያለመሰልቸት ከመምህሩ እየተቀበለ በከፍተኛ ጩኸት ለተማሪዎች ይነግራል፡፡ ከዚህ ችግር በመነሳት አንድ ተማሪ ሲማር ማለትም ዳዊት ሲደግም፣ ዜማ ሲያወርድ ወይም ቅኔ ሲነግርና ሲዘርፍ ሌሎች ቁጭ ብለው የመከታተል ግዴታ ይጣልባቸዋል፡፡ ይህንን የሚያደርጉት በእያንዳንዱ ጉባኤ ላይ ጀማሪዎችም ሆኑ ነባር ተማሪዎች በጋራ በመሆን

ነው፡፡ በቅኔ ቤት ቅኔ ዘራፊ የሆነ ተማሪ ቅኔ ‹‹ሀ›› ብሎ የሚጀምረው ተማሪ ቅኔ ሲነግር ቁጭ ብሎ ይከታተላል እንዲሁም በቅኔ አዋቂነቱ ‹‹አንቱ›› የተባለ ተማሪን ጀማሪ የቅኔ ተማሪን ቁጭ ብሎ ይመለከታል፡፡ በአጠቃላይ በተማሪዎች ዘንድ ማንም የማንን እውቀት መፍራት ወይም መናቅ አይፈቀድለትም፡፡ ማንም ከማን ይማራል የሚል መመሪያ አላቸው፡፡ አዋቂ ተማሪዎች የጀማሪ ተማሪዎችን ቁጭ ብለው መከታተላቸው በተማሪዎች ዘንድ ያለውን መከባበርና አለመናናቅ ያሳያል፡፡



ፎቶግራፍ 9፡- ነባር ተማሪዎች ቅኔ ሲነግሩ ጀማሪ ተማሪዎች ቁጭ ብለው ሲመለከቱ

በሌላ በኩል ሌሎች ሲማሩ ቀሪዎቹ ቁጭ ብለው በመከታተል ምልከታን እንደመማሪያ ዘዴ ይጠቀሙበታል፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ተማሪ ሲሳሳት ያለምንም መደበቅና መሸፋፈን ማንም ተማሪ ተነስቶ እርማት ይሰጣል፡፡ በዚህም እርስ በእርሳቸው እውቀታቸውን ሳይደብቁ እርስ በእርስ ያላቸውን የመተጋገዝ ስሜት መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ ምልከታ እውቀታቸውን ለማጠናከርና ተራቸው ደርሶ እነሱም ለብቻቸው እስከሚማሩ ያግዛቸዋል፡፡ አንድ ተማሪ በትምህርት እኩል ደረጃ ላይ ያለውን ተማሪ ሲመለከት በመንፈሳዊ ቅናት ተነሳስቶ እሱም ተራው ሲደርስ የተሻለ ሆኖ ለመገኘት ይጥራል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ተማሪ በእውቀት ከሱ በታች የሆኑትንና አልፎት የመጣን ትምህርት ሲመለከት ያለፈውን ለማስታወስና አዲስ ነገር ካለ ለመጨመር ያግዘዋል፡፡ እንዲሁም ጀማሪዎች ቁጭ ብለው የበላዮቻቸውን ሲመለከቱ ወደፊት ለሚደርሱበት ፍንጭ ያገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ለችግሩ መፍትሄ ብለው የሚጠቀሙበት ዘዴ እርስ በእርስ የመማማር ባህልን በመካከላቸው አዳብሯል፡፡

በአጠቃላይ በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ መምህሩ አንድ ብቻ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እርስ በእርስ ይማማራሉ መምህሩም ብዙውን ጊዜ ክርክር ይዘውበት ሲሄዱ እርማት ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል እንደተነገረው በማህይበር ቅኔ የተሻለ እውቀት ያለው ተማሪ በግዕዝ የሚነገረውን ቅኔ በአማርኛ እየፈታ ይነግራል፡፡ ቅኔ ተቀባዩ ቅኔውን እየተቀበለ ለጉባኤው ይነግራል፡፡ ሁሉም ተሳታፊ ይሆናል ያልገባውንም በቅኔ ተቀባዩ በኩል ይጠይቃል፤ ይከራከራሉ፡፡ ቅኔ ተናጋሪውን ምንም ያህል ሲሞግቱትና ሲከራከሩት ቢቆዩም መጨረሻ ላይ ግን ጉባኤው በጋራ ድምፅ ‹‹ይበልነው›› በማለት ያበረታቱታል፡፡ ጥሩ ነው በዚሁ ቀጥል እንደማለት የሚሰጥ ማበረታቻ ነው፡፡ ቅኔ ተናጋሪው ጥሩ ነገር ባያቀርብና ሲከራከሩት ቢቆዩም መጨረሻ ላይ ግን በማበረታታት ጉባኤው ይበተናል፡፡ በዚህም እርስ በእርስ ለመማማርና ለመተጋገዝ ያላቸውን ፍላጎት ማወቅ ይቻላል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

### 5. የቆሎ ተማሪ ተረቶች

በዚህ ምዕራፍ ‹‹የቆሎ ተማሪ ተረቶች›› ተብለው የቀረቡት ተረቶች የቆሎ ተማሪዎች በዋና ገፀባህሪይነት የተሳሉባቸው ተረቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ተረቶች መካከል ዘጠኙ በመስክ ስራ ጊዜ በቀጥታ የቆሎ ተማሪዎች ሲተርኳቸው የተሰበሰቡ ተረቶች ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ ማህበረሰቡ የቆሎ ተማሪ እንዲህ አደረገ እያለ የተረካቸው ተረቶች ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት የቆሎ ተማሪ ተረቶች የተባሉት በሁለት ምክንያት ነው፡፡ የመጀመሪያው ከአካባቢያዊ ስያሜ በመነሳት ነው ምክንያቱም ፊቃደ አዘዘ እንደሚለው ተረቶችን ስያሜ ከመስጠት በፊት ማህበረሰቡ የሚጠራበትን መንገድ ጠንቅቆ ማጤን ይገባል፡፡ (1991፡ 54) ስለሆነም እነዚህ ተረቶች በተማሪዎችም ሆነ በማህበረሰቡ ‹‹የተሜ ተረቶች (ቀልዶች)›› እየተባሉ ስለሚነገሩ ስያሜው ሊሰጥ ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ፊቃደ ኦክፒውህን ጠቅሶ እንደገለፀው በተረቶቹ ተደጋግመው የሚመጡ አብይ ገፀባህሪያት ለተረቶቹ ስያሜ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ በዚህ ምዕራፍ በቀረቡት ተረቶችም የቆሎ ተማሪዎች አብይ ገፀባህሪ ሆነው ስለተሳሉ የቆሎ ተማሪ ተረቶች ተብለው ሊጠኑ ችለዋል፡፡

በተጨማሪም በቆሎ ተማሪ ተረቶች ስር የተጠቃለሉ ተረቶች ይዘታቸውን መሰረት በማድረግ በተለያዩ ንዑስ ክፍሎች ተከፋፍለው ትንተና ተካሂዶባቸዋል፡፡ በንዑስ ርዕስ ለመከፋፈል እንደ መስፈርት የተወሰደውም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተረቶች የሚያስተላልፉት ይዘት ነው፡፡

#### 5.1. ትዝብትና ተቃውሞ ገላጭ ተረቶች

ተማሪዎች በተረቶች ተማሪነታቸውን ተጠቅመውና ማህበረሰቡ ለእነሱ የሚሰጠውን ግምት በመጠቀም በማህበረሰቡ ዘንድ የታዘቡትን ነገር ይገልፃሉ ተቃውሟቸውንም ያንፀባርቃሉ፡፡ በተረት አንድ ለብዙ ቀን ሲሄድ ውሎ ሲሄድ ያደረ ተማሪ በድንገት መንደር በማግኘቱ ተደስቶ ሆዱን በእጁ ደግፎ ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› ሲል ውሽማ ዘሎ ወደ ማጀት ሲደበቅ ያያል በተረት ሁለትም ባሏ አለመኖሩን እየጠበቀች ብቻዋን ሰርታ መብላት የለመደች ሴት ቂጣ ስትጠፈጥፍ ተማሪ በድንገት ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም›› ይላል፡፡

በተረት ሶስትም እንደዚሁ ተልባ የምትቆላለት ሴት የሚፈልግ ተማሪ ምጣድ የጣደች ሴት አግኝቶ ሲጠይቅ ውሽማ ዘሎ ሲደበቅ ያያል፡፡ በእነዚህ ሶስት ተረቶች ከህይወቱ ጋር

የተቆራኙ ጉዳዮችን ለመፈፀም ቢሄድም በማህበረሰቡ ዘንድ ጥሩ የማይባሉ ምግባሮችን ሴቶች ከባሎቻቸው ተደብቀው ሲፈፅሙ ያያል፡፡ ተረቶቹም የተዋቀሩት ይህንን ትዝብት ለማጋለጥ ይመስላል፡፡

ገና ከመነሻው በተረት አንድና በተረት ሶስት እንደተገለፀው ለምኖ የሚመለስ ተማሪን ብቻ ስላየ ውሽማ ዘሎ ይደበቃል፡፡ ተማሪም ይህንን ሲመለከት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የቆይታ ጊዜውን ማራዘም ይፈልጋል፡፡ ባል እስከሚመጣም ይጠብቃል፡፡ ማጋለጥ ባይፈልግ ኖሮ አይቶ እንዳላየ በሄደ ነበር፡፡ በተረት አንድ ሌትና ቀን ባዶ ሆዱን ሲጓዝ የነበረ ተማሪ ድንገት መንደር በማየቱ የለመለመው ተስፋ በሴትዮዋ እምቢታ ሲጨልምበት ወደ ሌላ ቤት እድሉን መሞከሩን ትቶ ባየው ነገር ስለተገረመ ባይሆን የእግር ውሃ እንድትሰጠው በመጠየቅ ቁጭ ይላል፡፡ በዚህ መሃል ምራቅ የሚያስውጥ የዶሮ ወጥ ሽታ ይሸተዋል፡፡ ሌላ ትዝብት ጨመረ ቁራሽ እንጀራ የለኝም ያለች ሴት ዶሮ ወጥ እየሰራች ነው ወይም ሰርታለች፡፡ ተማሪ የእግር ውሃ ብሎ የጠየቀው ጊዜውን ለማራዘም ብሎ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪ በሚሻገረው ወንዝ ሁሉ እግሩን ይታጠባል እንጂ የእግር ውሃ ለምኖ አይታጠብም፡፡ በሌላ በኩል ሆዱን በእጁ ደግፎ የያዘ ረሀብተኛ ሌላ እድል መሞከር እንጂ እግር መታጠብ ቅድሚያ የሚሰጠው ሁኔታ አይደለም፡፡ ነገር ግን ረሀቡን ችሎ የነገሩን መጨረሻ ማጋለጥ ፈልጓል፡፡ ሚስትም ከውሽማዋ ጋር ለመጻራት ቸኩላ በፍጥነት ስታቀርብለት ታጥቦ መነሳቱን ትቶ በመንገድ የወጋውን እሾህ በወረንጦ መልቀም ይጀምራል፡፡ እሾሁን አውጥቶ ሲጨርስም ቁስሉን የሚተኩስበት የዶሮ ስብ ይጠይቃል፡፡ እግረ መንገዱንም ዶሮ መታረዱን እንዳወቀ ገለፀ ማለት ነው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ጊዜውን ሲያራዝም ውሽማም እንደተደበቀ ባል በድንገት ከች ይላል፡፡ በተረት ሶስትም እንደዚሁ ተልባ ሊያስቆላ የሄደ ተማሪ የውሽማን መደበቅ አይቶ ተልባው እንዳይደፋ ሊከደን ሲል አላስከድንም በማለት ተፈናጥሮ እንዲደፋ ያደርጋል፡፡ በኋላም የማርያምን ስም የጠራሁበትን ጥ፬ አልሄድም በማለት ቁጭ ብሎ አቀርቅሮ ይለቅማል፡፡ በዚህ ጊዜ ባል ይመጣል ከተባለለት ጊዜ ቀድሞ ድንገት ከተፍ ይላል፡፡ እንዲሁም በተረት ሁለት ሴትዮዋ ተደብቃ ቂጣ ስትጠፈጥፍ ተማሪ ቆሞ እያለ ባል የረሳውን እቃ ለመውሰድ ይመጣል፡፡

በዚህ ጊዜ ሴቶች ባሎቻቸውን ለማታለል የሚፈጥሩት ዘዴ የባሰ ትዝብት ውስጥ ይጥላቸዋል፡፡ ነገር ግን እግር መንገዱን የሚፈጥሩት ዘዴ ለምስኪን ተማሪ ጥሩ ነገር ይዞ ይመጣል፡፡ ሴቶች በባሎቻቸው ላይ ከሰሩት ዝሙትና ስርቆት በተጨማሪ ባሎቻቸውን

ለማታለል የሚጠቀሙበት ዘዴ የባሰ ያስነውራቸዋል፡፡ የእነዚህን ሴቶች አይን አውጣነትም ይመሰክራል፡፡ በተረት አንድ እንደተገለፀው ባል የምን ዶሮ ወጥ ነው? ብሎ ሲጠይቃት መጀመሪያ ቁራሽ እንጀራ የለኝም ባለ አፏ ተማሪው አሳዝኗት የነፍሴ ይሆነኛል ብላ እንደሰራችለት ትገልፃለች፡፡ ባሏ ለተማሪ ያለውን አመለካከት በመጠቀምም ሀጢያቷን ለመሸፈን ትጥራለች፡፡ በተረት ሁለትም የተጠፈጠፈውን ቂጣ አይቶ የታዘበ ባል ይጠይቃል፡፡ እሷም ተማሪ ጋግሪልኝ ብሎ ለምኗት ለነፍሷ ስትል እንደጋገረችለት ትገልፃለች፡፡ በተረት ሶስትም ለውሽማ ብላ የጋገረችውን ቂጣ እና ውሽማ ያስቀመጠውን አሞሌ ጨው የማን እንደሆነ ቢጠይቃት የተማሪው መሆኑን ትገልፃለች፡፡ በሶስቱም ተረቶች ተማሪዎች የተጠቀሰውን ነገር ለማግኘት ምንም ያደረጉት ጥረት የለም፡፡ ነገር ግን ተማሪን መርዳትና ማገዝ የፅድቅ ምልክት ተደርጎ ስለሚወሰድ በዚህ ሰበብ ወንጀላቸውን ለመሸፈን ሲሉ የሚፈጥሩት መላ ማንነታቸውን ያጋልጣል፡፡ በፈፀሙት ሀጢያትና በፈጠሩት የውሸት መላ የእነዚህን ሚስቶች ዋሾነትና መልቲነት መታዘባቸውን በተረቶች ገልፀዋል፡፡ ተማሪዎችም ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው በእነሱ የተሳበበውን የውሸት ነገር መውሰድና ሴቶቹን መበቀል ይፈልጋሉ፡፡ በሌላ በኩል የወንዶቹን የዋህነት ምን ያህል እንደታዘቡ ይገልፃሉ፡፡ ምክንያቱም በሶስቱም ተረቶች ሚስቶቻቸው ከነፍስና ከፅድቅ ጋር አያይዘው ያቀረቡላቸውን ምክንያቶች ያለምንም ተቃውሞ ይቀበላሉ፡፡

በማህበረሰቡ ለተማሪ አንድ ነገር መፈፀም እንደፅድቅ ስለሚቆጠር ተማሪን እንደማምለጫ በመጠቀም ጥፋታቸውን ለጊዜውም ቢሆን መሸፈን ችለዋል፡፡ ነገር ግን ይህንን የታዘበና በሁኔታው የተናደደ ተማሪ ውሽማን ከተደበቀበት አውጥቶ እስከማጋለጥ የደረሰ ስራ ይሰራል፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች የውሽሞችን ስጋትና ፍርሃት በተረቶቻቸው አጋልጠዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪ ለደቂቃ ደጅ ላይ ብቻ ቆሞ የሚሄድ ነው፡፡ ወደቤት እንኳን አይገባም፡፡በተጨማሪም ቤት ውስጥ ያለው ሰው ባል ይሁን ውሽማ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ውሽማ በእራሱ ጊዜ ደንብሮ ዘሎ ሲደበቅ ተማሪ ያያል፡፡ ይህንን እንዲያደርግ የሚያስገድደውም ምናልባት ሳያውቀው በውስጡ ስለተማሪዎች ያለው አመለካከት ሊሆን ይችላል፡፡

ምክንያቱም ማህበረሰቡ ተማሪዎች ዝሙትን የሚወግዙ የነገ ሀይማኖት አባቶች አድርጎ ስለሚቆጥራቸው ከሌላው ሰው በተለየ መንገደኛ ተማሪን ስላዩ ብቻ ሊደነብሩ ችለዋል፡፡ በውስጣቸው ለተማሪዎች የሰጡት ግምት ተማሪዎች ገና «በእንተ ስመ ለማርያም›› ሲሉ ዘለው ወደ ማጀት እንዲደበቁ ያስገድዳቸዋል፡፡ እራሳቸው በሚፈጥሩት መደናገጥ ምንንም

ለማያውቁት ተማሪዎች ውሸማነታቸውን ይናገራሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ዝም ብሎ ለምኖ ይሄድ የነበረ ተማሪ ነገሩን ሌላ አቅጣጫ ያስይዛል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ሴቶች በተማሪዎች መምጣት ይጨነቃሉ ከውሸማ ጋር ያላቸውን ሰዓትም ያጣብባሉ፡፡ ለምን ተማሪዎችን አባረው ከውሸማቸው ጋር የስርቆት ፍቅራቸውን አይከመኩሙም? ብንል ሁለት ምክንያቶች እናገኛለን፡፡ በዚህም የሴቶች ሁለት ፈላጊነትና መጥፎ ባህርይ ጎልቶ ይታያል፡፡ በሶስቱም ተረቶች ሴቶች ከባሎቻቸው ተደብቀው የሚሰሩት ዝሙትና ስርቆት ቢሆንም ተማሪዎች ያሉትን በመፈፀም ደግሞ ፅድቅን ማግኘት ይፈልጋሉ፡፡ በዚህም ሁለቱንም ማስኬድ የፈለጉ ይመስላሉ፡፡ ይህ ባህሪያቸውም ሴቶቹን የበለጠ ትዝብት ውስጥ ይጥላቸዋል፡፡ ምክንያቱም በባል ላይ እየደረቡ ወይም ከባል ተደብቆ እየበሉ ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተናገድ ጽድቅን መመኘት አብረው የማይሄዱ ባህርያት በመሆናቸው ነው፡፡ እንዲሁም ተማሪዎችን በተጨነቀ መንፈስ የመቀበሉ ሁኔታ ከፍርሃት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተማሪን ማስቀየም ማለት በእነሱ ላይ ተንኮል እንዲያስብ ማነሳሳት ማለት ነው፡፡ በሶስቱም ተረቶች መግቢያ እንደተገለፀው ተማሪዎች ወደ ቤት የሚሄዱት ለተለያየ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ውሸሞች በድንጋጤ የሚፈጥሩት ሁኔታና ሴቶች በድንገት የመጡ ባሎቻቸውን ለማታለል የሚጠቀሙበት መላ ተማሪዎች ነገሩን በትኩረት እንዲከታተሉ ያነሳሳቸዋል፡፡

በተረቶቹ እንደተገለፀው ውሸሞች ባይደናገጡና ባሎች በድንገት ከተፍ ባይሉ ኖሮ በተረት አንድ የራበው ተማሪ ሌላ ፍለጋ ይሄድ ነበር፡፤ በተረት ሁለትም ያገኘውን ቁራሽ ይዞ ይመለስ ነበር፡፡ በተረት ሶስትም ተልባውን አስቆልቶና አመስግኖ በተመለሰ ነበር። ነገር ግን በወቅቱ በሚያዩት ነገር ተገርመው ቢያንስ ሴቶች ለመላ ባቀረቡት ምክንያት መሰረት የውሸማ የተባለን ነገር ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ይህንን የሚገልፅልንም የተረት ሶስት መዝጊያ ነው ተማሪዎች ነገሩን ሆን ብለው እዳላዘጋጁት ነገር ግን ይህንን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሰጣቸው በማሰብ ‹‹ባይሆን አሞሌውን ተወው›› ስትለው ‹‹እግዚአብሔር የሰጠኝን ለአንቺ አልሰጥም›› ይላታል፡፡ ያጋለጣት የጥፋቷ ብዛት እንደሆነም ይጠቁማል፡፡ ከዚህ ባለፈም በተረት አንድ እንደተገለፀው ደረቅ እንጀራ ተከልክሎ የነበረ ተማሪ ከባል ጋር በመሆን የዶሮ ወጥ ይበላል፡፡ ረሀቡን አስታግሶ የተሻለ ነገር በልቶ መሄድ ይችል ነበር ነገር ግን እስከ መጨረሻው በመሄድ ውሸማን ከተደበቀበት ያጋልጣል ሚስትንም ያዋርዳል፡፡

## 5.2. ማንነትን ገላጭ ተረቶች

በዚህ ስር የተጠቃለሉት አብዛኞቹ ተረቶች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተማሪዎችን ማንነት፣ ሰብዕና፣ ባህርይ እና አመለካከት የሚገልፁ ናቸው፡፡ የብዙዎቹ ተረቶች መቼትም በተማሪዎች የእለት ከእለት ህይወት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ተረቶቹ የሚጀምሩት ለልመና በወጣ ተማሪ፣ በጉዞ ላይ ባለ ተማሪ፣ የእግዚአብሔር እንግዳ ብሎ በሚያድር ተማሪ ወይም ደግሞ በጥናት ላይ ባለ ተማሪ ነው፡፡ ስለዚህ የተረቶቹም መቼት የተማሪዎችን ህይወት መሰረት ያደረጉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ስር የተጠቃለሉት አብዛኞቹ ተረቶች ብልጠት የሚታይባቸው ተረቶች ናቸው። በብዙዎቹ ተረቶች ማየት እንደተቻለው ተማሪዎች ሆን ብለው ተንኮል ባያስቡም ሌሎች ገፀባህሪያት በሚያመቻቹላቸው ሁኔታ በመጠቀም ያጡትን ሲያገኙ፣ ከገቡበት ፈተና በዘዴ ሲያመልጡና ሌሎችን በብልጠት ሲያሸንፉ ይታያል፡፡ በተረት አራት እንደተገለፀው ለልመና የወጣ ተማሪ የማይጠብቀው ጥያቄ ይገጥመዋል፡፡ ድንገት ሀገርህ የት ነው? የሚል ጥያቄ ይጠየቃል፡፡ እሱም ትክክለኛውን መልስ ከእነማይ ብሎ ይመልሳል በትክክል ያልሰማችው ጠያቂም ከሰማይ? ብላ ደግማ ትጠይቀዋለች። ተማሪም ምን ለማለት እንደፈለገች ለማወቅ ጓጉቶ ‹‹አዎ›› ይላታል፡፡ እሷም በሞት የተለዩ እናትና አባቷን አስታውሳ ደህና መሆናቸውን ከሰማይ የመጣውን ተማሪ ትጠይቃለች፡፡ ተሜም ብልጠቱን መጠቀም ይጀምርና ደህና ናቸው ግን ልብሳቸው አልቆ የሚለብሱት አጥተዋል በማለት ይመልሳል፡፡ በዚህ ጊዜ በሀዘኔታ የእሷንና የባሏን ልብስ ሰብስባ ሰማይ ላይ ላሉ ቤተሰቦችዋ እንዲያደርስላት ለተማሪ ትሰጣለች፡፡ ተማሪም ልብሱን በከረጢት ይዞ ውልቅ ይላል፡፡ ይህንን ሁሉ ስትነግረው የተናደደ ባልም በቅሎውን ጭኖ ተማሪውን ፍለጋ ሽምጥ ይጋልባል፡፡ ተሜም ብልሃቱን በመጠቀም ልብሱን ሊያስመልስ የመጣውን በማታለል በቅሎውንም ጨምሮ ባዶ እጁን ይመልሰዋል፡፡ ስሙን ሲጠይቀውም የአሁኑ ይባስ በማለት የፌዝ መልስ ይሰጠዋል፡፡

ተማሪዎች እነሱ ፈልገውና ሆን ብለው በሰዎች ላይ ተንኮል አይሰሩም እንጂ ነገሩ በእራሱ ጊዜ ሲመጣላቸው ብልጠታቸውን ከመጠቀምና ማንነታቸውን ከማሳወቅ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ በተረት አምስት እንደተገለፀው ተማሪ የእውቀት አባቱንም ቢሆን ከማታለል ወደ ኋላ አይልም፡፡ አብሮት ለግብዣ የሄደን ተማሪ ከውጭ አስቀምጦ ብቻውን ይበላ የነበረ ቄስ ድንገት ሳያስበው የተሰበሰበው ህዝብ በጠየቀው ጥያቄ መሰረት መልስ ፈልጎ ወደ ተማሪ ይመጣል፡፡ በሁኔታው ተናዶ የነበረ ተማሪም ሳያስበው እጁ ላይ ሲወድቅለት ብልጠቱን መጠቀም ይጀምራል፡፡

የተሳሳተ መልስ በመስጠት የእሱን አዋቂነትና የቂሱን አላዋቂነት ለማሳየት ያስባል፡፡ ቂሱም ተማሪው የሰጠውን የተሳሳተ መልስ በመያዝ ወደ ቤት ገብቶ በኩራት ይናገራል፡፡ በዚህ ጊዜ ተማሪው ኡ.ኡ ብሎ በመጮህ ቂሱ የተናገረው መልስ የተሳሳተ መሆኑን ገልጾ ትክክለኛውን መልስ ይናገራል፡፡ ከዚህ በኋላ ቂሱ የነበረው ክብር ተገፎና አፍሮ ያለ አጀቢ ወደ ቤቱ ይመለሳል፡፡ ተማሪም አዋቂነቱን አስመስክሮና ከቂስ በላይ መሆኑን አስታውቆ ይወጣል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ታላላቆቻቸውንም ቢሆን በመቃወም የእራሳቸውን ማንነት ከማሳወቅ ወደ ኋላ አይሉም፡፡ በተረቶቹ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው ተማሪዎች በጣም አጣብቂኝ ፈተና ውስጥ ቢገቡና ድንገት ሳያስቡት ትልቅ ስህተት ቢሰሩም በብልጠታቸው ከችግሩ ያመልጣሉ፡፡ ማምለጥ ብቻም ሳይሆን ሌሎችን ያጠቃሉ፡፡ የሚሰጡት መልስም ጥርጣሬ ውስጥ የሚያስገባ አይደለም፡፡ ይህንን የሚያረጋግጥልን በተረት ስድስትና በተረት ሰባት የተፈፀመው ሁኔታ ነው፡፡ በተረት ስድስት የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ያደረ ተማሪ ጎረቤት ግብዣ በተጠሩበት የሴትየዋን እግር ቆነጠጥሁ ብሎ የሰውየውን እግር ይቆነጥጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውየው ደንግጦ «ምነው ተሜ ስከርህ እንዴ?›› ብሎ ሲጠይቀው በቅፅበት የሰውየውን ጭን መቆንጠጡን ተገንዝቦ አፋጣኝ መልስ ይሰጣል፡፡ በፍጥነት ወደጆሮው ጠጋ ብሎ ‹‹ጠላው ጥሩ ነው ይደጋግሙ ብዬ ነው ጌታው›› ብሎ ከገባበት ስህተት ሰውየውንም በማታለል ያመልጣል፡፡ በተረት ሰባት የእግዚአብሔር እንግዳ ነኝ አሳድሩኝ ብሎ ከተጠጋበት ቤት ሴትዮዋን ከዚህ በፊት ለምዷት ኖሯል፡፡ ስለዚህ የለመደውን የሚያገኝበት መንገድ ሲያፈላልግ እሱን መሬት አስተኝተው ባልና ሚስት አልጋ ላይ ወጥተው ይተኛሉ፡፡ ተሜም ከጓዳ ያሉ ከብቶችን ፈትቶ በማስወጣት ባል ሊመልስ ሲሄድ እሱ የፍላጎቱን ያደርሳል፡፡ እዚህ ላይ የተጠቀመው ብልጠት እንዳለ ሆኖ እየደጋገመ ይህንን ሲያደርግ ነገሩ ያልገባው ባለቤት ከብቶቹን መመለስ ይሰለችና ሚስትን ይልካታል፡፡ ይህንን ያልተገነዘበ ተማሪም ሰው መውጣቱን አድምጦ ጠጋ ብሎ ሰውየውን በስህተት ይስመዋል፡፡ ሰውየውም ደንግጦ ምነው ተሜ? ቢለው ተማሪም ወዲያው የመፍጠር ችሎታውን ተጠቅሞ ‹‹ጌታው ደህና ይሁኑ እየነጋ ስለሆነ ልሰናበትዎ ነው›› ብሎ በለሊት ወጥቶ ጥርግ ይላል፡፡ ከገቡበት ስህተት የሚወጡበት መንገድ ብቻም ሳይሆን በፍጥነት የሚፈጥሩት መላ የተማሪዎችን ዘዴኛነትና አስተዋይት ያመላክታል፡፡

በተረት ስድስትና ሰባት እንደተገለፀው ተማሪው ስህተት ላይ የሚወድቀው ለወሲብ ባለው ፍላጎት ነው፡፡ ነገር ግን የተረቶቹ ዋና ይዘት ነገር ወሲብ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ምክንያቱም አንደኛ ተማሪ በማህበረሰቡ ዘንድ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ አይጠረጠርም፡፡

ይህም ይመስላል ስህተት እንኳን ሲሳራ ባሎች እንዳይጠረጥሩ ያደረጋቸው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ በቤተክርስቲያን ህግና ስርዓት መሰረት ጋብቻ ስለሚፈፅሙ ከዚህ አይነቱ ነገር ታቅበው ነው የሚኖሩት፡፡ ይህንን የፈፀመ ተማሪም ከአላማው እንደተደናቀፈ ይቆጠራል፡፡ እኩዮቻቸውንም እንኳን ሲያፌቅሩ በቁስና በሽማግሌ ማስጠየቅ እንጂ ተማሪ ከልጃገረድ ጋር ቆሞ ማውራትም ቢሆን አይፈቀድለትም፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ተረቶች ነገረ ወሲብ የመጣው ተማሪዎች የገቡበትን ትልቅ ፈተና ለመጠቆምና ከዚያ አጣብቂኝ እንዴት በዘዴ እንደወጡ አፅንኦት ለመስጠት ይመስላል፡፡ ስለሆነም የተረቶቹ ትኩረቱ የተማሪዎችን ዘዴኛነት ከማሳየት ላይ እንጂ የተማሪዎችን ዝሙት ፈፃሚነት ለመጠቆም አይመስልም፡፡

ተማሪዎች ዘዴኛ የመሆናቸውና ነገሮችን በጥልቀት የማየታቸው ችሎታ ከህይወታቸው ጋር የተቆራኘ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ካልተማረው ህብረተሰብ በተለየ መልኩ የማየት ችሎታ ስላላቸው እንጂ ይህንን የሚፈፅሙትና ከሌሎች በልጠው የሚገኙት በተዓምር አይደለም፡፡ ማህበረሰቡ እውቀታቸውን አይቶ ከሚጥልባቸው ግዴታዎች መካከልም ዘዴኛና አዋቂ መሆን እንዲሁም በፈተና አለመውደቅ ይጠቀሳሉ፡፡ ስለዚህ ብልጠታቸው ከትምህርት ቤት ህይወታቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ የተማሪዎች ብልጠትና ዘዴኛነት በሰዎች ላይ በሚያሳዩት የበላይነት ብቻ አያበቃም፡፡ በተረት ዘጠኝ እንደተገለፀው ከእንስሳት መካከል በብልጠቷ አቻ የላትም የምትባለዋ ጦጣንም በመብለጥ በገዛ እጇ አንገቷን እንድትቆርጥ ያደርጋታል፡፡ በተረት አስር እንደተገለፀው ተማሪዎች ማንነታቸውን ለመግለፅ ተማሪነታቸውን በተለያየ መልኩ ያነሳሉ፡፡ ተማሪን ለወሲብ ፈልጋ ስትጠይቀው የሚሰጣት መልስ ‹‹ተማሪ ነኝ›› የሚል ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪ መሆን በእራሱ ከዝሙት መራቅ ማለት መሆኑን በተዘዋዋሪ ይገልፃል፡፡ ሴትዮዋ በዚህ አላበቃ ብላ ፍላጎቷ ሲጨምር የተመለከተ ተማሪ ‹‹ሞቶብኛል›› ይላታል፡፡ እሷም ዘዴኛ ኖራለችና ‹‹እኔም የምለው ከሞተ አምጣና ቅበረው ነው›› ብላ ትመልስለታለች፡፡ እንዲህ ፈተና ውስጥ የገባ ተማሪም ቢሆን ስሜቱን በመቆጣጠር ማምለጥ እንደሚችል ተረቶች ያሳየሉ። ተማሪም ‹‹ቢቀበርም በሀገሩና በወጉ ነው›› በማለት የማያዳግም መልስ በመስጠት ከተጋረጠበት ፈተና በዘዴ ያመልጣል በዚህም እስከመጨረሻ ታግሎ የማሸነፍ ችሎታ እንዳላቸው ማሳየት ችለዋል፡፡

## 5.3. ያጡትን ማግኛ ተረቶች

የቆሎ ተማሪዎች የነፍሳቸውን እውነተኛ ጥሪ በማዳመጥ በተረቶቻቸው አማካኝነት ያጡትን ያገኛሉ፣ ፍላጎታቸውን ያሳካሉ፡፡ የቆሎ ተማሪዎች ተማሪ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ በማህበረሰቡ ከሚጣልባቸው ማዕቀብ ሰብረው ለመውጣት፣ ያጡትንና የሚፈልጉትን ለማግኘት ተረቶች እንደ ጀልባና መቅዘፊያ በመሆን ያሸጋግሯቸዋል፡፡ ከለመዱትና ከሚያሰለቻቸው ህይወት ለደቂቃም ቢሆን በተረቶቻቸው አማካኝት ይወጣሉ፡፡ በተረቶቻቸው ነውር የሚባል ነገርን ሲፈፅሙ፣ ታላቆቻቸውን ሳይቀር ሲተናኮሉ፣ የወንድ ሚስትን ሲያማግጡ ይታያል፡፡ በሌላ በኩል የለመኑትን ቁራሽ እንጀራና ጥሬ ቆርጥመው ከሚኖሩበት አለም ወጥተው የተሻለ በሚባል ህይወት ሲኖሩ ይታያል፡፡ እጅ የሚያስቆረጥም ዶሮ ወጥ ሲበሉ፣ ከረጢት ሙሉ ልብስ ሲያገኙ፣ ከባለትዳር ሴት ጋር ሲተኙ ይታያሉ፡፡ በዚህም ጊዜያዊ ደስታና እርካታ ያገኛሉ፡፡ ስሜታቸው ያመጣባቸውን ርሃብ፣ የወሲብ ፍላጎት ወዘተ በተረቶቻቸው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡ በተረት አስራ አንድ እንደተጠቀሰው ተማሪዎች በመንደሩ ቆንጆ የተባለች ባለትዳር ሴት እንዴት ለራሳቸው ማድረግ እንደሚችሉ ይወራረዳሉ፡፡ ሀሳባቸውንም ያሳካሉ፡፡ በተረት አስራ ሁለት እንደተገለፀው ባሏ ሳይኖር የለመዳትን ሴት ሲያማግጥ በድንገት ባሏ ሲደርስበት ባሏን በዘዴ አስወጥቶ ሌሊቱን ሙሉ አብሮ ያድራል፡፡ በተረት አስራ ሶስትም ለልመና የቆመ ተማሪ ነገሩን በመጠምዘዝ የወሲብ ፍላጎቱን ያሳያል፡፡ በተረቶቻቸው ፍላታቸውን ለማሳካት ሲሉ የማይደፈሩ ነገሮችን ሁሉ ይደፍራሉ፡፡ በተረት አስራ አራት እንደታየው የንስሀ አባቱን ሚስት ሳይቀር ይገናኛል፡፡ ሎሌ የጌታውን ሚስት እንደሚተናኮል ሁሉ፡፡

የቆሎ ተማሪዎች በተረቶቻቸው አማካይነት የማይደፈር ይደፍራሉ፣ አታድርጉ የተባሉትን ያደርጋሉ ይህንን በማድረግም ከጊዜያዊ ርሃብ፣ ጭንቀት፣ ስሜትና ፍላጎት ተላቀው እፎይታ ያገኛሉ፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ተማሪ እንኳን የባለትዳርን ሚስት መመኘትና ማግኘት ይቅርና ትምህርቱን ሳይጨርስ እኩያውንም ቢሆን መመኘት የሀጢያት ሀጢያት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ማህበረሰቡ የሚጣልባቸው ማዕቀብ ይበዛል፡፡ በተለይ መልካም ነገርን በመስራትና የሀይማኖት ህግጋትን በመጠበቅ ከቀሪው ካልተማረው ማህበረሰብ በበለጠ ከተማሪዎች ብዙ ነገር ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ ከዚህ ሀላፊነት ጋር የሚመጣን ማዕቀብ አፍርሰው ውስጣቸው የሚላቸውን ነገር መፈፀም አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች በእድሜያቸው በወጣትነት ደረጃ ላይ የሚገኙ ስለሆኑ ስሜታቸው ብዙ ነገር የሚጠይቅበት ደረጃ ነው፡፡ ይህንን የውስጣቸውን ስሜት ለማስታገስና ለመግታት

ከተረቶቻቸው የቀረበ ማንም የላቸውም፡፡ ስሜታቸውን አድምጠው የሚፈልጉትን ለማድረግ ቢነሱ ስርዓትን እንደመጣስ ይቆጠርባቸዋል፡፡ ስለዚህ በእውን ማድረግ ያልቻሉትን በተረቶቻቸው ይፈፅማሉ፡፡ ፍላጎታቸው እንዳለ ሆኖ ማድረግ አለመቻላቸውን በተረቶቻቸው ይገልጻሉ፡፡ ስርዓቱን በመቃወም እንደበቀልም ይመስላል በሁሉም ተረቶች ተማሪዎች ለወሲብ የሚመኟቸው ሴቶች እኩዮቻቸው ሳይሆኑ የባለትዳር ሚስቶችና በመንደሩ ቆንጆ የተባሉ ሴቶች ወዘተ ናቸው፡፡ አልፎም የሀይማኖቱ ስርዓት መሪ የሆኑትን የንስሀ አባትን ሚስት ሳይቀር በተረቶቻቸው ተመኝተው ይገኛሉ፡፡

ከዚህ ባለፈም ተማሪዎች ህይወታቸው በችግር የተሞላ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ በእለት ከእለት የተማሪነት ህይወታቸው ለማግኘት የማይችሏቸውን ነገሮች በተረቶቻቸው ያገኛሉ፡፡ ምክንያቱም በተረቶች እንደታየው እጅ የሚያስቀረጥም ዶሮ ወጥ ሲበሉ፣ አኮፋዳ ሙሉ ዳቦ ይዘው ሲመለሱ በማሳየት ጊዜያዊ ጥጋብና እርካታ ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ ተረቶቻቸው ሲራቡ ሆዳቸውን የሚሞሉባቸው፣ የፈለጉትን ነገር በፍጥነት የሚያገኙባቸው መሳሪያዎቻቸው ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እንደ አጠቃለይ በብዙዎቹ ተረቶች ተማሪዎች ያጡትን ነገር የሚገኙባቸው ተረቶች ይበዛሉ፡፡ በተረት አንድ በርሃብ ብዛት ሆዱን በእጁ ደግፎ ደረቅ እንጀራ የተከለከለ ተማሪ ዶሮ ወጥ በክብር ይበላል፡፡ በተረት ሁለትም አጋጣሚውን ተጠቅሞ አኮፋዳውን ሙሉ በትኩስ ዳቦ ሞልቶ ይመለሳል፡፡ በተረት ሶስትም ከረጢት ሙሉ ልብስ ተሸክሞ ይሄዳል፡፡ ተማሪ እንኳንስ በቅሎ ለእሾህና እንቅፋት መከላከያ የእግሩ ጫማ ማግኘት አይችልም፡፡ ነገር ግን በተረቱ በበቅሎ ላይ ሲቀብጥ ይታያል፡፡ እንዲሁም በተረት አምስት ከውጭ ተወርውሮ አጥቶት የነበረውን ክብር በብልጠቱ ምክንያት አግኝቶ ይመለሳል፡፡ ተማሪዎች በተረቶቻቸው ያጡትን ነገር እንደሚያገኙ ከሰለቻቸው አስቸጋሪ አለም እንደሚወጡ የበለጠ የሚገልፅልን ተረቶች የሚነገሩበት አውድ ነው፡፡

ብዙዎቹ ተረቶች የሚነገሩበት በተለይም ከርሃብ ጋር የተያያዙ ተረቶች የሚነገሩት ተማሪዎች የልመና ሰዓት ደርሶ ወደ ልመና ከመሄዳቸው በፊት ወይም ከልመና በቡድን ሲመለሱ ነው፡፡



ፎቶግራፍ 10፡- ተማሪዎች የልመና ሰዓት ከመድረሱ በፊት በጎጇቸው ዙሪያ ተሰብስበው ተረት ሲያወሩ

በምዕራፍ አራት እንደተገለፀው አንድም ቅኔ ቆጥረው እስከሚመለሱ ፆማቸውን ስለሚቆዩ በሌላ በኩል ከልመና መልስ በአኮፋዳቸው ሞልተው የያዙት ምግብ እየሸተታቸው ርሃባቸው ከመጠን ቢያልፍም በመንገድ ላይ ቀንሶ መብላት አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ይህንን ማድረግ እምነት እንደማጉደልና ድንግል ማርያምን እንደማሳዘን ስለሚቆጠር በምግቡ ሽታ የተቀሰቀሰ ርሃባቸውን የሚያስታግሱት በህብረት እያወሩ በሚመጡ ተረቶች ነው፡፡ ስለዚህ ለጊዜው መብላት የማይችሉት ሲሳይ ከሚፈጥርባቸው የምግብ ፍላጎት ለማምለጥ ተረቶቻቸውን እንደ አማራጭ ይጠቀማሉ፡፡ በተረቶቻቸው አማካኝነት በአኮፋዳቸው ከያዙት ነገር የተሻለ እየበሉ ይመለሳሉ፡፡ እንዲሁም የነገረ ወሲብ ተረቶቹን ብዙውን ጊዜ የሚተርኳቸው በማታ ሰዓት ነው፡፡ በእነሱ እኩያ ያሉ ነገር ግን ወደትምህርት ቤት ያልገቡ ወጣቶች በዚያ ሰዓት ከሚስቶቻቸው ጋር የሚኖሩትን ህይወት እያሰቡ እነሱም በተረቶቻቸው ፍላጎታቸውን ያስታግሳሉ፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

### 6. ማጠቃለያ

በኢትዮጵያ የቆሎ ተማሪዎች ታሪክ ብዙ ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም የእድሜውን ያህል ብዙ ጥናት አልተካሄደበትም፡፡ ከዚህ በመነሳትም በፍኖተሰላም አካባቢ የሚገኙ የቆሎ ተማሪዎች ህይወት ምን እንደሚመስል ለማሳየት ይህ ጥናት ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችም በመስክ ስራ ሂደት በምልከታና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው ገላጭና ትንታኔያዊ በሆነ መልኩ ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡

ጥናቱ እንደሚያሳየው የቆሎ ተማሪዎች ተለይተው የሚታወቁባቸው እና የእነሱ መገለጫዎች የሆኑ አያሌ የህይወት ተሞክሮዎች አሏቸው፡፡ ማንኛውም የቆሎ ተማሪ የንባብ ቤት ትምህርቱን ካጠናቀቀና ወደ ሌላ ደረጃ መሄድ ከፈለገ የግድ አድካሚና እልህ አስጨራሽ ጉዞ እንደሚያደርግ በጥናቱ ታይቷል፡፡ ይህንን የሚያደርገውም ከቤተሰብ ርቆ ሙሉ ሰዓቱን ለትምህርት ለማዋል በማሰብና ከቤተሰብ ጋር በምቾት እየተኖረ ትምህርት በቀላሉ አይገባም ብሎ ከማመን የተነሳ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ተማሪ ከቤተሰቦቹ ተነጥሎ ከሄደ በኋላ በመጀመሪያ የሚወስደው እርምጃ ቤተሰቦቹ ያወጡለትን ስም መቀየር ነው፡፡ ተማሪዎች ይህንን የሚያደርጉት ከቤተሰብ ለመደበቅ፣ እራሳቸውን ከመተት ለመከላከልና ከመጽሐፍ ቅዱስ በመነሳት አለማዊ ስማቸውን ከአለማዊ ህይወታቸው ጋር መተዋቸውን ለማመልከት እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በጥናቱ እንደተገለፀው በተማሪዎች የትምህርት ቤት ቆይታ ጊዜ ልመና ተለይተው የሚታወቁበት ተግባራቸው ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የተማሪዎች ልመና የራሱ የሆነ ደንብና ስርዓት አለው፡፡ ተማሪዎችም በልመና ጊዜ በሚያሳዩት ደንብና ስርዓት ከሌላው በልመና ከሚተዳደር ሰው ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ ስርዓታቸውም ከእምነትና ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ማህበረሰቡ ለልመና እና ለተማሪዎች ያለው አመለካከት ሁለት አይነት እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በአንድ በኩል ተማሪ ሲለምን መስጠት የፅድቅ ምልክት ሆኖ ተማሪዎች መለመናቸውም ለማህበረሰቡ የክርስቲያንነታቸው መገለጫ እንደሆኑ የሚያምኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ሲኖሩ በሌላ በኩል ደግሞ ለተማሪ መስጠት ከፍርሃት ጋር የተያያዘ እንጂ ተማሪዎች የፅድቅ ምልክቶች ሳይሆኑ ክፉ ነገር የሚደርጉና ሰይጣናዊ ስራ የሚሰሩ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡

በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ መከባበርና መደጋገፍ የተለመዱ የእለት ከእለት ተግባራቸው እንደሆኑ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከእነዚህም መካከል የአዲስ ተማሪ አቀባበል ስርዓትና ለአካል ጉዳተኞች የሚደረግ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ የመረዳዳት ባህላቸውን የሚያሳዩባቸው ክንውኖች ናቸው፡፡ ጥናቱ እንደሚያሳየው ተማሪዎች ምንም እንኳን አመቱን ሙሉ በትምህርት ላይ ያሉ ቢሆኑም በዓመቱ ውስጥ ክረምትና አብይ ፆም የተማሪዎች ዋና የትምህርት ወቅቶች ናቸው፡፡ ክረምት ሁሉም ነገር የሚቀያየርበትና አዳዲስ ነገሮች የሚታዩበት ወቅት ስለሆነ ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ተጠቅመው አዲስ ነገር ለመፍጠር እንደ ግብዓት እንደሚያገለግላቸው ጥናቱ ያሳያል፡፡ በዚህም ተማሪዎች ፈጠራንና ተፈጥሮን እንዴት እንደሚያገናኟቸው ማሳየት ችለዋል፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች በፆምና በፀሎት የታገዘ ትምህርት ውጤቱ ያማረ ይሆናል ብለው ስለሚያምኑ ሁለቱን ወር የፆም ጊዜ ሀሳባቸውን ሰብስበው የሚማሩበት ወቅት እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል፡፡

በጥናቱ እንደተገለፀው በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ከአንድ የትምህርት ደረጃ ወደ ሌላ የትምህርት ደረጃ መሸጋገር በተማሪዎች ማንነት ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣል፡፡ ይህ ሽግግርም በተማሪዎች ዘንድ ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው ነው፡፡ የንባብ ቤትን የጨረሰ ተማሪ ወደ ዜማ ቤት ሲቀላቀል ከአካባቢው ርቆ በመሄድ እየለመነ መኖር ይጠበቅበታል፡፡ የዜማ ቤትን አጠናቆ ወደ ቅኔ ቤት የገባ ተማሪም ከአነበበውና ከሰማው ነገር እንዲሁም ከተፈጥሮ ክስተት በመነሳት አዲስ ቅኔ መፍጠር ይጠበቅበታል፡፡

በአጠቃላይ ተማሪዎች እውቀታቸው እየጨመረ ሲሄድ በሚማሩበት ጉባኤ ውስጥ ያላቸው ቦታም ሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ይጨምራል፡፡ በጥናቱ እንደታየው ከተማሪዎች እውቀት መጨመር ጋር በተያያዘ ብዙ ኃላፊነቶች ይጣሉባቸዋል፡፡ ኃላፊነቱም መምህሩን ተክቶ እስከማስተማር ይደርሳል፡፡ እውቀትና ኃላፊነት በቆሎ ተማሪዎች ዘንድ ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች በእውቀት የተለያዩ ቢሆኑም ሳይናናቁ እርስ በእርስ ለመማማርና ለመተራረም የሚያደርጉት ጥረት ሁሉም ሰው የእራሱ የሆነ እውቀት አለው ብለው እንደሚያስቡ የሚያሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም የቆሎ ተማሪዎች በዋና ገፀባህርይነት የተሳሉባቸው ተረቶች ከቆሎ ተማሪዎች ህይወት ጋር የተገናኙና በቀጥታ ከህይወታቸው የተቀዱ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ተማሪዎች ማህበረሰቡ የሚጥልባቸውን ኃላፊነት ተጠቅመው በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታዘቧቸውን እንደ ዝሙት ያሉ መጥፎ ተግባሮች በተረቶቻቸው አማካኝነት

ትዝብታቸውን ገልፀዋል፡፡ አልፎም ይህንን ፈፃሚ ሰዎችን ያጋልጣሉ፡፡ በሌላ በኩል በተረቶቻቸው አማካኝነት ማንነታቸውን ያሳውቃሉ፡፡ ብልጦች፣ ዘዴኛና በፈተና የማይሸነፉ መሆናቸውን በተረቶቻቸው አማካኝነት ያፀድቃሉ፡፡ እንዲሁም ጥናቱ እንደሚያሳየው ተማሪዎች ተማሪ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ ያጧቸውን ነገሮችና የተከለከሉትን ነገር በመፈፀም ከነበሩበት አለም በመውጣት ጊዜያዊ እርካታ ያገኛሉ፡፡ በተረቶቻቸው አማካኝነት የተጣለባቸውን ገደብ አፈራርሰው በመውጣት በውኑ አለም መፈፀም የማይችሉትን ወይም የማይፈቀድላቸውን ተግባር ይፈፅማሉ፡፡ በአጠቃላይ የቆሎ ተማሪዎች ከሌላው ማህበረሰብ ተለይተው የሚታወቁባቸው ብዙ የህይወት መገለጫዎች እንዳሏቸው ጥናቱ አሳይቷል፡፡

## ዋቢ ጽሑፎች

ሀብተማርያም ወርቅነህ፣ *ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 1963 ዓ.ም፡፡

ምስጢረ ሰዋሰው፣ "ጥንታዊ የግእዝ ቋንቋ ትምህርት"፣ *ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ (ዲማጽ)*፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974ዓ.ም፡፡

በላይነህ ደሴ፣ "የቅኔ ቆጠራ፣ ነገራና ዘረፋ በተመረጡ የጎጃም ጉባኤዎች"፣ *ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ (ዲማጽ)*፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999ዓ.ም፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፣ *በይነ ዲስፕሊኒያዊ የሥነጽሑፍ ንባብ*፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 2001ዓ.ም፡፡

አምሃእየሱስ አሰፋ፣ "መንፈሳዊ ትምህርት ቤት (ቁስ ትምህርት ቤት) በኢትዮጵያ"፣ *ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ (ዲማጽ)*፣ ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት፣ 1994ዓ.ም፡፡

ኪዳነማርያም ጌታሁን፣ *ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ*፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1980ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ 2000ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1992ዓ.ም፡፡

ገዛኸኝ ጌታቸው፤ "የአብነት ትምህርት ቤቶች ለዘመናዊ ትምህት እድገትና ለሀገር አስተዳደር ያደረጉት አስተዋጽኦ"፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃና መምሪያ ባዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ፡ (አመተ ምህረት ያልተጠቀሰ)፡፡

ፈቃደ አዘዘ፤ *የስነ-ቃል መምሪያ፤* አዲስ አበባ፡ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡ 1991ዓ.ም፡፡

Alemayehu Moges. "The Traditional Church Education." Addis Ababa, Hile Selassie University, 1971.

Ben Amos, Dan. "Towards a Definition of Folklore in Context." Journal of American folklore, vol. 84,No.331,pp.3-15. http://www.Justor.org.1971.

Dorson, Richard M. (ed); *Folk and Folk Life.* USA: the University of Chicago Press LTD, 1772.

Enbakom Kalewod, Translated by Mengistu Lemma. *Traditional Ethiopian Education.* New York: Columbia University, 1970.

Finnegan, Ruth *Oral Tradition and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices.* London: Routledge, 1972.

Goldstein, Knneths, *A Guide for Field Workers in Folklore.* Pennsylvania: Folklore Associates inc, 1964.

Martha C. Sims, and Martine Stephens *Living Folklore: An Introduction to the study of people and their Tradition.* Ohio: Utah State University Press, 2005.

Georges, Robert A. and Jones Michael Owen. *Folkloristies: An introduction.* USA: Indiana University Press, 1995.

Moberg, David O. *The Church as a social Institution.* USA: Prentice-Hall Inc., 1972.

Oring, Elliot. "The interests of Identity." The Journal of American Folklore. Vol.107, No.424, pp.242-247, University of Illinois press. http://www.jstor org./stable/541202,1994.

Pankhurst, Richard. "Ethiopia". *Church, State, and Education in Africa.* Ed. Scanlon David G. New York: Teachers College Press, 1966.

Yehenew Jembere. "Ageneric Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M A Thesis, Addis Ababa University, 1996.

# አባሪ አንድ

## ተረት አንድ

አንድ የቆሎ ተማሪ ከአንድ መምህር ትምህርቱን ሲከታተል ቆይቶ ሌላ መምህር ፍለጋ ጉዞ ይጀምራል፡፡ ለሁለት ቀን ያህል ሰው በማይኖርበት በረሃ ሲጓዝ ውሎ በማደሩ በጣም ተርቦ ነበር፡፡ ሆዱን በእጁ ደግፎ ሲያዘግም በድንገት አንድ መንደር ላይ ይደርሳል፡፡ በጣም ተደስቶ በንተ ስመ ለማሪያም ብሎ ሲለምን አንድ ወንድ ተደናግጦ ወደ ማጀት ይገባል፡፡ ተሜም ይህን አይቶ እያለ ምራቅ የሚያስውጥ የዶሮ ወጥ ሽታ ያውደዋል፡፡ በኋላም ሴትየዋ ባዶ እጇን ወጥታ ምጣድ እንዳልጣደች ትነግረዋለች፡፡ ተሜም ወደ ማጀት የገባው ውሽማ መሆኑን ስለጠረጠረ ከሩቅ ሃገር ስለመጣና ስለደከመው ባይሆን የእግር ውሃ እንድትሰጠው በእመቤታችን ስም ይጠይቅና ቁጭ ይላል፡፡ እሷም ከውሽማዋ ጋር መጫወት ስለፈለገች ሳትጨቃጨቅ ውሃውን ታቀርብለታለች፡፡ ተሜም ታጥቦ ሲጨርስ ተነስቶ መሄዱን ትቶ በበርሃ ሲጓዝ የወጋውን እሾህ በወረንጦ ማውጣት ጀመረ፡፡ ሴትየዋም ባለመሄዱ ተናዳ ልታስነሳው ስትወጣ መርዛማ እሾህ ስለወጋው መተኮሻ የዶሮ ስብ ይጠይቃታል፡፡ ሴትየዋ ቶሎ ለማስነሳት የጠየቃትን ለመፈፀም ላይ ታች ስትል ባል ይመጣል ከተባለለት ሰዓት ቀድሞ ከች ይላል፡፡ ሴትየዋም የምትይዘው የምትጨብጠው ጠፍቷት ስትርበተበት የታመመ እግሩን እንዳንከረፈፈ ሰውየውን እጅ በመንሳት ሰላምታ ይሰጣል፡፡ ሰውየውም ተማሪውን ይዞ ወደቤት ይገባል፡፡ ሚስትም ለምን እኔ ሳልኖር ዶሮ ወጥ ሰራሽ እንዳትባል ተማሪው አሳዝኗትና ዝልፍልፍ ስላለባት ለነፍስ ይሆነኛል ብላ ለተማሪው መስራቷን ትገልፃለች፡፡ ተሜም ይህንን ሰምቶ ዝም ይላል፡፡ ተሜም ከእነሱ ጋር በመሆን ዶሮ ወጡን ልቅም አድርጎ ይበላል፡፡ ከበሉ በኋላ ሰውየውም ለእግዚአብሔር እንግዳው ጠላ እንድትቦጭለት ይጠይቃታል፡፡ እሷም ተማሪው ስላናደዳት ገንቦውን መሸከም እንደማይሆንላት ገልፃ ማንቆርቆሪያ ይዛ ወደ ጓዳ ትገባለች በዚህ ጊዜ ተሜ እያነከሰ ብድግ ብሎ እኔ እሸከመዋለሁ ብሎ ወደ ጓዳ ይገባል፡፡ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተነስ አሸክመኝ ይላል፡፡ ሰውየውም እኔን ነው? ብሎ ቢጠይቀው ኸረ እርስዎንም አይደል እዚህ ተቀምጦ ዝም አለኝ ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ ባለቤቱ ዘሎ ማጀት ሲገባ የተደበቀውን ሰው ያያል፡፡ ሁለቱ አንገት ለአንገት ሲያያዙ ተሜም ተነስቶ ውልቅ አለ ይባላል፡፡

ተረት ሁለት

በአንድ መንደር ውስጥ ባሏ ከስራ ከመምጣቱ በፊት ብቻዋን ሰርታ መብላት የለመደች ሴት ነበረች፡፡ ከእለታት በአንዱ ቀን እንደተለመደው ምጣድ ጥዳ ቂጣዋን ስጠፈጥፍ አንድ ተማሪ ‹‹በእንተ ስመ ለማሪያም›› ብሎ ቁራሽ እንጀራ ይለምናል በዚህ ጊዜ ባሏ የረሳውን እቃ ሊወስድ ድንገት ከተፍ ይላል፡፡ በሁኔታው ተገርሞ ምን እየሰራች እንደሆነ ሲጠይቃት ተማሪው ዱቄት አምጥቶ ጋግሪልኝ ስላላት የነፍስ ይሆነኛል ብዬ ነው የምለፋው ትለዋለች፡፡ ተሜም ነገሩን ይሰማና ዝም ይላል፡፡ ባለቤቱም ተማሪውን ገልመጥ አድርጎ ሊወጣ ሲል ተማሪው ጌታዬ ጭብጦዬን ሳያሰጡን እንዳይሄዱ ብሎ ይለምነዋል፡፡ ባለቤቱም እባክሽ ይህን ተማሪ ስጭና አሰናብችው ይላታል፡፡ እሷም ትኩስ ስለሆነ አኮፋዳውን እንዳያቃጥልበት ይብረድለት ብዬ ነው ብላ በል ወደስራህ ሂድ ትለዋለች፡፡ ሰውየውም ተሜ በል እስከሚበርድልህ ትንሽ ጠብቅ ብሎት መንገዱን ሲቀጥል ኡ.ኡ ብሎ ጭብጦዬን ሳያሰጡኝ ከሄዱ በእግዚአብሔር ስም እገዝትዎታለሁ ይለዋል፡፡ ሰውዬውም ሚስቱን ወዲያ ወርውሪለትና ይሂድ ጤነኛም አይመስለኝ ይላታል፡፡ ሚስትም በለፈለፈ አፉ ያለውዴታዋ በአኮፋዳው ጥቅጥቅ አድርጋ ትሞላለታለች፡፡ ተሜም ጭብጦውን ይዞ ዞር ብሎ ሳያይ ፈትለክ ይላል፡፡ እሷም ውሃ የምትቀዳ መስላ ተማሪውን ተከትላ ወጥታ እየተከተለች

ይነቅህ ስትለው ውሃ እጠጣለሁ
ይቁረጥህ ስትለው ግራዋ እጠጣለሁ
ከቤትህ አያድርስህ ስትለው በመንገድ አድራለሁ
ለእናትህ ልጅ አትሁን ስትለው ለአባቴ እሆናለሁ

እያለ በነገር እየሸነገለ ጥሏት ጥርግ አለ ይባላል፡፡

ተረት ሶስት

ከእለታት አንድ ቀን ተሜ በአኮፋዳው ተልባ ይዞ ከመንደር መንደር እየለመነ ተልባውን የምትቆላለት ምጣድ የጣደች ሴት ይፈልጋል፡፡ ድንገት ምጣድ የጣደች ሴት ያጋጥመውና ወደ ቤት ጠጋ ሲል አንድ ሰው ዘሎ ወደ ማጀት ሲገባ ይመለከታል፡፡ ተሜም እመይቴ እባክዎት አፀድቆዎታለሁ በጋለው ምጣድ ይቺን ተልባ ይቁሉልኝ ብሎ ይለምናል፡፡ ሴትየዋም መቁላት ስትጀምር ተልባው እየተፈናጠረ ሲደፋ ልትከድነው ሙግድ ስታነሳ ተሜ መዘግየት ስለፈለገ አይክደኑት የተደፋው ይደፋ ይላል፡፡ ተልባውም አብዛኛው እየተፈናጠረ ተደፍቶ አለቀ ፡፡እሷም ከመደፋት የተረፈውን አኮፋዳው ላይ በትና እንዲሄድ

ብትጠብቀው ተሜ የእመቤቴን ስም የጠራሁበትን ጥዬው አልሄድም በማለት አቀርቅሮ ይለቅማል፡፡

አቀርቅሮ ሲለቅም እደጠበቀው ባል ከች ይላል፡፡ አሞሌ ጨውና የዳቦ ክምር ስላስደነገጠው ይህ ሁሉ የማን ነው ብሎ ይጠያቃል፡፡ እሷም የተማሪው እንደሆነ ትናገራለች፡፡ ተሜም ይህንን እንደሰማ እመይቴ የነፍስ ዋጋ ያድርግልዎት ብሎ ዳቦውን በአኮፋዳው ጨምሮ አሞሌ ጨውን ሊያነሳ ሲል ያቅተዋል፡፡ እመይቴ ከደከሙት አይበልጥምና ያሽከሙኝ ይላል፡፡ እሷም በአይኗ ገላምጣው ወደ ማጀት ትገባለች፡፡ ባላየውም በይ አሸክሚውና ምርቃትሽን ጨርሺ ይላታል፡፡ እሳም ታሸከመውና ተከትላ ወጥታ ተሜ ዳቦውን ውሰደው ባይንሆ አሞሌውን ተወው ትለዋች እሱም እግዚአብሔር የሰጠኝን ለአንቺ አልሰጥም ይላታል፡፡

ተረት አራት

ከእለታት አንድ ቀን አንድ የቆሎ ተማሪ ለልመና ይወጣል፡፡ አንድ ቤት ደርሶም በእንተ ስመ ለማሪምያብሎ ሲለምን ባላቤቷ ቁራሽ እንጀራ በአኮፋዳው እየከተተች ተሜ ሀገርህ የት ነው? ስትለው እሱም ከእንማይ ይላታል፡፡ እሷም ከሰማይ? ብላ ትጠይቀዋለች ተሜም ምን ለማለት እንደፈለገች ለማወቅ ፈልጎ ነገሩን ገልበጥ አድርጎ አወን ይላታል፡፡ እሷም እናትና አባቷ ሞተው ስለነበር ተሜ እናትና አባቴን አግኝተሀቸዋል? ብላ ትጠይቀዋለች፡፡ ተሜም ደህና ናቸው ግን የሚለብሱት አልቆባቸው እየበረዳቸው ነው አላት፡፡ ምስኪኗ ሴትም በጣም እያዘነች የባሏን ልብስ ለአባቷ የእሷን ልብስ ለእናቷ በከረጢት ቋጥራ ሰጠችው፡፡ ተሜም ይህንን ተሸክሞ ውልቅ ይላል፡፡ ከቆይታ በኋላ ባሏ ከስራ ይመጣና ልብስ ሊቀይር ሲሞክር ልብሶቹን ያጣል፡፡ የት እንደደረሱ ሲጠይቃትም ሁኔታውን ሁሉ ትነግረዋች፡፡ ሰውየውም በሁኔታው ተናዶ በቅሎውን ጭኖ እየጋለበ ተማሪውን ፍለጋ ይሄዳል፡፡ ትንሽ ወረድ እንዳለም ተማሪውን ያገኘዋል፡፡ ተሜም ከሩቅ አይቶት ኖሮ ከረጢቱን ወደ ጥሻ ስር ይወረውርና መንገዱን ይቀጥላል፡፡ ሰውየውም ተሜ በዚህ በኩል አሁን አንድ ተማሪ ሲያልፍ አየህ ወይ ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ተማሪም አዎ ጌታዬ አሁን እየሮጠ አለፈ ነገር ግን ቁልቁለት ስለሆነ በቅሎዋን አያስሄድልዎትም ይላል፡፡ ሰውየውም እባክህ አንተ ጋር ትቆየኝ በእግሬ ለድረስበት ይለዋል። ተሜም እሽ ብሎበቅሎዋን ይቀበልና ስምህ ማን ሲባል የአሁኑ ይባስ በሎት በበቅሎላይ ተሞናሙኖ ሄደ ይባላል።

## ተረት አምስት

ከእለታት አንድ ቀን ተማሪና የሚማርበት ደብር ቄስ በአንድነት የሀዳር ሚካኤል ዝክር ይሄዳሉ፡፡ ዝክሩ ቦታ እንደደረሱም ቄሱ ተሜን በል ከእሱ ደጅ ላይ ተቀመጥ ብለውት ወደ ቤት ገቡ፡፡ ሲገቡም ለዝክር የመጣው ተነስቶ በክብር ተቀበላቸው። ቄሱም ወዲያው ዝክሩን አስጀመሩና ግብዣ በግብዣ ሆኑ፡፡ ተሜ ግን በኃላ ትርፍራፊ ይሰጠዋል ተብሎ ምንም ሳይሰጠው ቀረ፡፡ ቄሱም ስጡት ሳይሉ መምጣቱን ሁሉ እረስተው ተቀመጡ፡፡ የተሰበሰው ሰውም አባታችን የዛሬ ቀን ሚካኤል ምን የሆነበት ቀን ነው ብሎ ጠየቃቸው ቄሱም ታሪኩን ስለማያውቁት ቆይ ሽንት ልክፈል ብለው ወጥተው ተሜን ከደጅ አግኝተው ጠየቁት አንጀቱ እርር ያለው ተማሪም ዛሬ ሚካኤል የሞተበት ቀን ነው አላቸው፡፡ ቄሱም እንግዲህ ዛሬ የዘከርነው ሚካኤል የሞተበትን ቀን በማሰብ ነው ብለው ተናገሩ በዚህ ጊዜ ተማሪው እሪ ብሎ እየጮኸ ዛሬ ሚካኤል የሞተበት ቀን አይደለም ብሎ ታሪኩን ተናገረና በመጨረሻም መላዕክት ሞት የለባቸውም ብሎ ቄሱን አዋረዳቸው፡፡ ቄሱም ክብራቸውን ተገፈው ያለአጃቢ ተመለሱ ይባላል፡፡

## ተረት ስድስት

አንድ የቆሎ ተማሪ የለመዳት ሴት ነበረች፡፡ ባሏ በሌለ ቀን ማታ ማታ እየሄደ ያድር ኖሮ አንድ ቀን እንደለመደው ሲሄድ ባልየውን ቁጭ ብሎ ያገኘዋል፡፡ ተሜም የእግዚአብሔር እንግዳ አሳድሩኝ ብሎ ይለምናል፡፡ ማታውኑ ጎረቤት ግብዣ ይጠሩና ተሜን አብረው ይዘውት ይሄዳሉ አብረው እየተመገቡ እያለ የሴትየዋን እግር አገኘሁ ብሎ የሰውየውን እግር ይቆነጥጣል። በዚህ ጊዜ ምንው ተሜ ሰከርኽ እንዴ ብሎ ሲጠይቀው ወዲያው ነገሩን ይለውጥና ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ ጠላው ጥሩ ነው ይደጋግሙ ብዬ ነው አለው ይባላል፡፡

## ተረት ሰባት

ከእለታት አንድ ቀን የቆሎ ተማሪ ከአንድ መንደር ይጠጋና አሳድሩኝ ብሎ ይጠይቃል፡፡ ሴትየዋን ከዚያ ቀደም ለምዷት ኖሮ ባሏ ስላለ የሚደርገውን ያጣል፡፡ እነሱም አልጋ ላይ ተኝተው ተሜን መደብ ላይ ያስተኙታል፡፡ ተሜም መላ አገኘና ከጓዳ ያሉትን ከብቶች በሩን ከፍቶ ያስወጣቸዋል፡፡ ሰውየው ከብቶቹን ሊመልስ ሲወጣ ተማሪ ከሴትየዋ ጋር የልቡን ይፈፅማል፡፡ እየደጋገመ ይሄንን ሲያደርግ ሰውየው ይሰለችውና እስኪ አንቺ አስገቢያቸው በማለት ያዝዛታል፡፡ ተሜም ሴትየዋ መውጣቷን አላወቀ ኖሮ ሰውየው የወጣ

መስሎት ወደ አልጋው ይሄዳል ሰውየውንም ይስመዋል፡፡ ባለቤቱም ተደናግጦ ምነው ተሜ ቢለው ጌታው እየነጋ ስለሆነ ተሰናብቼዎት ልሂድ ብዬ ነው ብሎ በለሊት ወጥቶ ቀረ አሉ፡፡

ተረት ስምንት

ከእለታት አንድ ቀን የቆሎ ተማሪ የእግዜር እንግዳ ብሎ ወደ አንድ መንደር ጎራ ይላል እነሱም ቤት ለእግዚአብሔር ነው ግባ ብለው ይቀበሉታል፡፡ ነገር ግን እራታቸውን ዶሮ ወጥ ሰርተው ነበርና ተሜ እንዳይበላ ሰስተው ሽሮ ይሰሩና እንደምንም ቀማምሰው ይተኛሉ ተሜም ሽሮውን ይቀማምስና ይተኛል፡፡ ሰዎቹም አንድ ቀበኛ ጥጃ ስላለች ልብስህን እንዳትበላብህ ብለው ደህና ልምጭ ይሰጡትና በዚህ በላት ይሉታል፡፡ ተሜም የዶሮ ወጥ ሽታ እንቅልፍ ሲያሳጣው ከተኙ በኋላ ቀስ ብሎ ተነስቶ ሙልጭ አድርጎ ይበላና ተመልሶ ይተኛል፡፡ ባለቤቶችም ተሜ ተኝቷል ብለው ሲነሱ ድስቱ ባዶውን ቀርቷል በዚህ ጊዜ ሴትየዋ ቆይ ተሜ በልቶት ነው ብላ አፉን ለማሽተት ጎንበስ ስትል ጌታው አረ ያሏት ጥጃ መጣች በማለት ሴትየዋን በያዘው ልምጭ ለምጦ መለሳት ይባላል፡፡

ተረት ዘጠኝ

አንድ ተማሪ ቅኔ ለመቁጠር ሁልጊዜ የሚሄድበት ዘወር ያለ ስፍራ ነበር ነገር ግን ውሃ ለመጠጣት ወይም ሽንት ቤት ለመጠቀም ሲነሳ አንዷት ጦጣ ወረቀቱን እየቀዳደደች እሱ ሲያደርግ የተመለከተችውን ሁሉ ለማድረግ እያለች ትበጠብጠው ነበር። ይሄንን የተረዳ ተማሪ አንድ ቀን ካራ ይዞ ይመጣል ቁጭ ብሎ ይቆይና ውሃ ለመጠጣት እቃውን አስቀምጦ ሲሄድ ካራውን ያነሳና በደንደሱ በኩል አንገቱን የሚቆርጥ መስሎ ይገዘግዛል፡፡ ይህንን ስትመለከት የቆየች ጦጣም ካራውን ታነሳና በስለቱ በኩል የገዛ አንገቷን ቆርጣ እዚያው ላይ ሞታ አገኛት፡፡ ተማሪ ጦጣንም በለጠ ተብሎ ይወራል፡፡

ተረት አስር

ተማሪ መቼም በአካባቢው በሚገኝ ትምህርት ቤት የመማር ልምድ የለውምና ራቅ ወዳለ ቦታ ሲጓዝ ውሎ ሲመሽበት ወደ አንድ ቤት ጎራ በማለት የእግዚአብሔር እንግዳ ነኝ አሳድሩኝ ይላል፡፡ የቤቱ ባለቤትም ትንሽ ካቅማሙ በኋላ ግባ ቤት ለእንግዳ ይሉታል፡፡ እመቤቲቱ ወጣ ገባ ሲሉ ተሜን ቢመለከቱት አይን የሚስብ ሆኖ አገኙት፡፡ ልጃቸውን ጠርተው ማነሽ ለብ ያለ ውሃ ለተሜ አምጪለት ብለው አዘዙ ተሜም እግዚአብሔር

ይባርክልኝ ብሎ ቂምጣውን ከፍ አድርጎ መታጠብ ይጀምራል፡፡ ሴትየዋም ተሜን ትኩር ብለው ሲመለከቱት መንገዱ ቢያደክመውም ወዘናው ያማረ ሆኖ አገኙት። ሴትየዋም በል ና ከፍ ብለህ ተቀመጥ ብለው ሲንከባከቡት አመሹ ተሜም ግብዣውን ሲጨርስ የነፍስ ዋጋ ያድርግልኝ ብሎ እዛው ከተቀመጠበት ላይ ለመተኛት ዞር ሲል በተማሪው ቀልባቸው ያረፈው ሴትዮም በል ና እዚህ ከመደቡ ጋ ብለህ ተኛ በእኔ ልታስፈርድ ነው ብለው ይገስፁታል፡፡ ተሜም ከዚህ ውጪ አልንቀሳቀስም ብሎ እምቢ ይላል። ሆኖም ሴትየዋ ጠጋ ብላ እንደማባበል ሲቃጣቸው ተሜ ነገሩ ገባውና እመይቴ አይሆንም አይሆንም እንዲያውም ሞቶብኛል ደግሞም ተማሪ ነኝ ይላቸዋል ሴትየዋም በቀላል የሚሸነፉ አልነበሩምና ሞቶብኛል ሲላት እኔስ ምን አልኩ አምጣና ቅበረው ነው ያልኩህ ትለዋለች፡፡ የሴትየዋ አይንአውጣነት እያስገረመው እመይቴ ቢቀበርም የሚቀበረው በሀገሩ በወጉና በደንቡ መሰረት ነው ብሎ አሳፈራት ይባላል፡፡

ተረት አስራ አንድ

ሁለት የቆሎ ተማሪዎች አንዲት ቆንጆ ሴት ይወዱና እንዴት እንደሚያገኟት ግራ ይጋባሉ፡፡ ከመካከላቸው አንደኛው ተማሪ እኔ ይችን ሴት ማግኘት አያቅተኝም ይላል፡፡ ሌላው ተማሪም አንተ ይቺን ሴት ከተገናኘሀት እኔ ጥላዬን እሰጣለሁ ብሎ በጥላ ተወራርደው ይሄዳሉ፡፡ እንደደረሱም የእግዚአብሔር እንግዳ ብለው ለምነው ሰዎች ይቀበሏቸዋል፡፡ እራት በልተው እንደተኙም ያ ተማሪ አይኔን አመመኝ ብሎ መጮህ ይጀምራል፡፡ ሰዎቹም ተደናግጠው ምን ይሻልሀል ቢሉት እናቴ አይኔ ላይ ጡቷን ስታፈስብኝ ይሻለኝ ነበር ይላል፡፡ ባልም ፈጣሪ ምኑን ጉድ አመጣብን ብሎ ሚስቱን ሂጂና እስኪ አፍስሺበት ለነፍስ ይሆነናል ይላታል፡፡ እሷም እሺ ብላ ተነስታ ጡቷን ልታፈስ ስትጠጋ ተማሪ ቆይ እዚህ ላይ ነው ብሎ ጡቷን ይይዛል፡፡ ብልቱንም ያስጨብጣታል ከዚያም ግንኙነት ይፈፅማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስት የጩኸት ድምፅ ታሰማለች ባልም ምን እንደሆነች ቢጠይቃት እውነትም ቅል አክሎ አይኑ አብጧል እያለች ሲደጋግሙ አደሩ ይባላል፡፡ ጥላው የተወሰደበት ተማሪም የተማሪው ስም አስመስሎ ወይኔ ጥላዬ እያለ ሲጮህ አደረ፡፡

ተረት አስራ ሁለት

አንድ የቆሎ ተማሪ ባሏ ሳይኖር እየሄደ የለመዳት ሴት ነበረች፡፡ አንድ ቀን አብረው እየቀበጡ እያለ ባል በድንገት ይመጣል፡፡ ተሜም ዘሎ ቆጥ ላይ ይወጣል፡፡ ባልና ሚስት

አብረው እንደተቀመጡም ከላይ ሆኖ ዱባ እየወረወረ ባልየውን ነጥሎ ይማታ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስት የላይኛው ጌታ በዱባ ተማታ ትላለች፡፡ ባልም ነገሩ አልቆም ሲል ከጌታ የመጣ ቅጣት መስሎት እስኪ ቤቱን ለቅቄ ልውጣ ብሎ ጎረቤት ያድራል፡፡ ተሜም ከቆጥ ወርዶ ያቋረጠውን ቀጠለ ይባላል፡፡

## ተረት አስራ ሶስት

ከእለታት አንድ ቀን ተሜ ለልመና ይሄድና አንድ ቤት ሲደርስ በእንተ ስመ ለማርያም ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ ሴትየዋ ትወጣና ተሜ እቤት ውስጥ ምንም ነገር የለም ቁጭ ብዬ ብቻ ነው ያለው ቁጭ ብዬ ልስጥህ ትለዋች ቁጭ ብዬ የእህል አይነት ነው፡፡ ተሜም እመይቴ ካሉስ ተኝተው ቢሰጡኝ ይሻለኛል አለ ይባላል፡፡

## ተረት አስራ አራት

አንድ የንስሀ አባቱን ሚስት እሁድ እሁድ እየጠበቀ የለመደ ተማሪ ነበር፡፡ የንስሀ አባቱ እሁድ እሁድ በተስኪያን ቀርተው አያውቁም ተሜም እሁድን እየጠበቀ የልቡን ያደርሳል። አንድ ቀን ሰውየው ከመንገድ የሀመም ስሜት ተሰምቷቸው ይመለሳሉ፡፡ እነተሜም ሳያስቡት ሲደርሱባቸው ደንግጠው ተማሪ አልጋ ስር ይገባል፡፡ ባልና ሚስትም ገንፎ አገንፍተው ሲበሉ ሚስት ለአዋዩ እያለች ወደ አልጋ ስር ትወረውራለች፡፡ በዚህ ጊዜ የወረወረችው ትኩስ ገንፎ ተማሪው መቀመጫ ላይ ይለጠፋል፡፡ ትኩስ ገንፎ ያቃጠለው ተማሪም አልጋውን ከነሰውየው ገልብጦ ወጥቶ ይሮጣል፡፡ ሚስትም በስመ አም በሉ መምህሬ ሰይጣን እኮነው አለች ይባላል፡፡

## አባሪ ሁለት

### የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

#### አውራ መረጃ አቀባዮች

| ስም | ጾታ | እድሜ | ሙያ | መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ | መረጃው የተሰበሰበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| መሪጌታ አብዩ ጊዮን | ወ | 76 | ከ1958ዓ.ም ጀምሮ ለ46 ዓመታት የቅኔ መምህር | ፍኖተሰላም ባታ ደብር | ግንቦት 6 እና 9፣ 2003ዓ.ም |
| መሪጌታ ሀይማኖት ዓለሙ | ወ | 59 | ከ1980ዓ.ም ጀምሮ ለ24 ዓመታት የዜማ መምህር | ባከል ገብርኤል | ግንቦት 12፣ 2003ዓ.ም |
| መሪጌታ ወንጌል እንዳለው | ወ | 63 | ከ1974ዓ.ም ጀምሮ ለ30 ዓመታት የድጓ መምህር | የባዲ ሚካኤል | ግንቦት 13 እና ሰኔ 15፣ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ አምሃ በድሉ | ወ | 31 | የቅኔ ተማሪ | ፍኖተሰላም ባታ ደብር | ሰኔ 18፣ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ለይከማርያም እንተነህ | ወ | 24 | የቅኔ ተማሪ | የልምዳር አቦ | ሰኔ 19፣ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ሙሴ ተሻገር | ወ | 27 | የዜማ ተማሪ (ለመምህርነት የደረሰ) | ባከል ገብርኤል | ሚያዚያ 29፣ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ጥዑመልሳን እሸቱ[1] | ወ | 23 | የቅኔ ተማሪ | የልምዳር አቦ | ግንቦት 5፣ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ልጃለም ደግፌኝ | ወ | 13 | የዳዊት ተማሪ | የባዲ ሚካኤል | ሚያዚያ 30፣ 2003ዓ.ም |
| ወ/ሮ ሽታዬ ደለለ | ሴ | 75 | የቤት እመቤት | ቦንጊት ማርያም | ግንቦት 11 እና ሰኔ 20፣ 2003ዓ.ም |
| አባ አያሌው አለሙ | ወ | 93 | አርሶአደር እና የሀገር ሽማግሌ | ባከል ገብርኤል | ሰኔ 22፣ 2003ዓ.ም |

[1] ይህ ተማሪ እድሜው ትንሽ ቢሆንም አሁን ባለበት ጉባኤ የተሻለ የቅኔ ችሎታ አለው የሚባል ተማሪ ነው

ንዑስ መረጃ አቀባዮች

| ስም | ጾታ | እድሜ | ሙያ | መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ | መረጃው የተሰበሰበበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| መሪጌታ አእምሮ ብርሃኑ | ወ | 47 | ከ1989ዓ.ም ጀምሮ ለ15 ዓመታት የቅኔ መምህር | የልምዳር አቦ | ሰኔ 18፡ 2003ዓ.ም |
| መላዕከ ሠላም ኤፍሬም ሙሉአለም | ወ | 54 | የወረዳው ቤተ ክህነት ኃላፊ | ፍኖተሰላም ጊዮርጊስ ደብር | ሰኔ 16፡ 2003ዓ.ም |
| መሪጌታ ዳዊት አብዩ | ወ | 41 | የወረዳው ቤተ ክህነት ፀሐፊ | ፍኖተሰላም | ግንቦት 7፡ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ፅጌ ተገኘ | ወ | 26 | የቅኔ ተማሪ | ፍኖተሰላም ባታ ደብር | ሰኔ 14፡ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ መንክር ግርማ | ወ | 19 | የዜማ ተማሪ | ባከል ገብርኤል | ሰኔ 15፡ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ማስተዋል ዓለሙ | ወ | 11 | የድጓ ተማሪ | የባዲ ሚካኤል | ግንቦት 10፡ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ኤፍሬም ንጉሱ | ወ | 24 | የቅኔ ተማሪ | የልምዳር አቦ | ግንቦት 8፡ 2003ዓ.ም |
| ተማሪ ገነት አለማየሁ | ወ | 24 | የቅኔ ተማሪ | ፍኖተሰላም ባታ ደብር | ሰኔ 14፡ 2003ዓ.ም |
| ወ/ሮ አገሪቱ አስማረ[2] | ሴ | 68 | የቤት እመቤት | የባዲ ሚካኤል | ሰኔ 20፡ 2003ዓ.ም |
| አስር አለቃ ማሞ ደምለው | ወ | 72 | አርሶአደር እና የሀገር ሽማግሌ | ባከል ገብርኤል | ሰኔ 22፡ 2003ዓ.ም |
| ቄስ ዘውዱ ተዋበ | ወ | 43 | አርሶአደርና የቤተክህነት አገልጋይ | የልምዳር አቦ | ግንቦት 5፡ 2003ዓ.ም |

[2] ሁለት የቆሎ ተማሪ ልጆች አሏቸው

አባሪ ሶስት

### የጃቢ. ጠህናን ወረዳ ቀበሌዎችና
### አዋሳኝ ወረዳዎች



ምንጭ፡- የጃቢ. ጠህናን ወረዳ ማስታወቂያ ጽህፈት ቤት

# አባሪ አራት
## የተጨማሪ ፎቶግራፎች ስብስብ



የቅኔ ተማሪዎች በማታ ጉባኤ ላይ



የቅኔ መምህር በማታ ጉባኤ ላይ



የተማሪ ጎጆዎች በከፊል



ተማሪዎች በጋራ የለመኑትን እንጀራ በፀሐይ ሲያደርቁ



ተማሪዎች ምግባቸውን በጋራ ሲቋደሱ



ተማሪ ለምኖ አመስግኖ ሲሄድ



ተማሪዎች ከቅኔ ቆጠራ ሲመለሱ



ተማሪው ድንጋይ ስር ቁጭ ብሎ ቅኔ ሲቆጥር



በማታ ጉባኤ ላይ ቅኔ ሲዘረፍ



አጥኚው ከተማሪዎች ከዜማ ተማሪወች ጋር



ተማሪዎች በተጣበበ ጎጇቸው በጋራ ሲኖሩ



ተማሪዎች በዜማ ልምምድ ላይ እያሉ

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የኔ የግል ስራ መሆኑንና በፅሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ጽሑፎችና መረጃዎችን በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡ የኔአሳብ የሠራህ

ፊርማ ____________

የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ

መስከረም 2004ዓ.ም